# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# ድኅረ-ምረቃ ት/ቤት

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ
ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት
ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና
የስህተት አይነቶችና
የስህተት ምንጮች
ትንተና

ደብሬ ተሰማ

ሰኔ 1990 ዓ.ም.

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

አማርኛን በማስተማር ዘዴ
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

በ
ደብሬ ተሰማ

አዲስ አበባ
ሰኔ፣ 1990 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድኅረ-ምረቃት/ቤት

በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ
ክፍል ተማሪዎች ድርሰት በሚፅፉበት
ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና
የስህተት አይነቶችና
የስህተት ምንጮች
ትንተና

በ

ደብሬ ተሰማ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

## ምሥጋና (Aknowledgement)

ከመነሻ እስከመድረሻ የጥናቱን ትክክለኛ አቅጣጫ በመጠቆም ከፍተኛ እርዳታ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ደጀኔ ለታ ልባዊ ምሥጋና አቀርባለሁ:: ለመልካም ትህትናቸውና ለበጎ ተግባራቸው የተለየ አክብሮትና አድናቆት አለኝ::

የጥናቱን ረቂቅ በማስተካከልና ጠቃሚ ምክሮችን በመስጠት ለረዱኝ ጓደኛዬ ለአቶ ሠለሞን ተሰማ እንዲሁም በዚህ የትምህርት ፕሮግራም እንድሳተፍ ላበረታቱኝ ለአቶ ደረጀ ገብሬ ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው:: ጥናቱን ባካሄድኩባቸው ት/ቤቶች ለጥናቱ መሣካት አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ ርዕሳነ መምህራንና የ11ኛ ክፍል መምህራንም ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ::

ከዲፕሎማ መርሀ ግብር ጀምሮ አሁን የደረስኩበት ደረጃ እስከምደርስ ድረስ የቤተሰቡን ሃላፊነት በመሸከም እንድማር ላደረገኝ ባለቤቴ ለአቶ ፀሐይ በላይ ምሥጋናዬ ከልብ ነው::

ትምህርቴን እንድከታተል የዘወትር ምኞቷ ለሆነው እናቴ ለወ/ሮ ይናኙ ሽበሽ እንዲሁም ከልጅነት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ የማቴሪያልም ሆነ የሞራል ድጋፉ ዘወትር ላልተለየኝ ወንድሜ ለአቶ አሉላ ተሰማ፣ ምክሯና እገዛዋ ላልተለየኝ እህቴ ወ/ት አገር ተሰማ ያለኝ ምስጋና ከፍተኛ ነው::

በመጨረሻም መረጃ ባሰባሰብኩበት ወቅት ከእኔ ጋር ከት/ቤት ት/ቤት የተዘዋወረውን ወንድሜን ፍቃዱ ዓለማየሁን ከልብ አመሰግናለሁ::

# አኅፅሮተ-ጥናት (Abstract)


የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች የስህተት ብዛትና ድግግሞሻቸውን እንዲሁም ዋና ዋና የስህተት ምንጮቹን ለመለየት ነው::

ለጥናቱ ዓላማ በናሙናነት የተመረጡት ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሲሆኑ፤ በነዚህ ት/ቤቶች በ11ኛ ክፍል ውስጥ ከሚማሩ 480 የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎች መካከል 50% ያህሉን በመውሰድ 240 ተማሪዎች በቀጥታ በጥናቱ ተሳትፈዋል:: አስፈላጊው መረጃም በድርሰትና በመጠይቅ አማካይነት ተሰብስቧል::

ለጥናቱም የሚያስፈልጉት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በስህተት ትንተና የአተናተን ዘዴ መሰረት ስህተቶቹ በዓይነት ተልይተውና ተቆጥረው ተተንትነዋል:: በተገኘው ውጤት መሠረትም በአጠቃላይ ድርሰቶቹ የተፈፀመው የስህተት መጠን 9818 ሲሆን አማካይ ድግግሞሹም 27.17 ሆኗል:: በዚህ የስህተት መጠንና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ አምስት ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች የተፈፀሙ ሲሆን እነዚህም የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ብዛት 45.71%፣ አማካይ ድግግሞሹ 12.42%፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት 19.56 በመቶ አማካይ ድግግሞሹ 5.31%፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት 19.37 በመቶ አማካይ ድግግሞሽ 5.26%፣ ለመለየት ወይም ለመፈረጅ ያልተቻሉ ስህተቶች 8.03 በመቶ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ 2.18% እና የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት 7.33 በመቶ፣ አማካይ ስህተት ድግግሞሽ 1.99 ሊሆኑ እንደቻሉ ጥናቱ አመልክቷል:: በጥናቱ በተገኘው የስህተት ትንተናና የመጠየቅ መረጃዎች ውጤት መሠረትም ዋና ዋናዎቹ የስህተት ምንጮች ውስጠ-ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደትና የሥነ ልቦናዊ ተፅዕኖ መሆናቸው ተመልክቷል::

የጥናቱን አጠቃላይ ውጤት መሠረት በማድረግም የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፈቺ ተማሪዎች ችግር የሚቃለልበትን፣ መርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፍ አዘገጃጀትን የአማርኛ ክፍለ ጊዜን፣ የመምህራን ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ኮርስን ... በሚመለከት አስተያየቶች ቀርበዋል::

## ማውጫ

ዝርዝር | ገጽ


ምሥጋና (Acknowledgement ) ........................................ i

አህጽሮተ ጥናት (Abstract) ........................................ ii

የሠንጠረዥ ማውጫ ........................................ vi

ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the Study) ........................ 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ (Objectives of the Study) ........................ 3

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study) ............ 4

1.4 የጥናቱ ክልል (Area of the Study) ........................ 4

1.5 የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study) ........................ 5

1.6 የቁልፍ ቃላት ትርጉም (Definition of Terms) .......... 5

1.7 የጥናቱ አወቃቀር ........................................ 7

ምዕራፍ ሁለት :- ክለሳ ድርሳን (Review of Related Literature) ... 8

2.1 የስህተት ምንነት ........................................ 8

2.2 የስህተት ምንጮች ........................................ 12

2.2.1 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ........................ 13

2.2.2 ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ........................ 15

2.2.3 የመማር ማስተማር ሂደት ........................ 18

2.2.4 ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ........................ 19

2.3 የስህተት ትንተና ዘዴ ........................................ 21

2.3.1 የስህተት ትንተና ምንነት ........................ 21

2.3.2 የስህተት አተናተን ችግሮች ........................ 23

2.3.3 የስህተት ትንተና ጠቀሜታዎች........................ 24

2.3.4 በስህተት ትንተና ዘዴ የተጠኑ ጥናቶች .............. 25

2.3.5 የስህተት ትንተና ጥበቦች ........................ 30

ምዕራፍ ሦስት:- የአጠናን ዘዴ ........................................ 34

3.1 የት/ቤቶች የመምህራንና የተማሪዎች አመራረጥ .............. 34

3.1.1 የት/ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........................ 34

ገጽ


3.1.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ .......................... 34
3.1.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ .......................... 34
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች .......................... 35
3.2.1 መጠይቅ .......................... 35
3.2.1.1 የተማሪዎች መጠይቅ .......................... 35
3.2.1.2 የመምህራን መጠይቅ .......................... 36
3.2.2 ድርሰት .......................... 37
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ .......................... 38
3.3.1 የድርሰት መልመጃዎች አተናተን .......................... 38
3.3.2 የስህተት ምንጭ መላምቶች ትንበያ .......................... 40

ምዕራፍ አራት፡- የጥናቱ ውጤት ትንተና .......................... 41
4.1 አጠቃላይ የስህተት ብዛትና የመልመጃ አይነት .......................... 43
4.1.1 ዋና ዋና የስህተት ዓይነት ምድቦች .......................... 43
4.1.2 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች .......................... 48
4.1.2.1 የቃላት አጠቃቀም .......................... 48
4.1.2.2 ግድፈት .......................... 58
4.1.2.3 የኢ-መደበኛ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም 59
4.1.2.4 የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ....... 61
4.1.2.5 ተደጋጋሚነት .......................... 62
4.1.3 የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች .......................... 63
4.1.3.1 የዓረፍተ ነገር ስምሙነት .......................... 64
4.1.3.2 የመስተአምር፣ የመስተዋድድና ተሳቢ አገባብ .......................... 67
4.1.3.3 የአጣማሪዎች አገባብ .......................... 70
4.1.4 የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች .......................... 71
4.1.4.1 አራት ነጥብ .......................... 72
4.1.4.2 ነጠላ ሰረዝ .......................... 73
4.1.5 ለመለየት የሚያስቸግሩ ስህተቶች .......................... 75
4.1.6 የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች .......................... 77
4.2 የስህተት ምንጭ መላምቶች .......................... 79
4.2.1 ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ .......................... 79
4.2.2 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ .......................... 86

ገፅ

4.2.3 የመማር ማስተማር ሂደት ...................................... 94

4.2.4 የሥነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ...................................... 102

ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት ...................................... 104

5.1 ማጠቃለያ ...................................... 104

5.2 አስተያየት ...................................... 111

አምደ ቃላት ...................................... 113

ዋቤዎች ...................................... 114

አባሪዎች ...................................... 117

1. ለተማሪዎች የተበተነ መጠይቅ ...................................... 117

2. ለመምህራን የተበተነ መጠይቅ ...................................... 127

3. ለተማሪዎች የተሰጠ የድርሰት መልመጃ ...................................... 137

4. የቲ ስሌት መግለጫ ...................................... 140

5. የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች ምሳሌዎች ...................................... 141

6. የቋንቋ አወቃቀር የስህተት ምሳሌዎች ...................................... 147

7. ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ምሳሌዎች ...................................... 149

8. የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት ምሳሌዎች ...................................... 151

9. የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ምሳሌዎች ...................................... 153

## የሠንጠረዥ ማውጫ


| ሠንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | የመልመጃዎች ዓይነት፣ የድርሰቶቹ የተፃፉባቸው ቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛትና መቶኛ፣ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ ........................................................................ | 42 |
| 2 | በዋና የስህተት ዓይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠሩ ስህተቶች ብዛትና መቶኛ፣ አማካይ ስህተትና ድግግሞሽ በመልመጃዎች ዓይነት .......................................................................... | 43 |
| 3 | በድርሰት አንድና ሁለት መካከል ያለ ንፅፅራዊ የስህተት ውጤት ............................................................................. | 45 |
| 4 | የዐቢይና የንዑስ ስህተት ዓይነት ምድቦች፣ የስህተት ብዛት መቶኛ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ በመልመጃዎች ዓይነት ........................................................................... | 47 |
| 5 | ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸውን የስህተት ዓይነቶችና ምክንያት በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ.................... | 91 |
| 6 | ተማሪዎች ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው የስህተት መጠኖችና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የሚፈፀም የስህተት መጠንን በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ መልሶች ......... | 92 |
| 7 | በፅህፈት ልምምዱ ጊዜ ችግር የሚፈጥሩ ነገሮች፣ የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮችን በተመለከተ ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ መልሶች ............................................ | 93 |
| 8 | የክፍልና የቤት ሥራ ልምምድን በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ............................................. | 95 |
| 9 | የክፍልና የቤት ሥራ ልምምድን በሚመለከት የተማሪዎች መጠይቅ ምላሽ ........................................................... | 97 |
| 10 | በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ የመምህራኑን የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለመምህራኑ የቀረበ መጠይቅ ምላሽ .................. | 98 |
| 11 | ፅህፈትን ለማለማመድ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን ማቴሪያሎች በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ ምላሾች ........ | 100 |

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ /Background of the Study/

ጽህፈት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ክሂል ከመሆኑ ባሻገር ለቋንቋው አፊ ፊት ተናጋሪዎችም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከንግግር ይበልጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ በርካታ ስህተቶችን ይፈጽማሉ። አንድ ሰው በጽህፈት አማካኝነት ለመግባባት ሲያስብ የሚፈልገውን መልእክት ለተቀባዩ ለማስተላለፍ በተጨማሪነት ለድጋፍ የሚቀርቡ ምልክቶች /የፊት ገጽታ÷ መሳቅ÷ ማዘን÷ የድምጽ ጫና÷ የንግግር መደጋገም የመሳሰሉት ነገሮች /አይኖሩም። ከዚህም የተነሳ ጸሃፊው የሚያስተላልፈው መልዕክት ለተቀባዩ ግልጽ እንዲሆንለትና አሻሚ የሆኑ ነገሮች እንዲቀሩ ለማድረግ ተማሪዎች ጽህፈት ከመጻፋቸው በፊት በጥንቃቄ የተሞላ ቅደመ ዝግጅትና በቂ ልምምድ እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል። /ኖሪሽ 1990÷ 63-6/

ምንም እንኳን ጽህፈት ከላይ የተገለጹት ችግሮች ቢታይበትም የሰው ልጅ ሃሳቡን ለሌሎች ቀርጾ ለማቆየትና ለማስተላለፍ ይችል ዘንድ የጽህፈት ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልገው ይታመናል። ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ ሥርአተ ትምህርት ተነድፎለት ከወጣበት ከ1944 ዓ.ም. ጀምሮ የአማርኛ የድርሰት ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ለመሆኑ በትምህርት ሚኒስቴር በ1970÷1981÷1984... /ከተጻፉ ጽሁፎች ለመገንዘብ ተችሏል።

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥበት አጠቃላይ አላማዎችም አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ስርዓት ጠብቆ ድርሰት÷ ደብዳቤ÷ ሪፖርት... መጻፍ እንዲችል ለማድረግ መሆኑ በስርዓተ ትምህርትና ሱፐርቪይዥን ዋና ክፍል በ 1970 ዓ.ም. ከ7ኛ-12ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ተገልጿል። ይሁን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ አቀናብረው መልእክት ለማስተላለፍ የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑ በሰፊው እየተነገረ ነው።

ይህንኑ የጽህፈት ችግር በማስመልከትም ባዩ/1984÷8/ ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የቋንቋ ትምህርት በሰዋሰው ላይ ያተኩር እንደነበርና አሁን ጊዜ ደግሞ በክሂል ዘርፎች ላይ እንዳተኮረ ገልጸው ሆኖም ግን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት በሚታይበት ጊዜ እንኳንስ ትምህርታቸውን ያላጠናቀቁት ቀርቶ አስራሁለተኛን ያጠናቀቁትም ቢሆኑ ሌላው ቢቀር የማመልከቻ ደብዳቤ መጻፍ እማይችሉበት ደረጃ እንደደረሱና በጥቅሉም ተማሪዎቹ ከቋንቋው ስርዓትም ሆነ ከክሂሉ እንደሌለበት ገልጸዋል፡፡

ከተወሰኑ አመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መጨመርና የትምህርቱ ክፈለ ጊዜ በመብዛቱ እየተመካኘ ተማሪዎች የሚጽፉት ነገር ትክክል ይሁን ስህተት ሳይታረም መቅረቱ በጽህፈት ላይ ችግር ያስከተለ ጉዳይ መሆኑን ተስፋዬ (1986÷9-10) ገልጸውታል፡፡

ሰለሞን /1987/ በተማሪዎች መብዛት የተነሳ በተማሪዎች የድርሰት መልመጃዎች ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች በአፋጣኝ ከመምህራኑ ምላሽ ባለማግኘታቸው የተማሪዎቹ የጽህፈት ችግር በየጊዜው እየታየ መሄዱን ጠቅሰው ይህንኑ ችግር ለማቃለልም "የቢጤ እርማት" ስልትን በተጠኝነት በተመረጡ የናሙና ተማሪዎች ላይ ሙከራ አድርገዋል፡፡

ማረው /1987፡1/ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው ውስጥ በቅርብ ጊዜ ከተካሄዱ ጥናቶች በመነሳት በርካታ አጥኚዎች የተማሪዎች ድርሰት በስህተት የተሞላ ለመሆኑ በጋራ የተስማሙበት ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው ለነዚህም ስህተቶች መከሰት ምናልባትም ከመምህራኑ የማስተማር ስልትና መጻህፍት በብዛት ካለመዘጋጀታቸው ሊሆን እንደሚችል ኃይለሚካኤል /1993/ን በመጥቀስ ገልጸውታል፡፡

በሌላም በኩል ነጋሳ /1965/ ና ታደሰ /1979/ ለመጀመሪያ ዲግሪ ሚሟያ ያቀረቧቸው ጥናቶች ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች

የሚጠቁሙ ሲሆኑ በቅርቡም ክፍሌ /1986/ ና አለማየሁ /1986/ በሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያ ጥናታቸው ላይ ይኸው ችግር የሚታይ መሆኑን አመልክተዋል። አለማየሁ /1986/ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ዋና ዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች በማለት የተማሪዎቹን ድርሰቶች በስህተት ትንተና ዘዴ ከመረመሩ በኋላ ዋና ዋና ያሏቸውን የስህተት አይነቶችና ምንጮች ጠቁመዋል።

ስለሆነም በተማሪዎች ጽህፈት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶችና የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የገመገሙ ስራዎችና የዲግሪ ሟሟያ ጥናቶች በሚታዩበት ጊዜ በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ በርካታ የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀም÷ የቋንቋ አወቃቀር÷ የጽንስ ሃሳብ ግንዛቤ÷ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና የአረፍተ ነገርን ትክክለኛ አሰካክ ጠብቆ የመጻፍና ሃሳብን አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታቸው አነስተኛ እንደሆነና በጥቅሉም የጽህፈት ልምምዱ እድገት እያሳየ ያለመሄዱን ያመለክታሉ።

ሆኖም ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን በጽሁፍ ለመግለጽ ያለባቸውን ችግር በስህተት ትንተና ዘዴ በማጥናት የስህተት አይነቶቹንና የስህተት ምንጮቹን ለይቶ ለማወቅና መፍትሄ ለመፈለግ የተደረጉት ጥናቶች ብዙ አይባሉም። ስለዚህ የዚህ ጥናት አነሳሽ ችግርም የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶችንና የስህተት ምንጮችን በስህተት ትንተና ዘዴ በማጥናት ውጤቱን ለመግለጽ ነው።

### 1.2. <u>የጥናቱ አላማ /objecctives of the Study/</u>

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ በመመርመር የሚፈጽሟቸውን የስህተት አይነቶችና ምንጮች ለመለየትና ለስህተቶቹ መቃለልም የመፍትሄ ሃሳብ ለመጠቆም ነው።

ጥናቱ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

1. ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምን ምን ናቸው?

1.1. የስህተቶቹ ብዛት ምን ያህል ነው?

1.2. ድግግሞሻቸውስ?

2. ለነዚህ ስህተቶች መከሰት የስህተት ምንጮች ይሆናሉ የተባሉት ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ስለሆነም ጥናቱ እነዚህን መሰረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች ለመመለስ ከሚገኘው ውጤት በመነሳት በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የሚፈጽሙትን የስህተት አይነቶች ለመቆጣጠር የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመጠቆም ይሞክራል።

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት /Significance of the Study/

ጥናቱ ቀጥሎ በሚገለጹት ጉዳዮች ምክንያት አስፈላጊ ሆኗል፥

1. በጥናቱ አላማ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ያስችላል።
2. ለኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በማስተማር ረገድ ውጤት ሊያስገኙ የሚያስችሉ ስልቶችን ለመምረጥ ይረዳል።
3. ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም ለኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተሻሽለው የሚዘጋጁበትን መንገድ ይጠቁማል።

## 1.4. የጥናቱ ክልል /Area of the Study/

ጥናቱ የተካሄደው በሰሜን ኦሮሚያ በሰላሌ ወረዳ ከሚገኙ የመንግስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል በሙከጡሪ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፥ በፍቼ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትና በገብረጉራቻ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ነው። ዝርዝር ሁኔታውም በክፍል ሶስት የት/ቤቶች፥ የተማሪዎችና የመምህራን ናሙና አመራረጥ ላይ ይቀርባል።

## 1.5. የጥናቱ ወሰን /Scope of the Study/

በጥናቱ አቢይ ትኩረት በተሰጣቸው ት/ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈጽሙትን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ መተንተን ነው። ጥናቱም በቋንቋ አጠቃቀም የቋንቋ አወቃቀር፥ የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ፥ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ያተኩራል።

## 1.6. የቁልፍ ቃላት ትርጉም /Definition of Terms/

ስህተት /Error/- በዚህ ጥናት ውስጥ "ስህተት" የተሰኘው ቃል በተጠኝነት የተመረጡት ተማሪዎች በሚጽፏቸው ደርሰቶች ውስጥ የተፈጸሙትን የቋንቋ አጠቃቀም፥ የቋንቋ አወቃቀር፥ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፥ የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤና ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶችን የሚመለከት ነው። ኖሪሽ /1990:71/፥ ሞርሴይ /1983:196 ና ብራውን/1994:205/ እንደሚሉት ስህተት "መሰረታዊ"ና "ውሱን" ተብሎ በሁለት የሚከፈል ነው።

መሰረታዊ ስህተት /Global Error/- ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጪ ስርአታዊ በሆነ ሁኔታ ማፈንገጥ ሲሆን ይህም በቋንቋ ለመዳ ወቅት ሊከሰት የሚገባውና የሚታወቅ የተማሪው የቋንቋ ችሎታ ነጸብራቅ ነው። አለማየሁ /1986:8/ ዱሌይበርትና ክራሼን /1982/ን በመጥቀስ ስህተት የአንድን አ.ነገር ቅንብር የሚያፋልስና መግባባትን የሚያግድ ነው ይሉታል።

ውሱን ስህተት /Local Error/

ሀ- ግድፈት:- ወጥ ባልሆነ ሁኔታ ወይም ተመሳሳይነት ባልኖረው ሁኔታ ተማሪው የቋንቋውን ቅርጽ በመማሩ አንዳንድ ጊዜ ነገሩን በትክክል ሲያገኘው ሌላ ጊዜ ደግሞ የተሳሳተ ቅርጽ

ይፈጽማል። ሆኖም ስህተት ፈጻሚው ስህተቱን አውቆ በቀላሉ ሊያርመው የሚችልና የተማሪው የቋንቋ ብቃት ነጸብራቅ ነው።

ለ-ዝንጋታ- በማንኛውም ሁኔታ ግድፈትም ያልሆነ ስህተትም ያልሆነ የተሳሳተ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚገልጽ ሲሆን ይህም ከትኩረት ማነስ፥ በስራ ምክንያት፥ ከሰውነት መዛልና መድከም የተነሳ የሚከሰት ነው።

የቋንቋ አወቃቀር ስህተት:- በዚህ ጥናት ውስጥ "የቋንቋ አወቃቀር ስህተት" ሲባል በአ.ነገር ስምምነት /ባለቤትና ግስ፥ ጾታ፥ መደብ፥ ቁጥር/ መዛባት፥ በአጣማሪዎች አጠቃቀም /መገደፍ ወይም መጨመር ያለቦታው ማስገባት/ ፥በመስተዋድዶችና መስተአምሮች አጠቃቀም.../ መገደፍ ወይም መጨመር ያለቦታው ማስገባት /የተነሳ የሚከሰት የዐ.ነገር ቅንብር ወይም ቅደም ተከተል መፋለስ ነው።

የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት: ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በቃላት አመራረጥና አመሰራረት፥ በቃላት አደራደር፥ በቃላት አውዳዊ አገባብና በቃላት ፍቺ ምክንያት ያለውን የዐ.ነገር መዛባት የሚያመለክት ነው።

የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት: ምንም እንኳን መደበኛ የሆነ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ባይኖርም በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ውስጥ ይበልጥ የተለመዱትን የነጠላሰረዝ፥ አራት ነጥብ፥ የጥያቄ ምልክትና ቃለ-አጋኖ ምልክት በዐ.ነገሩ ውስጥ በተገቢው ስፍራ አለመዋልን የሚያመለክት ነው።

የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተት፡ ይህ የሚያመለክተው የቃሉን ወይም የአባባሉን ምንነት ካለመገንዘብ የተነሳ ለቃሉ ወይም ለአባባሉ ተቀራራቢ የሆነ ወይም የተለየ ፍች የሚሰጥበት ሁኔታ መሆኑን ነው።

ለመለየት ያልቻሉ ስህተቶች፡ ከነዚህ ከላይ ከተገለጹት ውጭ የሆነ ወይም ግልጽ ያልሆነ ማለት ነው።

## 1.7. <u>የጥናቱ አወቃቀር</u>

ጥናቱ አምስት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለጥናቱ ስራ መንስኤ አላማና ጠቀሜታ ሃሳብ የሚሰጥ፥ ሁለተኛው ለጥናቱ ተዛማጅ የሆኑ ክለሳ ድርሳናት የቀረበበት፥ ሶስተኛው የጥናቱ የአጠናን ዘዴ ማለትም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፥ የአሰባሰቡ ሂደት፥ የተሰበሰቡት መረጃዎች የአተናተን ስልት የተገለጹበት፥ ምእራፍ አራት የተሰበሰቡት መረጃዎች ውጤት በመተንተንና ማብራሪያ በመስጠት በጥናቱ ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበት ሲሆን የመጨረሻው ምዕራፍ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት አስተያየትና ማጠቃለያ የሚሰጥበት ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳድርሳን /Review of Related Literature/

### 2.1. የስህተት ምንነት

እስካሁን ድረስ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ግድፈቶችና ስህተቶች በተመለከተ ሁለት የተለያዩ መሠረታዊ አመለካከቶች አሉ፡፡ አብዛኞቹ መምህራን ስህተት በተማሪዎች ድክመት የሚመጣ እንደሆነ አድርገው የሚገምቱ ሲሆን ይህም ትምህርቱ በሚሰጥበት ጊዜ በሚገባ ካለማዳመጥ፥ ለትምህርቱ በከፊል ትኩረት ከመስጠት፥ ከመምህሩ የትምህርት አሰጣጥ ወይም ደግሞ ለተማሪዎች የሚለማመዱበት በቂ ጊዜ ካለመስጠት የተነሳ የተከሰተ ነው የሚሉ ሲሆን፥ ሌሎች ደግሞ ግድፈትና ስህተት መፈጸምን በትክክል የትምህርቱ የመጀመሪያ አካል እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል፡፡ በመሆኑም ስህተት እንደ ድክመት ምልክት ተደርጎ መታየት የሚገባው ሳይሆን የተማሪው የቋንቋ ለመዳ ስርአታዊ ዕድገትና ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚጠቀሙበት ጊዜ ያለው ሂደት እንዴት እንደሆነ ምልክት የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚፈጸሙትን ስህተቶች እንደጉድለት በሚቆጥሩና መወገድ ያለባቸው መሆኑንም በሚያምኑት ዘንድ ተማሪዎቹ ስህተት መፈጸማቸው በመምህሩም ሆነ በተማሪዎቹ ዘንድ ዋጋ የሚያሳጣ ተደርጎ የሚወሰድ ስለነበር በርካታ ስህተቶችን መፈጸማቸውም ተግሳጽንና ቁጣን ያስከትልባቸው ነበር፡፡ /ሊትልውድ፥1986፡225፥ ኖሪሽ፥ 1990፡1/

በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ግድፈትን ወይም ስህተትን ላለመፈጸም ይፈራሉ፡፡ የፍርሃታቸው ምንጭም ተማሪዎቹ ግድፈት ወይም ስህተት በሚፈጽሙበት ጊዜ በቋንቋው አፍ ፈቺ ተማሪዎች፥ በክፍል ጓደኞቻቸውና በመምህራቸውም ዘንድ ይሳቅብናል፥ ይፌዝብናል፥ ቂል ያስመስለናል ከሚል ፍርሃት የተነሳ በትምህርቱና በተማሪዎቹ ላይ ጥላቻ ያድርባቸዋል፡፡ /ኖሪሽ፥ 1990፡1/

ሊንድማን /1996፡112/ እንደሚሉት ስህተት የመማር ሂደቱ አንዱ አካልና ትምህርቱም በንቃት ለመካሄዱ ጠቃሚ ምልክት ነው፡፡ ስህተት ቀደም ሲል በልማዳዊ

ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች /ቃላትን በማጥበቅ፥ በንቃት ባለመከታተል፥ ሃሳበ ብኩን በመሆን ወይም የእውቀት ማነስ.../ ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ማፈንገጥ እንደሆነ ተደርጎ ይገለጽ ነበር። ሆኖም በውጭ ቋንቋዎች ተማሪዎች ላይ ከተካሄደ ምልከታዊ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከታላሚው ቋንቋ አገባብ አለማፈንገጥም ስህተት ላለመፈጸም ዋስትና ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ የጀርመንኛ ቋንቋን የሚማር አንድ ኖርዌጅያዊ ተማሪ በሰዋሰው በኩል ትክክለኛ የሆነ ሀ.ነገር ሊመሰረት ይችላል። ነገር ግን ስለጻፈው ጉዳይ እንደገና ሀ.ነገር እንዲጽፍ ቢጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ከበፊቱ የተለየ ሊሆን ይችላል። ይህም ሊከሰት የቻለው ሃሳቡን በትክክል ካለመገንዘብ የተነሳ ይሆናል። በእያንዳንዱ የቋንቋ ተማሪ የሚፈጸሙ ስህተቶችም የተማሪው ዕድገት አመልካቾች እንዲሆኑ ተደርገው መቆጠር ያለባቸው ናቸው።

እንደ ሊንድማን እምነት ተማሪዎች በቋንቋው ላይ ካላቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ ግብአትና አጠቃቀም በመነሳት ስለታላሚው ቋንቋ ስርአት መላምታቸውን እየመሠረቱ ይሄዳሉ። መምህራን ግን በቋንቋ ለመዳው ሂደት ተማሪዎቹ የሚያመነጯቸውን ነገሮች አውድ በማየት ስህተቶቹን ካልገመገሙ በስተቀር በተማሪዎቹ ላይ ይህን ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለው ብያኔ ሊሠጡ አይችሉም። ስለሆነም የዚህ አይነቱ ግንዛቤ ሊኖር የሚችለው መምህራኑና ተመራማሪዎቹ በተማሪዎቹ ደረጃ በመምጣትና የተማሪዎቹንም ባህርይ ለማጥናት ሰፊ ምልከታ የሚያካሂዱ እስከሆነ ድረስ ነው።

በሌላም በኩል ሁሉም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በሚካሄድበት ጊዜ ተማሪዎቻቸው የተለያዩ ስህተቶቹን እንደሚፈጽሙ ያውቃሉ። እነዚህ ስህተቶችም በተማሪዎቹ የንግግር ቋንቋ ወይም የጽህፈት ቋንቋ ላይ የሚታዩና ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ለመናገር ወይም ለመጻፍ በሚያፈልቅበት ጊዜ ከስነድምጽ፥ ሰዋሰው፥ ከቃላትና አጻጻፍ ያፈነገጡ ሲሆን ስህተቶቹም ሰዋሰዋዊ፥ አነባበባዊ፥ የአጻጻፍ ስህተቶችና የአጠቃቀም ስህተቶች ናቸው። ስለሆነም አንድ አንባቢ ወይም አድማጭ እነዚህን ስህተቶች የሚገነዘባቸው ከታላሚው ቋንቋ ስነልሳናዊ ህግ የተለዩ መሆናቸውን ነው።/ ነጋሪ፥ 1983፡35/

ነጋራ ለጥናታቸው መነሻ አድርገው ያቀረቡት ከተጻፉ ድርሰቶች ያገኟቸውን መረጃዎች በመንተራስ ሲሆን አብዛኞቹ ምሳሌዎች የተወሰዱት ከሌሶቶና ስዋዚላንድ ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎችም የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ከሚገኙባቸው ከቦትስዋና፥ ደቡብ አፍሪካና ዝምባቡዌ ዩኒቨርሲቲዎች ነው፡፡ አብዛኞቹ ምሳሌዎች ከዩኒቨርሲቲዎች የአንደኛ አመት ተማሪዎች ሌሎቹ ደግሞ ከዝምባቡዌ የሁለተኛ አመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጽሁፎች ላይ የተወሰዱ ነበሩ፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ያረፈው የሁለተኛ ቋንቋውን ለረጅም አመት የሚያውቁ ተማሪዎች በፈጸሟቸው ስህተቶች ላይ ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች ለረጅም አመት ለታላሚው ቋንቋ የተጋለጡ በመሆናቸው ለቋንቋው በመጀመሪያ ከተጋለጡት ይልቅ በርካታ ችግሮችን ለመወጣት ይችላሉ የሚል ግምት አላቸው፡፡

በስህተትና በግድፈት መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያዩ ስያሜዎች ሲሰጡ የቆየ ሲሆን ከነዚህም መካከል ኖሪሽ /1990፡7/ ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ባሉት ባህርያት/ ማለትም በስህተት፥ ግድፈትና በንግግር መሃል የሚፈጸም ትንሽ ስህተት / መካከል ያለውን ልዩነት መለየቱ ጠቀሜታ እንዳለው ያስገነዝባሉ፡፡ ስህተት ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ስርአታዊ በሆነ ሁኔታ ማፈንገጥ ማለት ሲሆን ይህም ተማሪው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ያልሆነን ነገር በመማሩ የሚፈጸም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ተማሪው አንድን የቋንቋ ቅርጽ ይማራል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ተመሳሳይ ባልሆነ ሁኔታ ሌላ ቅርጽ ይማራል፥ በመሆኑም በዚህ ወጥ ባለሆነ ሁኔታ መማሩ መሳሳትን ያስከትላል፡፡ ይህ መሳሳት ደግሞ "ግድፈት" ይባላል፡፡ ግድፈት ሲባልም ተማሪው አንዳንድ ጊዜ ነገሩን በትክክል ሲያገኘው ሌላ ጊዜ ደግሞ ስህተት በመፈጸም በተሳሳተ ቅርጽ ይገለገልበታል፡፡ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ግድፈትም ያልሆነ ስህተትም ያልሆነ የተሳሳተ የቋንቋ አጠቃቀም ይከሰታል፡፡ ስህተቱም ከትኩረት ማነስ፥ ከዝንጋታ፥ በስራ ምክንያት ከሰውነት መዛልና መድከም የተነሳ የሚከሰት ነው፡፡ ይህም ቋንቋውን ይማሩትም አይማሩትም ወይም ደግሞ ሁለተኛ ቋንቋውን በሚማሩበት ጊዜ የተሰጠ የቋንቋው ቅርጽ ይሁንም አይሁንም ሊከሰት የሚችል ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታም ሞርሴይ /1983÷196/ የተለያዩ ምሁራንን ሃሳብ ወስደው እንደሚሉት ግድፈት በአፍ መፍቻ ቋንቋና በሁለተኛ ቋንቋ መማር ላይ የሚከሰት ሲሆን ይህም ስህተት ፈጻሚው ስህተቱን አውቆ በቀላሉ ሊያርመው የሚችለው አይነትና ኢስርዓታዊ ስህተት ወይም የቋንቋ ብቃት ስህተት በመባል የሚታወቀው ነው። ስህተት ስርአታዊ ስህተት ወይም የቋንቋ ችሎታ ስህተት በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህም በቋንቋ ለመዳ ወቅት ሊከሰት የሚገባው ነው።

ነጋሪ /1983፥6/ ከሞርሴይ ሃሳብ ባልተለየ ሁኔታ የግድፈትንና ስህተትን ልዩነት ይገልጹታል። እንደ እርሳቸው አስተሳሰብም የቋንቋ ብቃት ስህተት የሚፈጸመው ተማሪው ቋንቋውን ባለማወቁ ሳይሆን በሚናገርበት ወይም በሚጽፍበት ጊዜ በነበረ ጭንቀት÷ ጫና÷ መርሳት ወይም ግዴለሽነት የተነሳ ሲሆን÷ የስህተቶች መከሰት ግን ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ የማወቁን የደረጃ መጠን የግድ አያንጸባርቅም። የቋንቋ ችሎታ ስህተቶች የሚባሉት ግን ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በሚጠቀምበት ጊዜ ያለውን የቋንቋ ችሎታ ውሱንነት የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ብራውን /1994፥254-205/ ከሞርሴይና ነጋሪ ሃሳብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው አስተያየት ከሰጡ በኋላ የሰውን ልጅ ቋንቋን የመማር ሂደት ከዋና ሂደት ጋር በማመሳሰል ገልጸውታል። አንድ ዋናተኛ ዋናን ለመልመድ ውሃ ውስጥ ከገባ በኋላ ለመንሳፈፍና ለመዘዋወር እስኪችል ድረስ ክንዶቹንና እግሮቹን በማወራጨት ይማራል። ዋናውን በሚማርበት ጊዜም በመጀመሪያው ደረጃ በርካታና ጉልህ ግድፈቶች ይፈጽማል። ቀስ በቀስ ግን እየተማረ በመሄዱ የሚፈጸመው ስህተት እየቀነሰ ይሄዳል። አንድ ሰው ለመዋኘት÷ ቴኒስ ለመጫወት÷ ለመተየብ... በሚማርበት ሂደት ለሚፈጸሙት ስህተቶች ከአካባቢው ከሚገኘው አስተያየት በመነሳት ሌላ አዲስ ሙከራ እያደረገ ሄዶ የታለመውን ግብ ሊመታ ይችላል። ዋናተኛውም ዋናውን ይችላል። ቋንቋ መማር ሲባልም ከዚህ የተለየ ሳይሆን ልክ እንደሌላው የሰው ልጅ ትምህርት የሚወሰድ ነው። ስለሆነም ህጻናትም የአፍ መፍቻ ቋንቋውን ሲለምዱ ስህተቶችን ቢፈጽሙም በሌሎች ሰዎች ከሚሰጣቸው መረጃ-ምገባ በመነሳት በጥንቃቄ ግን በዝግታ

በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተቀባይነት ያለውን ንግግር ያፈልቃሉ፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደትም ካለው የስህተት መማር ባህሪው በግልጽ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለየ አይደለም፡፡ የማይቀረው ነገር ቢኖር ግን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ ሂደት ስህተት መፈጸማቸው ሲሆን፥ ስህተት የማይፈጽሙ ከሆነና ከፈጸሙት ስህተት በመነሳት ከሌሎች ሰዎች በተሰጣቸው የማስተካከያ ሃሳብ ማረም ካልቻሉ ግን የቋንቋ ለመዳ ሂደት ሊደናቀፍ ይችላል፡፡

በጥቅሉም ስህተቶች የቋንቋ ችሎታ ነጸብራቆች ሲሆኑ እነሱም ተማሪው በታላሚው ቋንቋ በሚገባ ያላወቃቸው አካባቢዎች የትኞቹ እንደሆኑ የሚያመለክቱ፥ የተማሪውንም ሆነ የአስተማሪውን ስራ በይበልጥ የሚጠይቁ፥ ቋንቋን እንዴት መማር ወይም መልመድ እንደሚቻል፥ ተማሪውን ቋንቋውን ለማሻሻል ምን አይነት ስልትና ስልተ-ትግበራ ሊከተል እንደሚገባው ለተመራማሪው ማረጋገጫ የሚሰጡ ናቸው፡፡ /ምርሴይ፥ 1983፡ 196፥ ነጋሪ፡ 1983 ፡6፥ ብራውን 1994፡ 204-205/፡፡ በሌላም በኩል ስህተት ተማሪው ለሚጠቀምበት የቋንቋ ስርዓት ማረጋገጫ የሚያቀርብና ተማሪው በትክክለኛው ስርዓት የማይጠቀም ከሆነ እንደገና በመድገም ከትክክለኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓት የሚያደርሰው ነው፡፡ /ስፖልስኪ፥ 1979፡250/

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት የሚከሰቱት የእነዚህ ስህተቶች ምንነትና ጠቀሜታ የተገለጸ ቢሆንም ለስህተቱ መፈጸም አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ የስህተት ምንጮችም እንዳሉ በተለያዩ ምሁራን ዘንድ በተለያዩ መልኮች ተጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ተከታይ ክፍል ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የተገመቱትን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 2.2. የስህተት ምንጮች /Sources of Errors/

በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ የተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምሁራን አማካኝነት ሲጠቀሱ ቆይተዋል፡፡ ከእነዚህም

መካከል ዋና ዋና የተባሉት የስህተት ምንጮች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፡ ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፡ የመማር ሂደቱ÷ ስነልቡናዊ ጉዳዮችና ሌሎችም ናቸው።

2.2.1. <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ</u>

ብራውን /1994:213-4/ እንደሚሉት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም ጣልቃገብነት ነው። ይህንን ጉዳይ ተመራምረው ካገኙት መካከል ታይለር /1975/ ዋነኛው ሲሆኑ፡ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን ስርዓት ከራሱ ጋር ከማዋሃዱ በፊት በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ከቀደምት ልምዱ ውስጥ ሊመጣለት የሚችለው ስነልሳናዊ ስርዓት የአፍ መፍቻ ቋንቋው ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ። ለምሳሌ የእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች " ship " ለማለት ሲፈልጉ "sheep" ÷ "Jack's book" ለማለት "the book of the Jack"ይላሉ። ስለሆነም እነዚህ ስህተቶች የሚታዩት ከአሉታዊ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር አንጻር ነው።

ሊትልውድ /1986:20-1/ በሁለተኛ ቋንቋ መማር የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነትንና የቋንቋ መማር በልምድ ተገኘ የሚለውን የባህርያውያን አስተሳሰብ ተቃዋሚ የነበሩትን ዱሌይናበርት /1973፡ 1974/ ስራዎች በመጥቀስ ምሁራኑ ዕድሜያቸው ከ5-8 አመት የሚደርሱ 145 እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የእስፓኒሽ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች ንግግር ካጠኑ በኋላ ያገኟቸውን ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስህተቶችና ዕድገታዊ ስህተቶች በማለት የከፋፈሏቸው መሆኑን ገልጸውታል። ከተፈጸሙት ስህተቶች ውስጥ 3% በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት÷ 85% ዕድገታዊ ስህተቶች፡ 12% ለመፈረጅ ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው። እንደሊትልውድ /1986/ አባባል ጥናቱ የሚጠቁመው "የፈጠራ ግንባታ" ከመጀመሪያ ቋንቋ ልማዳዊ ቅርጽ ይበልጥ ሀይለኛ ሂደት መሆኑን ሲሆን ዱሌይና በርትም /1973÷1974/ ለማሳየት የፈለጉት ይህንኑ ዕውነታ ነው። ሊትልውድ የመጀመሪያ ቋንቋ ሽግግር የሚባለውን ሙሉ በሙሉ የባህርያውያን ቲዎሪ ከሆነው ከልማዳዊ ቅርጽ ጋር ማያያዙ አስፈላጊ መሆኑን የማያምኑበት ሲሆኑ ለዚህም የሰጡት ምክንያት የመጀመሪያ ቋንቋ ሽግግር የፈጠራ ግንባታው ሂደት አካል ሊሆን ይችላል የሚል ነው። እንደሳቸው እምነት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ህጎችን ወደ ሁለተኛው ቋንቋ ማሸጋገር ተማሪው ሁለተኛ

ቋንቋውን በይሁንታ የሚለምድበት ስልት ሊሆን ሲችል ጣልቃገብነቱም አዎንታዊና አሉታዊ ሊሆን ይችላል።

ኖሪሽ /1990:41-2/ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት በአሁኑ ሰአት የሚኖረው ሚና አነስተኛ መሆኑን ቢገልጹም ለስህተት መፈጠር ምክንያት በመሆኑ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አልካዱም። ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋው መግባባት ቢፈልግና የዚያን ቋንቋ ተገቢ አገላለጽና የቋንቋ መዋቅር በሚገባ ባያውቅ የግዴታ ሀሳቡን ለመግለጽ ሲል ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋው መሄዱ የግድ ነው። በዚህም የተነሳ ስህተት ይፈጸማል። ቋንቋ ማለት ይኸ ነው ተብሎ በቀላሉ የሚገመት ሳይሆን ማለቂያ የሌለው በመሆኑ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ በቋንቋው ሊጠቀም በሚፈልግበት ጊዜ ማለትም ሲናገር ወይም ሲጽፍ ያልተማረውን ወይም ያልጻፈውን በመጻፍ ስህተት ይፈጸማል። በውጭ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚፈጸሙት ስህተቶች ምክንያቱ ተማሪው በክፍል ውስጥ ለተጋለጠበትና ይማረዋል ተብሎ በታሰበው ቋንቋ የሚወሰን ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ለሚፈጽመው ስህተት ምክንያቱ ተማሪው ከክፍል ውጭ በሚያጋጥመው ተጽዕኖ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው።

ነጋሩ /1983:36/ እንደሚሉት ለቋንቋ ችሎታ ስህተቶች ዋና የስህተት ምንጭ የሚሆነው እንደተለመደው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት ሲሆን ይህም የአሁኑዎቹ ጸሃፊዎች "አፕሮክስሜሽን" ብለው የሚጠሩት ነው። የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባህርይ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ወይም ግምታዊ በሆነ ሙከራ ቋንቋውን ያፈልቃሉ። እነዚህ አፕሮክስሜሽኖችም ከታላሚው ቋንቋ ትክክለኛ ቅርጽ ያፈነግጣሉ። በዚህም የተነሳ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ።

እንደሚታወቀው ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ እየተማረው ሲሄድ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ከታላሚው ቋንቋ ጋር ይበልጥ እየተዋሃደ የሚሄድ በመሆኑ የሚፈጠሩ ስህተቶችም ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ይገመታል። ይሁንና አንዳንድ ስህተቶች ግን ፈጽሞ ሊጠፉ አይችሉም። እንደነዚህ አይነት ስህተቶችም "ፎሲላይዝድ" በመባል የሚገለጹ ሲሆን እነዚህም የተማሪው ንግግር ቋሚ ባህርያት

እየሆኑ ይሄዳሉ። በሽግግር ስህተትና በፎሲላይዝድ ስህተት መካከል ያለውን ልዩነት ለመለየት ካስፈለገ ሽግግራዊ ስህተት የሚባለው ተማሪው ዕድገት እያሳየ ሲሄድ እየጠፋ የሚሄድ መሆኑ ሲሆን ፎሲላይዝድ ስህተት የሚባለው ደግሞ ሙሉ በሙሉ የማይጠፋው ነው በማለት ምሁራን አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።/ሊትልውድ፡ 1986፡34÷ ብራውን÷ 1994፡217/

ኖሪሽ /1990፡19/ እንደሚሉት ለስህተት መፈጠር እንደምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉት ነገሮች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ አንዱ ሲሆን ይህም የትርጉም ስራ በሚካሄድበት ጊዜ ሊፈጸም የሚችልና በአብዛኛውም የተለመደ ነው። የትርጉም ስራ በሚፈጸምበት ጊዜ ቃል በቃል የሚደረገው የቋንቋ አገላለጽ መንገድ ቀደም ብሎ የሚያውቀውን ቅላጼ እንዲያመነጭ ያደርገዋል። ለምሳሌ ኖሪሽ /1990፡21-26/ እንደሚሉት ከሆነ የጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች "I dont mind" ለማለት ሲፈልጉ "It makes me nothing out" ይላሉ። ወይም ደግሞ "It is about to start" ለማለት "Equal goes it loose" ይላሉ። ምንም እንኳን ጣልቃገብነትና ትርጉም ለስህተት መፈጠር ምክንያት ናቸው ቢባልም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ግን ሊታወቅ ይገባዋል። ስለሆነም ጣልቃገብነት ሲባል በተማሪው አእምሮ ምንም ሳይታሰብ የሚፈጸም ሲሆን ትርጉም ግን ተማሪው አማራጭ ሲያጣ የሚጠቀምበት ነው።

### 2.2.2. <u>ውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ /Intralanguage Interference/</u>

ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የሚታወቀው አሉታዊ ውስጠ ቋንቋ ሽግግር ስህተት ብያኔ የሚባለው ሲሆን ይህም አንድ ጊዜ ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን አዲስ ስርአት ከለመደ በኋላ የታላሚው ቋንቋ ሽግግር በይበልጥ እየጨመረ በመሄድ ስህተት የሚያመጣ ነው። /ብራውን÷ 1994፡ 214 እና ሊትልውድ÷ 1986፡23/። ይህንኑ በተመለከተም ነጋራ /1983፡36/ ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች መፈጠር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በርካታ ምሁራን "ስህተተ ብያኔ" ብለው እንደሚጠሩት ከገለጹ በኋላ ለውስጠ-ቋንቋ ስህተቶች መነሻ የሆኑትን ሶስት ጠቃሚ ጉዳዮች ተመራምረው በማግኘት እነዚህኑ ምክንያቶች ያልተሟላ ትምህርት÷ የተሳሳተ ቅንጅትና ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም ናቸው በማለት ይገልጿቸዋል። ነጋራ "ስህተተ ብያኔ" ማለት ምን ማለት

እንደሆነም ሲያብራሩ ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ያወቃቸውን የቋንቋውን ህጎች ወይም የስነልሳን ጉዳዮች በማይመለከተው ስፍራ ወይም ተገቢ ባልሆነ አውድ ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ከጠቆሙ በኋላ ይህም በቋንቋው ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ህግ በማስፋፋት የመጠቀም ጉዳይ እንደሆነ ገልጸውታል።

እንደነጋራ አስተያየት ለውስጠ ቋንቋ ስህተቶች ምክንያት ይሆናል ተብሎ የተገመተው ያልተሟላ የትምህርት ስህተት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪው ከታላሚው ቋንቋ መዋቅር÷ ከቃላቱ÷ ከአገላለጹ ወይም ደግሞ ከሆነው ሌላ ገጽታ ውስጥ ግማሹን ብቻ የተማረ በመሆኑና ሊያፈልቅ የሚችለውም ከመዋቅሩ÷ አገላለጹ... በከፊል በመሆኑ ከፊሉ ብቻ ትክክል ይሆናል። በዚህም ምክንያት ያልተሟላ ትምህርት ለስህተቱ መነሻ ይሆናል።

ያልተሟላ ትምህርት ስህተት የሚባለው የተለያዩ ዘርፎች ያሉት ሲሆን እነዚህም፡ 1) ያልተሟላ የሰዋሰው ህግ አዘገጃጀት፡ 2) ያልተሟላ የመስተዋድዳዊ ሀረግ ትምህርት፡ 3) ያልተሟላ የቋንቋ አገላለጽ ትምህርትና 4) ፍቹን (ትርጉሙን) በቀላሉ ለመለየት ወይም ለመገንዘብ ያልተቻሉ የቃላት አይነት ናቸው።

ትክክል ያልሆነ ዝምድና የሚከሰተው ተማሪው በታላሚው ቋንቋ የተማረው ስነልሳናዊ ቅርጽ በዚያው ቋንቋ ካለ ሌላ ቅርጽ ጋር በሚጋጭበት ጊዜና በመቀጠልም ከተለመደው የቋንቋ ስርአት ውጭ ያፈነገጠ ቅርጽ በሚያመነጭበት ጊዜ ነው። ትክክለኛውን የቋንቋ ቅርጽ ትክክል ካልሆነው ጋር የማዋሀዱ (የማዛመዱ) ጉዳይም ስነምዕላዳዊ÷ ፍችያዊ÷ ወይም ደግሞ ሰዋሰዋዊ ሊሆን ይችላል። "ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም" የሚባለውም መለያ ባህሪው ከፍተኛ ድምጽ ባላቸው ቃላትና በረጃጅም ዐ.ነገሮች ሲሆን ተናጋሪው ወይም ጸሃፊው በታላሚው ቋንቋ ያለውን ዕውቀት ለማመልከት በሚጨነቅበት ጊዜና ለአድማጪ ወይም አንባቢው ትኩረት ለመስጠት ሲፈልግ የሚከሰት መሆኑ ነው። ስለሆነም በዚህ ሁኔታ ሃሳቡን ለመግለጽ ሲፈልግ የተሳሳተ የቃላት አጠቃቀም፡ ትርጉም አልባ አገላለጽና የቃላት ግንባታ ሲከሰት

ትርጉም የለሽ ቃላትን መደርደሩም ያለአግባብ ቃላትን የመጠቀም የተለመደ ገጽታ ነው። /ነጋሪ፡ 1983፡37-9/

ብራውን /1994፡214/ እንዲህ አይነቱ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ቀደም ሲል ከተማሩት ያገኙት ቀደምት ልምድና በአእምሮአቸው የያዙትን የአወቃቀር ህግ ባጠቃላይ እንደሚሰራ አድርጎ ማምጣቱ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ሲታይ ከሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዕድገት የመማር ቲዎሪ ላይ የመጣ ነው ካሉ በኋላ ስህተት ብያኔ እና ሽግግር የተለያዩ ሂደቶች ሳይሆኑ ተመሳሳይ የሆኑ የቋንቋ መማር ስትራተጂን የሚወክሉ ናቸው ይላሉ። ሁለቱም ቢሆን ተማሪው አዲሱን ቋንቋ በሚለምድበት ጊዜ ስሜት እንዲሰጥ ለማድረግ ቀደም ሲል የሚያውቀውን የመጠቀም ውጤቶች ናቸው። "ስህተት ብያኔ" ሲባልም ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ወይም በሁለተኛው ቋንቋ በሚያውቀው ህግ ሌላውን ለማጠቃለል መሞከር ሲሆን "ሽግግር" በሚባልበት ጊዜ ግን ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋውን በሚማርበት ጊዜ ሃሳቡን ለማቀናጀት በአፍ መፍቻ ቋንቋው የሚያውቀውን ቀደምት ልምድ አምጥቶ መጠቀም ማለት ነው።

ሆኖም ሊትልውድ /1986፡25/ እንደሚሉት ለአንድ ለተወሰነ ወይም ለተለየ ስህተት መፈጠር ምክንያቱ "ስህተት-ብያኔ" ይሁን "ሽግግር" ለመለየት የማያስችሉ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ሌላው ቀርቶ ቀደም ባለው ጊዜ ለስህተት-ብያኔ በምሳሌነት ቀርበው የነበሩኳነገሮች ዛሬ እንደገና ለሽግግር የሚቀርቡ መሆናቸውንም ሊትልውድ ሳይጠቅሱት አላለፉም። ሊትልውድ /1986/ በመቀጠልም ሌላው ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናል ብለው የጠቀሙት ጉዳይ አስፈላጊ ጉዳዮችን በመግደፍ አላስፈላጊ ጉዳዮችን መደጋገምን ሲሆን በጥቅሉም ለስህተት መፈጠር ምክንያት ናቸው ያሏቸው 1) ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የተሸጋገሩ ህጎች፡ 2) የሁለተኛ ቋንቋ አጠቃላይ ህግና ስህተት ብያኔ 3) ነገሮችን መግደፍ ናቸው። እንደሳቸውም አባባል የመጀመሪያው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሂደት፡ ሁለተኛውና ሶስተኛው ደግሞ ውስጠ ቋንቋ ሂደቶች ናቸው።

### 2.2.3. የመማር ማስተማር ሂደት /Learning Teaching Process/

ኖሪሽ /1990፡ 12-15/ እንደሚሉት ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ÷ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል÷ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት÷ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች÷ በምሳሌዎቹ አማካኝነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ደግሞ ተማሪዎቹ እነዚህን ማቴሪያሎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ።

- ኖሪሽ /ኮርደር 1973፡283/ን ጠቅሰው እንደገለጹት ተማሪዎቹ ማቴሪያሎቹን ሲጠቀሙ ከሚፈጽሟቸው ስህተቶች በስተቀር ሌሎች ስህተቶች መምህሩ ሊለውጣቸው የሚችሉ በሱ ቁጥጥር ስር ያሉ ናቸው። ለስህተት መፈጠር ምክንያት ናቸው የተባሉት ነገሮችም ከማስተማር ሂደት ጋር የተያያዙ ቢሆኑም ተማሪዎቹ በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ግን ከመምህሩ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ከሰው ልጅ ስነአእምሮአዊ ክፍል የሚመደቡ ናቸው።

- ብራውተን /1993፡133-5/ እንደሚሉት ደካማ የማስተማር ዘዴ ለስህተት መከሰት ምክንያት ከመሆን ባያልፍም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮቹን እንዲከሰቱ የሚያደርጉ ከመምህሩ ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ነገሮች አሉ። ለዚህም መርሃ ትምህርቱ በሚታይበት ጊዜ ሁልጊዜ ከብዙዎቹ ነባር መምህራን ዕውቀትና ሃሳብ ጋር የተያያዘ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ቀደም ሲል ይሰጡ የነበሩ ጥንታዊ ትምህርቶች በሚታዩበት ጊዜ ከአንድ የማስተማር ሂደት ወደሚቀጥለው ሲሸጋገሩ መስመራዊ ግንኙነቶችን የተከተሉ ነበሩ። በዚሁ አይነት መንገድ ከአመታት በላይ መርሃ ትምህርቱ ለብዙ ጊዜ ዋና ዋና መዋቅራዊ ጉዳዮችን በጥልቀት ይሸፍን ነበር። እዚህ ላይ የሚታየው ችግር ታዲያ ተማሪዎቹ አንድ ነገር ላይ ትኩረት በመስጠት አብላልተው ከሚገባው በላይ ሲሰሩት፡ ያ አንድ ጊዜ ያለቀለት ርዕስ በሌላም ጊዜ እየተደጋገመ መጠቀሱና ተግባራዊ የመሆኑ ጉዳይ ለስህተቱ መከሰት ምክንያት ይሆናል።

- ሌላው ዋና የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ በብራውን /1994፡215-6/ የተገለጸው ጉዳይ የትምህርቱ አውድ ሲሆን ይህም በሁሉም አይነት ሽግግር በተደራራቢ የሚመጣ ነው። አውድ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከመምህሩ አቀራረብ ወይም ደግሞ ከክፍል ውጭ ባለው ሁኔታ እንጻር

የሚጠቀስ ነው። እንደብራውን አባባል ከመምህሩ በሚሰጠው የተሳሳተ ገለጻ፣ የተዛባ የቋንቋ አወቃቀር ወይም በመማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ያሉ የቃላት አወቃቀር ወይም ደግሞ ከተደረገው ልምምድ መካከል ተማሪው በልቡ የሚያስበውን ማስታወሱ… ከአውዱ ውጭ በመሆናቸው ስህተት ሊከሰት ይችላል። በሌላም በኩል በክፍል ውስጥ ካለው የትምህርት አውዱ ውጭ ባጋጣሚ በሚከሰት አዝማሚያ ከትምህርቱ አውድ ጋር ያልተያያዘና ተገቢ ያልሆነ የቋንቋ ኢንፎርሜሽን እንዲሰጥ ያደርጋል። ይህም ለስህተት መከሰት ምክንያት ይሆናል።

-ሌላው በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የሚገባው የስህተት ምንጭ ከአእምሮአዊው የቋንቋ ስርአት /ታህታይ መዋቅር/ የሚመነጭ ሳይሆን በይበልጥ በላዕላይ መዋቅር ተጽዕኖ አማካኝነት ሊፈጽሟቸው የሚችሏቸው ስህተቶች መኖራቸው ነው። እንደነዚህ ያሉት ለስህተት መፈጠር ምክንያት የሆኑ ሁለት የስህተት ምንጮችም፡- 1) ቀጥተኛ የተግባብኦት ስትራቴጅና 2) የቋንቋ ብቃት ምክንያቶች ናቸው። ተማሪዎቹ የተግባብኦት ሂደት በሚፈጽሙበት ጊዜ አስፈላጊውን ፍች ለማግኘት ሲፈልጉ ከዚያ ጋር ለሁኔታው የሚስማማ ቃል በመፍጠር በወቅቱ ለተከሰተው ችግር መፍትሄ ይፈልጉለታል። በዚህም ሁኔታ ስህተት ሊፈጠር ዋችላል። /ሊትልውድ 1986:30-1፥ ብራውን 1994:217/። ሆኖም ከተለመደው ስርአት የማፈንገጡ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ፍንገጣው የተግባብኦት ስልት ይሁን የቋንቋ ህግ ውጤት ለመወሰን ዘወትር አስቸጋሪ ነው።

2.2.4. <u>ስነልቡናዊ ሁኔታዎች</u> <u>/Psycological Events/</u>

ኖሪሽ /1990፡19/ እንደሚሉት ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ ተማሪዎቹ ስህተቶቹን እንዲፈጽሙ የሚያደርጓቸው ስነልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ነው። ስነልቡናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን ይህም ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአእምሮአቸው ውስጥ ይዘውት የመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጓቸው ነው። የዚህ አይነቶቹ ስህተቶቹም በኮርደር "ያላስፈላጊ ድግግሞሽ" ተብለው መጠራታቸውን ኖሪሽ /1990/ የገለጹት ሲሆን እነዚህ ስህተቶችም ከቋንቋ መማር ጠቃሚ ክፍሎች ከሚቆጠሩት ስህተቶች የተለዩ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ስለስህተት ምንጮች በሚጠየቁበት ጊዜ የሚሰጧቸው መልሶች ተቀራራቢነት ያላቸው ቢሆኑም አንዳንዶቹ ከተማሪዎቹ ግዴለሽነት የሚመጣ ነው ማለታቸውንም ኖሪሽ ገልጸውታል። ሆኖም እንደኖሪሽ አባባል ግዴለሽነት ብቻውን ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን አይችልም። ይሁን እንጂ መምህራን ተማሪዎቻቸው ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። ግዴለሽነት ለመማር ካለፍላጎት መቀስቀስ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ይህም የፍላጎት ማጣት ምናልባትም የትምህርቱ አቀራረብ ወይም ደግሞ ለትምህርቱ የቀረበው ነገር ከተማሪው ጋር ባለመስማማቱ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በግዴለሽነት የሚፈጸመውን ስህተት ለመቀነስ ከሚያስችለውም መንገድ አንዱ የእርስ በእርስ እርማት ማካሄድ እንደሆነና የዚህ አይነቱ የአስተራረም መንገድም ስህተቶችን የመመርመር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚሆን ኖሪሽ ገልጸውታል።

የስህተት ምንጮችን በተመለከተ ከላይ ከፍ ብሎ በዝርዝር የተቀመጠ ቢሆንም ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ስህተቶች፡-

1) ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፡-
2) ከታላሚው ቋንቋ ሽግግር /ስህተቱ ብያኔ፡ የትምህርቱ አውድና በላዕላይ መዋቅር አማካኝነት የሚፈጸሙት ስህተቶች/፡
3) ከመማር ሂደቱ /ለትምህርት ከሚቀርቡት ማቴሪያሎች ምርጫ፡

   ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፥ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡት ምሳሌዎች፥ በምሳሌዎች አማካኝነት ከሚደረጉት ልምምዶች፡ ከልምምዱ ውጤቶችና ከደካማ የማስተማር ዘዴ፥ ከመርሃ ትምህርቱ አቀራረብ/ና
4) ከስነልቡናዊ ምክንያቶች የተነሳ ሊመነጩ ይችላሉ።

በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት የድርሰት ትምህርትን ችግር ለመመልከትና ለመመርመር፥ የስህተቶቹን ምንጭ ለመረዳትና ብሎም ስህተቶቹ እየቀነሱ የሚሄዱበትን ሁኔታ ለመጠቆም የተለያዩ ምሁራን ከተጠቀሙባቸው የጥናት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ "የስህተት ትንተና" / Error Analysis / ጥናት ነው። በመሆኑም

"የስህተት ትንተና" ማለት ምን እንደሆነና የሚሰጠውም ጠቀሜታ ምን እንደሚመስል ለማስገንዘብ በተከታዩ ክፍል እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል።

## 2.3. የስህተት ትንተና ዘዴ /Error Analysis/

### 2.3.1. የስህተት ትንተና ምንነት

የስህተት ትንተና በፍሪስ /1945/ ጀምሮ በላዶ /1957/ እየተስፋፋና እውቅናን እያገኘ በመሄድ እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ድረስ በተለያዩ የዶክትሬት ዲግሪ ሚሚያ ጥናቶችና ሌሎችም ጥናቶች ሲሰራበት የቆየውን ንጽጽራዊ ትንተና በመተካት የመጣ ነው። /ስፖልስኪ፡1979፡ 250-255/

ይህ በኮርደር /1967/ የተጀመረው የስህተት ትንተና በቋንቋ ትምህርት አካባቢ ምርምር ለማካሄድ ለሚፈልጉ ሰዎች ጠቀሜታ እንዳለው ክንውን የሚቆጠር ሲሆን፣ ተግባራዊ መሆን በጀመረበት በዚሁ ጊዜም በቋንቋው ትምህርት ስነዘዴና በአላማው ላይ ግልጽ የሆነ ለውጥን አስከትሏል። በዚሁ ወቅት በርካታ የስነልሳን ስራዎች የተከናወኑበት፣ ትራንስፎርሜሽናል ሰዋሰው ቀደምቱን የንጽጽራዊ ትንተና እየጣለ ሁለንተናዊ የሆነውን የቋንቋ ባህርይ እየገለጸ የመጣበትና በህጻናት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳና በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ጥናት ምክንያት በስነዘዴው ላይ አዲስ ችግር የተፈጠረበት ነው።

በንጽጽራዊ ትንተና መስክ ተሰልፈው የነበሩት ምሁራን ራሳቸውን እንደተግባራዊ ስነልሳናውያን አድርገው ይቆጥሩ የነበሩ በመሆናቸው ግምታቸውም ንጽጽራዊ ስነልሳን ብቃት ያላቸውን የትምህርት መሳሪያዎች ለማዘጋጀት ያስችላል የሚል ነበር። ቤሪ /1968/ የንጽጽራዊ ትንተናን ኢ-ብቃት እስካመለከቱበት ጊዜ ድረስም በስህተት አካባቢ ለሚፈጠሩ ችግሮች መጠነኛ ማረጋገጫዎችን ያቀርብ የነበረና ለሰዋሰው ትምህርት ጠቃሚ መሰረት በማቅረብ በኩልም ጠቀሜታ የሚሰጥ የነበረ ቢሆንም ለቋንቋ ትምህርት ንደፊ ሃሳብ የጣለው መሰረትና ያመቻቸው ጥሩ ሁኔታ ግን ይህ ነው ተብሎ በስፋት አልተጠቀሰም። /ስፖልስኪ፣ 1979፡ 250-255/። እንደስፖልስኪ እምነት በጣም ጥሩ የሆነ አጠቃላይ የስህተት ትንተና ቅኝት የቀረበው

በሹማንና ስቴንሰን /1974/ በተሰበሰቡ ስራዎች ላይ የተገለጸው ሲሆን፥ ይህም የንጽጽራዊ ትንተና ንደፈ ሃሳብ የወደቀበትና አዲሱ የስራ መስክ ማለትም የስህተት ትንተና ሊኖረው የሚችለው ተግባሪዊና ንድፈሃሳባዊ ጠቀሜታ ምን እንደሚመስል የተገለጸበት ነው። የስህተት ትንተናም የሁለተኛ ቋንቋን የመማር ንድፈሃሳብ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ስራ ጋር በማገናኘት ስርአታዊ ስህተቶች የሚባሉት በመማር ሂደቱ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ማረጋገጫ የሚሰጥና የሚያመለክት ነው።

ብራውን /1994:206/ እንደሚሉት የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፥ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበትና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ የምድብ አይነቶች ተከፋፍለው የሚቀመጡበት ዘዴ ነው። የስህተት ትንተና በአፍ መፍቻ ቋንቋ አሉታዊ ሽግግር ብቻ ሳይሆን ሊሆኑ ከሚገባቸው የስህተት ምንጮች አንጻር ስህተቶችን የሚመረምር በመሆኑ ከንጽጽራዊ የስህተት ትንተና የተለየ ነው።

በርካታ የዘመኑ የስህተት ትንተና ተንታኞች እንደሚያምኑት የታላሚውን ቋንቋ ችግር በመግለጽ በኩል ሲታይ ንጽጽራዊ ትንተና ብቃት የሌለው ነው። በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት የሚያጋጥመውን ችግር ለማጥናት የስህተት ትንተናን የሚያቀርቡ ሰዎች እንዳመለከቱት የስነልሳን ሰዎችና መምህራን በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳው ሂደት ይበልጥ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ተማሪዎቹ ወደፊት ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ በመተንበይ እንጂ ተማሪዎቹ በሰሩት ስራ ላይ መሆን የለበትም። /ስታችህተር፥ 1974:205-6/። ምንም እንኳን የስህተቶች ትንተና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አስፈላጊ ቢሆንም በአተናተን ላይ የሚታዩ ችግሮች አሉ።

### 2.3.2. <u>የስህተት አተናተን ችግሮች</u>

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳና በስህተት ትንተና መስክ አወዛጋቢ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም አወዛጋቢ ጉዳዮች በተለያዩ አመለካከታዊ ግጭቶች የተነሳ ተቃራኒ

ውጤቶችን ያስከትላሉ። እነዚህም ተቃራኒ ውጤቶች ከማስተማሩ አይነት፥ ከተማሪው ዕድሜ፥አመለካከቱ፥ ተማሪው ለትምህርቱ ካለው መቀስቀስ፥ የታላሚው ቋንቋና የአፍ መፍቻ ቋንቋው የዝምድና ደረጃ፥ የአገላለጽ መንገድ... ባላቸው የተለያዩ የርቀት አይነት የተነሳ ሊከሰቱ ይችላሉ። የነዚህም መከሰት የስህተቶቹን ውስብስብነት ሊያመጣ ይችላል። በጥቅሉም በቋንቋው መማር ሂደት ውስጥ የሚታቀፍ ስነልቡናዊና አእምሮታዊ ሂደቶች የስህተቶችን ውስብስብነት ሊያስከትሉ ይችላሉ። /ሉት፡ 1983፡256/

እንደሉት አባባል የስህተት ትንተና ፕሮጀክት ተቃራኒ ውጤቶችን የሚያመለክተው በብያኔዎች የተነሳ ነው። ይህን ያሉበት ምክንያትም በአንድ ወቅት ዱሌይና በርት /1976/ እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚያጠኑ የእስፓኒሽኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች የተፈጸሙ 513 ስህተቶችን በመረመሩበት ጊዜ ከ 5%የሚያንሰው ስህተት በጣልቃገብነት በተፈጸሙ ስህተቶች ምድብ ውስጥ ተካቶ በመገኘቱ ነው። በሌላ ወቅት ደግሞ የጥቂት ንጽጽራዊ ስነልሳን ተመራማሪዎችን ውጤት ኒኬል /1981/ በተመለከቱበት ጊዜ 80% ያህሉ በጣልቃገብነት በተፈጸሙ ስህተቶች ምድብ ውስጥ በመገኘታቸውና ሌሎችና መሰሎቻቸው ምርምር ባደረጉበት ጊዜ ደግሞ በግምት 50% የሚሆነው ስህተት በጣልቃገብነት የተከሰተ በመሆኑ ነው። ከነዚህ ችግሮች በመነሳትም ሉት አስተያየት ሲሰጡ አንድ የሁለተኛ ቋንቋ መምህር የተማሪዎቹን ስህተቶች ለመተንተን በሚሞክርበት ጊዜ 1) በተለያዩ የስህተት አይነቶች 2) አወዛጋቢ በሆነ የቁልፍ ቃላት ግላጼ 3) በስህተት ትንተና ዘዴ የተሰሩ ስራዎች በያዙት የተቃራኒ ሃሳብ ውጤቶች የተነሳ ችግር ይፈጠርበታል። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች አስቀድሞ ማወቁ ተገቢ ይሆናሉ ይላሉ። /ሉት 1983፡257/

በተመሳሳይ ሁኔታም ኖሪሽ /1990፡91-2/ እንደሚሉት የስህተት ትንተና በሚደረግበት ጊዜ ችግር ያለ ሲሆን ችግሩም ሊመጣ የሚችለው በአንድ ዘመን አንድ ሰው ወይም መምህሩ ስህተት ነው ብሎ የገመተው ነገር በሌላው ጊዜ ደግሞ እንደትክክል ሆኖ በመቆጠር ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ነው። ቋንቋ በየጊዜው እየተለዋወጠና እያደገ በመሄዱ ለዛሬ በስህተትነቱ የተቀበልነው ነገር ለነገ ደግሞ

ተቀባይነት ያለው ይሆናል፡፡ በዚህም የተነሳ በአተናተን ላይ ችግር ያመጣል፡፡ በስህተት ትንተና ላይ ከዚህ የበለጠ ችግር ቢኖርም ችግሩ የግድ ከመምህሩ አተያይ ጋር መዛመድ አይኖርበትም፡፡ ምክንያቱም ችግሩ ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው በስህተቶች ላይ ከሚታየው አተረጓጎም አንጻር ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪው " choose " የሚለውን ለመጻፍ " chose " ብሎ ቢጽፈው መምህሩ ይህን ስህተት የሚመድበው እንዴት ነው? እንደ አጻጻፍ ስህተት ይቆጥረዋል? ምናልባትም "lose" ከሚለው ጋር በማመሳሰል? ወይስ ትክክል ያልሆነ ድርጊት በሚለው? አጠያያቂው ጉዳይ እዚህ ላይ ነው በማለት ኖሪሽ የስህተት አተናተንን ችግር ይገልጻሉ፡፡

ምንም እንኳን ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የስህተት ትንተና በሚካሄድበት ጊዜ አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮች ቢኖሩም ለሁለተኛ ቋንቋ ለመደ ጠቀሜታ ያለው መሰረታዊ ጥናት የሚያቀርብና ለወደፊቱ በጥናት መስኩ ለሚሰማሩ ወጣቶች ጥሩ መንገድ የሚከፍት እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ገልጸውታል፡፡ /ስፖልስኪ፥ 1979፡255/፡፡ ስለሆነም ጠቀሜታውን በተመለከተም በተከታዩ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 2.3.3. <u>የስህተት ትንተና ጠቀሜታዎች</u>

ሎት/ 1983፡256/ የስህተት ትንተና ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን ስህተቶች እንዴት መተንተን እንደሚችሉ ቴክኒኮችን በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ ያለው ስራ እንደሆነ ይገልጹታል፡፡ በተጨማሪም ሎት ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የሚፈጽሙ ስህተቶችን በስህተት ትንተና ዘዴ በመመርመር ለመምህራን የሚያስገኘው ጠቀሜታ ተማሪዎቻቸው ለምን ስህተት እንደፈጸሙ ለማሳወቅና ተገቢ የሆነ አፋጣኝ ትምህርት እንዲያቀዱ ለማድረግ ይረዳል ይላሉ፡፡ መምህራን በስህተት ትንተና ዘዴ ተጠቅመው ተማሪዎቻቸው የፈጸሟቸውን ስህተቶችና ተደጋጋሚ የሆኑ የስህተት አይነቶችን በመሳል እነዚህ ስህተቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በማስተማር ቴክኒክ ስህተት ወይም በታላሚው ቋንቋ የተፈጠሩ ስህተቶች ይሁኑ አለዚያም በተማሪው በራሱ የተፈጠሩ ስህተቶች በመለየት በክፍል ውስጥ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመርዳት አመች ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡

በኖሪሽ /1990፡80/ አስተሳሰብ የስህተት ትንተና ተማሪዎች ጽሁፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ያለባቸውን ችግር ያሳያል፥ በክፍል ውስጥ ወይም በሃገር ደረጃ የተለያዩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጻሪ ያላቸውን ተማሪዎች የጋራ ችግርና እንዲሁም ለተወሰነ ቡድን ያለውን የተለየ ችግር ይጠቁማል፥ መምህሩ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት በሚያደርገው የሁለትና ሶስት ጊዜ ቅኝት የሚያገኘው ውጤት የእያንዳንዱ ተማሪ ችግር ግላዊ ባህርይና የሚያስተምረው ትምህርት ወይም ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ያሳየው መሻሻል እምን ድረስ እንደሆነ እንዲያይና የስህተት ትንተናን እንደመቆጣጠሪያ መሳሪያ በመጠቀም መምህሩ የእሱ የማስተማር ዘዴ እንዴት እንደሆነ እንዲፈትሽበት ያስችለዋል።

በዚህም የተነሳ የስህተት ትንተና ዘዴን መሰረት ያደረጉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተለያዩ ጉዳዮችን የሚመረመሩ የጥናት ስራዎች ከጊዜ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረና የበርካታ ምሁራንንም ትኩረት እየሳበ መጥቷል። በተለይም በትምህርት መስክ በመማርና ማስተማር ሂደት የስህተት ትንተና ጠቀሜታ እንዳለው ከተለያዩ ስራዎች ለመገንዘብ ተችሏል።

ስለሆነም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶችን በስህተት ትንተና ዘዴ ካጠኑት በርካታ የውጭ ምሁራን መካከል ጥቂቶቹን ለማቅረብ ተሞክሯል።

2.3.4. <u>በስህተት ትንተና ዘዴ የተጠኑ ጥናቶች</u>

ስኮትና ቱከር /1974፥69-71/ ቤይሩት በሚገኝ የአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በሚማሩ 22 የአረብ ተማሪዎች ላይ የእንግሊዝኛ የቋንቋ ብቃት ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት በስህተት ትንተና ዘዴ ጥናት ያደረጉ ሲሆን፡ በጥናቱ ሂደትም የሴሚስተሩ ትምህርት ከመጀመሩ በፊትና ከተጠናቀቀ በኋላ በቅድመ ሙከራና ድህረ ሙከራ አማካኝነት የጽሁፍና የቃል ናሙናዎችን በመውሰድ የተፈጸሙት ስህተቶች ከቋንቋ ብቃት ስህተቶች፥ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃገብነት፥ ወይም ደግሞ ከውሸት የውስጠ ቋንቋ ማመሳሰል አንጻር ተተንትነዋል። የመረጃዎቹ ውጤቶችም የስህተት አይነቶቹን፥ ድግግሞሻቸውንና የስህተት ምንጮችን ለመለየት

ከማስቻላቸውም በላይ የአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ለሆኑ ተማሪዎች ለሚያስተምሩ መምህራንና በጥቅሉም የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ስህተትን ለሚመራመሩ ተመራማሪዎች ጠቀሜታ የሚሰጡ እንደሆኑ ገልጸዋል።

ሪቻርድ /1970/ የተለያየ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዳራ ያላቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ድርሰት በስህተት ትንተና ዘዴ አጥንተው ካገኙት መረጃ በመነሳት ሁለተኛ ቋንቋን በመልመድ ሂደት የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመለየትና የስህተቶቹንም ምንጭ ለመጠቆም እንዲሚያስችል ገልጸዋል።

ኤፍስታትሂድ /1972፡159-167/ የእንግሊዝኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የግሪክ ተማሪዎች ነጻ ድርሰት ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶቹን በስህተት ትንተና ዘዴ ካጠኑ በኋላ ከጥናቱ የተገኘውን ውጤት ሲያመለክቱ በተጠኑት ናሙናዎች ውስጥ የቃላት ስህተቶችና መዋቅራዊ ስህተቶች ሊከሰቱ እንደቻሉና ከነዚህም ስህተቶች መካከል መዋቅራዊ ስህተቶች በውስጣቸው የተግባር ቃላትና የይዘት ቃላት አጠቃቀም ስህተቶችን እንዳቀፉ ጠቅሰው የስህተት ምንጮቹም የአፍ መፍቻ ቋንቋ፥ የባህል ጣልቃገብነት፥ ከታላሚው ቋንቋ ጋር የተሳሳተ ማመሳሰል (ዝምድና)ና ድክመት ያለው የማስተማር ዘዴ ሊሆኑ እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በሃትያ /1974/ የተማሪዎችን ድርሰት በስህተት ትንተና ዘዴ መርምረው ካጠኑ በኋላ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ላይ ችግር የሚፈጥሩ ነገሮችን፥ በጽህፈት ውስጥ የተስተካከሉ ዐ.ነገሮችን ለመጻፍ የማያስችሉና ሃሳብ ትክክል እንዳይተላለፍ የሚያደርጉ ነገሮችን ለመለየት ያስችላል ብለዋል።

ኖሪሽ /1990፡80/ በስህተት ትንተና ዘዴ የተከናወኑ ጥናቶችን ገምግመው ካገኙት ውጤት በመነሳት የስህተት ትንተና ዘዴ ያለውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል።

1. አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመምህሩ ያስጨብጣል፥

2. የተለያዩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዳራ ያላቸው ተማሪዎች በሚገኙበት ክፍል ውስጥ የሚካሄድ የስህተት ትንተና ጥናት ቋንቋን በመማር ሂደት ለሁሉም ተማሪዎች የጋራ የመማር ችግሮቹን፥ ለአንድ ለተወሰነ ቡድን ደግሞ ብቸኛ ችግሮቻቸውን ለመረዳት የሚያስችል መረጃ ይሰጣል፥

3. በክፍል ውስጥ ከተደረገ የስህተት ትንተና ጥናት የሚገኝ መረጃ የማስተማር ዘዴን መገምገሚያሆኖ ያገለግላል።

ኮክስ /1996፡173/ በአንድ ክፍል ውስጥ ስለኢኮኖሚ የሚያጠኑ ሁለት ቋንቋዎችን እኩል በሚናገሩ የፍራንሲስኮስ ተማሪዎችና ሌሎችም ተማሪዎች ጽህፈት ለማረምና ለመቆጣጠር ታስቦ ለሶስት ተከታታይ የትምህርት አመታት በስህተት ትንተና ዘዴ ጥናት እንደተካሄደ አውስተው፡ የጥናቱ አላማም፡ 1)የፍራንኮፎንና የአንግሎፎንስ ተማሪዎች ተመሳሳይ ወይም የተለያየ ስህተት መፈጸማቸውንና 2) ሁለቱ ቡድኖች አንዱ ወይም ሌላው ያለምንም ቅደመ ዝግጅት በአንድ ላይ የተማሩ መሆናቸውን ለመወሰን እንደነበር ሲገልጹ፥ የስህተት ትንተናው ውጤትም ሁለቱ ቡድኖች ተመሳሳይ ስህተቶችን ሊፈጽሙ በመቻላቸው ሁለቱን ቡድኖች አንድ ላይ አድርጎ ማስተማሩ የሚያስከትለው ዋና ችግር አለመኖሩን የሚጠቁም ነው በማለት የስህተት ትንተና የተማሪዎችን ችግር ለመመርመር ያለውን ጠቀሜታ ገልጸዋል።

ቱሼ /1996፡255/ በስህተት ትንተና የተሰሩ ስራዎችን አንስተው እንደገለጹት እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የአረብ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የስነልሳን ችግሮች ለመመርመር በተካሄደ ጥናት የቀረበው ጽሁፍ የስህተት ትንተናን ጠቀሜታ፣ የስህተት አይነቶችንና ድግግሞሻቸውን እንዲሁም የስህተት ምንጮችን በሚገባ ገልጿል። የወረቀቱ አብዛኛው ክፍልም የአረብኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ወይም በውጭ ቋንቋነት ሲማሩ የሚያጋጥማቸውንም ችግር ይዟል። ተማሪዎቹ እንግሊዝኛን በሚማሩበት ጊዜ በአጻጻፍ፡ አነባበብና ሰዋስዋዊ ገጽታዎች ከአረብኛው ወደ እንግሊዝኛው በጣልቃገብነት የገቡትን ስህተቶችም የያዘ ከመሆኑም በላይ ስለስህተት ትንተናም ጥቂት ስነትምህርታዊ ጉዳዮችን አቅርቧል።

ወደሀገራችን ስንመጣም በጽህፈት ስራ ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ጥናቶች በተለያዩ ምሁራን አማካኝነት የተከናወኑ ሲሆኑ ከነዚህም ምሁራን መካከል ይልማ (1956)፥ ነጋሳ (1965)፥ ክፍሌ (1986) ና አለማየሁ (1986) ይገኙበታል።

ይልማ /1956፡3-5/ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ የ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ጽህፈት ላይ በሚታዩ ስህተቶች ጥናት ባደረጉበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሳልስና የሳድስ፡የግእዝና የሀምስን ቦታ ማለዋወጥ፥ የመስተዋድዶችንና የተሳቢ ምልክቶችን አገባባቸውን አለማወቅ፡ የባለቤትና ግሶች አለመስማማት ስህተቶች እንደሆኑና የስህተቶቹ ምንጭም የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደሆነ ጠቅሰው ከነዚያ ውጭ የሚፈጸሙ ሌሎች የስህተት ዓይነቶች ግን በራሱ በቋንቋው ውስጣዊ ባህርይ ምክንያት ሊመጡ እንደሚችሉ ገልጸዋል።

ነጋሳ /1965/ በ1962 ዓ.ም. የተሰጠውን የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ የድርሰት ፈተና መርምረው በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የታዩትን ስህተቶች ሲተነትኑ አብዛኞቹ ስህተቶችም የተፈጸሙት ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት በማያውቁት ተማሪዎች እንደሆነና ለብዙዎቹ ስህተቶች መከሰትም ምክንያት የሆነው አፍ የፈቱበት ቋንቋ እንደሆነ ገልጸዋል።

ክፍሌ /1986/ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ እንዴት እንደሆነ ለማወቅ በአዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ ት/ቤቶች በናሙናነት በተመረጡ 360 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጥናት ባደረጉበት ጊዜ ተማሪዎቹ ከሞሏቸው የጽሁፍ መጠይቆች መልሶችና ከተሰጠው የችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኘው ውጤት ተጠኝ ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው የሚያመለክት ሲሆን ችግሩ በትክክል ቃላት የመምረጥ፣ ሰዋሰዋዊ አገባብን የመጠበቅ፣ በስርአተ ነጥቦች በአግባቡ ያለመጠቀም፣ የሀ.ነገርን ትክክለኛ አስካክ ጠብቆ ያለመጻፍ ሲሆን ሀሳብንም አቀናብሮ በመግለጽ በኩል አነስተኛ ችሎታ እንዳላቸውና አንቀጽ በመጻፍም ያላቸው ልምድ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ያመለክታሉ።

ክፍሌ ለእንደነዚህ አይነቶቹ ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ብለው የገለጿቸውም የመማሪያ መጻህፍት አቀራረብና የትምህርት አሰጣጡን ነው።

በጽህፈት ልምምድ ላይ የሚታየውን ችግር አስመልክቶ እነዚህ ከላይ ከፍ ብሎ ስማቸው የተጠቀሱት ምሁራንና ሌሎችም በተዘዋዋሪ መንገድ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ቢሆንም በስህተት ትንተና ዘዴ ተጠቅመው በአማርኛ ጽህፈት ላይ የሚፈጸሙ የስህተት አይነቶችን፥ ድግግሞሻቸውንና የስህተት ምንጮችን ለመለየት የቻሉት አለማየሁ /1986/ ናቸው።

አለማየሁ በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ የተለያየ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዳራ ያላቸው /ማለትም 356 በአማርኛ፡ 34 በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በድምሩ/ 390 ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በሀ.ነገር ላይ የሚፈጸሙ ስህተቶችን በስህተት ትንተና ዘዴ ተጠቅመው በማጥናት የተፈጸሙት ዋና ዋና ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም፥ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ በአይነት ለመፈረጅ ያልተቻሉና የጽንሰሃሳብ ስህተቶች እንደሆኑና ለነዚህም ስህተቶች መከሰት ምክንያት የሆኑት የስህተት ምንጮች የጽሁፍ ቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ደንብን አለማወቅ፥ ጽህፈትን አለመለማመድ፣ አሉታዊ የመማርና የማስተማር ዝንባሌና የተሳሳተ የጽንስ ሀሳብ ግንዛቤዎች እንደሆኑ ገልጸዋል።

በጥቅሉ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚሉት የስህተት ትንተና ለስነልሳን ሰዎችና መምህራን፥ ተማሪዎች ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ፡ ለየትኛው በቂ ትኩረት እንደሚሰጡና እንደማይሰጡ የሚያመለክት ነው። እነዚህ በትምህርት መስኩ የተሰለፉ ተመራማሪዎች እንደሚጠቁሙትም አብዛኞቹ የቋንቋ ለመዳ ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ውጤቶች ብቻ ሳይሆኑ ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ በሚለምድበት ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርገው ስልትና ከታላሚው ቋንቋ የጋራ ጣልቃገብነት ሊመነጩ የሚችሉ ሲሆን በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ጥናት ውስጥም የስህተት ትንተና ጠቃሚ መሳሪያ ነው። /ስታቸህተር፥ 1974፡ 206/

አንድን ጥናት በስህተት ትንተና የአተናተን ስልት ለማቅረብ እንዲቻል የአተናተን ጥበባቱን ማወቅ የግድ ይሆናል። በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ የስህተት ትንተና ጥበቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል።

2.3.5. <u>የስህተት ትንተና ጥበቦች</u> <u>/Techniquies of Error Analysis/</u>

የቋንቋ ስርአቶች ዘወትር በሂደትና በለውጥ ላይ ያሉ በመሆናቸውና በዚህም የተነሳ አዳዲስ ነገሮች እየተጨመሩ የሚሄዱ ስለሆነ የቋንቋ መዋቅር በየጊዜው እንዲታይ ምክንያት ሆኖታል። ይህም እንደገና የማየቱ ጉዳይ ቀደም ሲል ከተገኘው መረጃ በተቃራኒው ያለዚያም የተለየ፥ ያልታሰበና ያልተገመተ ነገር እንዲገለጽ ያስችላል። ስለዚህ በስህተት ትንተና ሂደት የመጀመሪያው እርምጃ ስህተቶችን መለየትና መግለጽ ይሆናል። ሆኖም ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች ተደራርበው የሚመጡ በመሆናቸው የስህተት አይነቶችን በቀላሉ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። ስለሆነም የተፈጸሙትን ስህተቶች ለመተንተንና አስተያየት ለመስጠት የሚቻለው ስህተቶቹ በተለያየ መንገድ ከተመረመሩና ከተለዩ በኋላ ነው። /ብሬውን፥ 1994፡ 207/

ይሁን እንጂ ከላይ በተገለጸው ችግር ምክንያት ወጥ የሆነ የስህተት ምደባ አከፋፈልና አተናተን ስልት ያለመኖሩ በጥናት መስኩ ምርምር ለሚያካሄዱ ተመራማሪዎች አስቸጋሪ ቢሆንም፥ በስህተት ትንተና ዘዴ የሰሩ አብዛኞቹ ተመራማሪዎች የተጠቀሙባቸው፥ ስህተቶችን በየዘርፉ ለመመደብና ለመተንተን የሚያስችሉ ሁለት ዋና ዋና የአተናተን ጥበቦችና እነዚህ የሚገኙባቸው ሶስት የአተናተን ስልቶች እንዳሉ ኖሪሽ /1990፡81-97/ ገልጸዋል።

እነዚህም ጥበቦች 1. ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ክፍፍል /ምደባና
2. ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል/ምደባ/
ናቸው።

ሀ. <u>ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ምደባ</u>

ይህ ምደባ ይበልጥ እየተለመደ የመጣ ሲሆን ስህተቶቹ አስቀድመው የተወሰኑ በመሆናቸው የሚፈለጉት በየምድቦቹ ለመሰግሰግ ነው፡፡ ስለሆነም ስህተቶቹ የሚዘረዘሩት ቀድመው በተወሰኑት የስህተት አይነቶች አንጻር ይሆናል፡፡ ይህ የስህተት አመዳደብ ዘዴ ስህተቶቹን ፈልጎ በየምድቦቹ ስር ለማመልከት በጣም ቀላልና ጊዜን የሚቆጥብ በመሆኑ ለአሰራር ቀላል ነው፡፡

ለ. <u>ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል/ምደባ/</u>

ይህ የስህተት አከፋፈል ወይም ምደባ ዘዴ በጽህፈት ላይ የተፈጸሙት ስህተቶች በራሳቸው የስህተቶቹን ምደባ እንዲወስኑ የሚፈቅድ ሲሆን በዚህ የስህተት ምደባና ትንተና ዘዴ የሚጠቀም ተመራማሪም የስህተቶቹን አይነቶች በካርድ ላይ በመዘርዘር ከተፈጸሙት ስህተቶች በመነሳት ስህተቶቹን በየፈርጁ ያስቀምጣል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው እነዚህ ዘዴዎች የሚገለጹባቸው ሶስት የተለያዩ ቴክኒኮች ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

1. ቅደመ ምርጫ የአከፋፈል ዘዴ
2. ስህተቶቹን መሰረት ያደረገ ክፍፍልና
3. ፈጣን የማረጋገጫ ዘዴ ናቸው፡፡

ኖሬሽ /1990/ እንደገለጹት ከሆነ የመጀመሪያው ምሳሌ ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ምደባ ሲሆን ሁለተኛውና ሦስተኛው ምሳሌዎች የተፈጸሙ ስህተቶችን መሰረት ያደረጉ ምደባዎች ናቸው፡፡

<u>ቅደመ ምርጫ የአከፋፈል ዘዴ፡-</u> ይህ ዘዴ የቋንቋውን ሳዕላይ መዋቅሮች መሰረት በማድረግ ስህተቶችን በአይነት ለመመደብ የሚያስችል ሲሆን ይህም ይፈጸማሉ ተብለው የሚገመቱትን የስህተት ዝርዝሮች አስቀድሞ በማስቀመጥ/ ለምሳሌ፡- የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ ስሙሙነት፣ ጾታ፣ ቁጥር፣ መደብ፣ ስርዓተ ነጥቦች፣ የሀ.ነገር

ቅደም ተከተል፣ የቃላት አጠቃቀም፣ መስተአምሮች፣ መስተዋድዶች.../ በጽህፈት ውስጥ የተገኙትን ስህተቶች በተዘረዘሩት ውስጥ እየወሰዱ የማስገባት ጉዳይ መሆኑን ኖሪሽ /ኤዘርተን 1975/ን በመጥቀስ ገልጸውታል /1990፡81/

<u>ስህተቶችን መሰረት ያደረገ ክፍፍል/ምደባ</u>/፡- ይህ በሀድሰን /1971/ ተግባራዊ የሆነው ምደባ የተመዘገቡ ስህተቶችን በተለያዩ የካርድ አይነቶች /ማለትም አንድ የስህተት አይነት በአንድ ካርድ ወይም አንድ ካርድ ለአንድ የስህተት አይነት /የመመዝገብ ሂደት ሲሆን እያንዳንዱ የስህተት አይነትም በተለያየ ካርድ ከተመዘገበ በኋላ ካርዶቹ በየምድቡ ተመድበው በአንድ ላይ በሳጥን ውስጥ የሚቀመጡበትና ቀስ በቀስም በትንሽ በትንሹ በየምድቡ የተቀመጡት ትናንሽ ስህተቶች አንድ ላይ በመሆን ወደ አጠቃላይ የስህተት ምድቦች የሚጠቃለሉበት ነው፡፡

ለምሳሌ ቃላዊ ክፍሎችና መዋቅራዊ ክፍሎች ቢኖሩ በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚነሱት መስተዋድድ፣ ስርአተ ነጥቦች፣ የአጻጻፍ ቅርጽ፣ ለመመደብ የማያስችል ወይም ከየትኛው ክፍል እንደሆነ ያልታወቀ... የሚባሉ ሲሆን የዚህ አይነቱ አቀራረብ ለጽህፈት የተመቻቸ ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜን ከመቆጠብ አንጻር ሲታይ ድክመት ይታይበታል፡፡

<u>ፈጣን የማረጋገጫ ዘዴ</u>፡- ይህ ቴክኒክ ለንግግር ወይም ለጽህፈት የሚያገለግል ሲሆን በዚህ ቴክኒክ የመጠቀሙ ዋና አላማም አሁን በቅርብ ያለው የማስተማር ቅርጽ ትክክል ይሁንም አይሁንም ለመገንዘብና ለማስታወስ የሚረዳ ነው፡፡ ይህም የማረጋገጫ ዝርዝር /Check List/ ትክክለኛውንና ያልሆነውን ቅርጽ መምህሩ እንዲያመጣጥንበት ሃሳብ ወይም ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ወጥ የሆነ የስህተት ምደባ አከፋፈልና አተናተን ስልት ባለመኖሩ አብዛኞቹ ምሁራን ወይም ተመራማሪዎች ከሰበሰቧቸው የስህተት አተናተን ዘዴ መረጃዎች አንጻር ከስራቸው ጋር አብሮ ይሄዳል ብለው የገመቱትን የአጠናን ዘዴና ስልት ይከተላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ኖሪሽ /1990፡81-97/

አብዛኞቹ የስህተት ተንታኞች የሚጠቀሙበትንና ስህተቶችን በየዘርፉ ለመመደብና ለመተንተን የሚያስችሉ ጥበቦችን ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ምደባና ስህተቶችን መሰረት ያደረገ የስህተት አከፋፈል ምደባ በማለት አስቀምጠዋቸዋል።

ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ በሥራ ላይ የዋለው ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ምደባ / Pre-Selected Category Approach/ የሚለው ነው።

በዚህ የትንተና ሞዴል ይፈጸማሉ ተብለው የተገመቱት የስህተት ዝርዝሮች አስቀድሞ ይቀመጣሉ። /ለምሳሌ የቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር፥ የስርአተነጥብ አጠቃቀም፥ የጽንሰሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶችና ሌሎችም/ . ከዚህ በኋላ በጽሁፉቱ ውስጥ የተገኙትን ስህተቶች በተዘረዘሩት የስህተት አይነት ምድቦች ውስጥ በመስግሰግ ስራው ይካሄዳል።

የዚህ ጥናት አላማ በስህተት ትንተና ዘዴ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስና ከጥናቱ ግብ ለመድረስ በክለሳ ድረሳኑ ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች፥ የተጠቆሙትን የጥናት ውጤቶች፥ የአተናተን ዘዴዎችና የአጠናን ስልቶችን በመነሻነት ይጠቀማል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

### 3.1. የት/ቤቶች የመምህራንና የተማሪዎች አመራረጥ

#### 3.1.1. የት/ቤቶች የናሙና አመራረጥ

ከላይ እንደተገለጸው ጥናቱ በሰሜን ኦሮሚያ ከሚገኙ ሰባት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል በሶስት ት/ቤቶች ላይ ያረፈ ሲሆን እነዚህም ት/ቤቶች 1. ሙከጡሪ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ፥ 2. ገብረጉራቻ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ፥ 3. ፍቼ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ሲሆኑ፥ ለጥናቱ ለመመረጥ የቻሉት የምቾት ናሙና /Convinience Sampling/ን በመጠቀም ነው። ምክንያቱም 1) ካለው የገንዘብ መጠን፡ የጊዜ ጉዳይና የቦታ ርቀት ጋር በማጣጣም፥ 2) ሦስቱ ናሙና ት/ቤቶች ካላቸው የቦታ ቅርበት አንጻር ጥናቱን በቅርብ ለመከታተልና 3) የሌላ የተለያየ የቋንቋ ተጽዕኖ የሌለባቸውን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ከሚያጠኑ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ ጥናቱን ለማሳረፍ ሲባል ነው።

#### 3.1.2. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚመለከታቸው ት/ቤቶች ከታወቁ በኋላ በጥናቱ ውስጥ የተዘጋጀውን መጠይቅ ለመሙላት የሚመለከታቸውን መምህራን ለማግኘት የተመረጠው የታመነ ሁነኛ ናሙና/Purposive Sampling/ ሲሆን በዚህም በመጠይቁ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን ለማግኘት ሲባል በሶስቱ ት/ቤቶች ውስጥ አማርኛን ከሚያስተምሩት መምህራን መካከል በ11ኛ ክፍል ገብተው የሚያስተምሩት መምህራን ሊመረጡ ችለዋል።

#### 3.1.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ ያረፈው በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በመጀመሪያ በእያንዳንዱ ት/ቤት በ11ኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች መካከል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ተለቀሙ። ቀጥሎም የተማሪዎች ቁጥር ከታወቀ በኋላ

ከተገኘው የተማሪዎች ቁጥር ላይ 50% በማውጣት የተጠኝ ተማሪዎች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ ታወቀ። ከዚያም ተጠኝ ተማሪዎችን ለማግኘት ሲባል በነሲብ ናሙና ስልት በመጠቀም ተማሪዎቹ ተለዩ። በመጨረሻም በሶስቱ ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ተጠኝ ተማሪዎች ትክክለኛ ቁጥር ታወቀ። በመሆኑም ጥናቱ ባረፈባቸው ት/ቤቶች ከተገኙት 480 የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተናጋሪ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 240 ተማሪዎች ለጥናቱ ሲቀርቡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 50% ያህሉን ሸፍኗል ማለት ነው።

## 3.2. <u>የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች</u>

ለዚህ ጥናት ይጠቅማሉ ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠይቅና ድርሰት ናቸው።

### 3.2.1. <u>መጠይቅ</u>

#### 3.2.1.1. <u>የተማሪዎች መጠይቅ</u>

የመጠይቁ አላማ በጥናቱ በሚደረስበት ውጤት ላይ አጠራጣሪ ሁኔታ እንዳይፈጠር በድርሰት መልመጃው ለሚገኘው ውጤት የድጋፍ ሀሳብ ለማግኘት ነው።

መጠይቁ ከተዘጋጀ በኋላ በሶስት ባለሙያዎች ተገምግሞ የተሰጡትን አስተያየቶች በመቀበል እንደገና ተዘጋጅቶ በሙከራ ጥናቱ በተሳተፉ 18 ተማሪዎች ተሞልቶ ተመልሷል። ተማሪዎቹ ከሰጧቸው መልሶችና አስተያየቶችም በመነሳት አሻሚና ግልጽ ያልሆኑ ናቸው ተብለው በባለሙያዎች የተገመቱት እንደገና ተሻሽለው ተዘጋጅቷል። የመጠይቁ ዝግጅት ከተጠናቀቀም በኋላም በተጠኝዎቹ ልክ ተባዝቶ ተጠኝ ተማሪዎቹ እንዲሞሉት ተደርጓል። ተማሪዎቹም መጠይቁን ከመሙላታቸውም በፊት ስለአሞላሉ በዚህ ጥናት አቅራቢ ገለጻ ተደርጎላቸዋል። ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለም እንዲጠይቁ እድል ተሰጥቷቸዋል። በዚህም መሰረት ግልጽ ያልሆነላቸውን የጠየቁ 4 ተማሪዎች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል።

መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያው ገጽ የመጠይቁ አላማ የተብራራበት ነው:: የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎቹን ዳራ ለማወቅ የተጠየቀበት ነው:: ሁለተኛው ክፍል ተማሪዎቹ ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አስተያየት በተለይም የጽህፈት ክሂሉን በተመለከተ ስለስህተት መፈጠር፣ የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች፣ የጽህፈት ልምምዱን ለማዳበር የትምህርቱ ሂደት ስለሚኖረው አዎንታዊና አሉታዊ ጠቀሜታ ለመረዳት የሚያስችሉ የምርጫ መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በዚሁ ክፍል በምርጫ መልሶቹ የቀረቡትን ሀሳቦች በድጋሚ ለማረጋገጥ በማሰብ 5 የስኬል ደረጃዎች /በጣም ከፍተኛ፥ ከፍተኛ፥ መካከለኛ፥ ዝቀተኛና በጣም ዝቀተኛ/ ያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል:: በክፍል ሶስት በጽህፈት ልምምዱ ወቅት ለተማሪው ችግር የሚፈጥሩትን ነገሮች፥ የሚያጋጥሙትን የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጭ ብሎ የሚያስባቸውን እንዲሁም ስለትምህርቱ አጠቃላይ አስተያየት እንዲሰጥበት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: (ስለመጠይቁ ዝርዝር አባሪ 1 ይመልከቱ)

3.2.1.2.<u>የመምህራን መጠይቅ</u>

የዚህ መጠይቅ አላማው ጽህፈትን በተመለከተ የተማሪዎቹን ዳራ ለማወቅ፣ የመርሀ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሀፍ የጽህፈት ክሂልን በማዳበር በኩል ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ጠቀሜታ በሚመለከትና መምህራን ስህተቶችን፥ የስህተት አይነቶችንና የስህተት ምንጮችን እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚመለከት ስለአላቸው አስተያየት መረጃ ለማሰባሰብ ነው::

መጠይቁ እንደተማሪዎቹ መጠይቅ በሙከራ ጥናቱ የተሞከረ ሲሆን ይህም በገምጋሚዎች አስተያየት ተሰጥቶበት ለዚሁ ጥናት ተሻሽሎ ቀርቧል::

ተጠቃሹ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጠይቁ የመጀመሪያው ገጽ የመጠይቁ አላማ የተብራራበት ነው:: ክፍል አንድ የመምህራንን አጠቃላይ መረጃ የሚመለከት ነው:: በክፍል ሁለት ስለመማር ማስተማሩ ሂደት፥ መርሀ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሀፍ አዘገጃጀት፥ ተማሪዎቹ ራሳቸው ስለጽህፈት ልምምዱ

የሚኖራቸውን አዎንታዊና አሉታዊ መልሶች የሚጠይቁ የምርጫ መልሶችን የያዙ ጥያቄዎች ሲኖሩ እነዚህንም በሌላ መንገድ ለማረጋገጥ አምስት የስኬል ደረጃዎች /በጣም ከፍተኛ÷ ከፍተኛ÷ መካከለኛ÷ ዝቀተኛና በጣም ዝቀተኛ/ ያሏቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ክፍል ሶስት ስለስህተት ምንነት፡ የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ነጻ አስተያየት የሚሰጥበት ነው፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 2 ከ ገጽ 127-136 ይመልከቱ)

3.2.2. <u>ድርሰቶች</u>

ለዚህ ጥናት በዋናነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ድርሰት ነው፡፡ ድርሰት ከመጻፍ በፊት በቅድሚያ ርዕሱ መዘጋጀት ያለበት በመሆኑ ከተማሪዎቹ ዕድሜ÷ ልምድ ፍላጎትና የክፍል ደረጃ ጋር በሚጣጣም መልኩ ርዕሶቹ ተዘጋጅተዋል፡፡ ርዕሶቹም በትምህርት መስኩ ባለሙያዎች ተገምግመው በሙከራ ጥናቱ ተግባራዊ ከሆኑ በኋላ እንደገና ታርመውና ተሻሽለው ቀርበዋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 3 ከገጽ 137-139 ይመልከቱ)

ድርሰቶቹ ነጻ የድርሰት አጻጻፍ / Free Writing / ስልትን በመከተል የተጻፉ ሲሆኑ በመጀመሪያው ዙር 240 ድርሰቶች፡ በሁለተኛው ዙር 200 ድርሰቶች በድምሩ 440 ድርሰቶች በክፍል ውስጥ ተጽፈዋል፡፡ ድርሰቶቹ በቤት ስራ እንዳይሰሩ የተደረገው ተማሪዎቹ ሌሎች ሰዎችን አሰርተው ይመጣሉ ከሚል ፍርሀት የተነሳ ነው፡፡

የድርሰት መልመጃው ወረቀት የድርሰቱን ርዕሶችና አስፈላጊውን መመሪያ የያዘ ሲሆን ተጠኝዎቹ ድርሰቶቹን ከመጻፋቸው በፊት ስለአሰራሩ በዚህ ጥናት አቅራቢ አማካይነት መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ግልጽ ያልሆነውንም እንዲጠይቁ ዕድል ተሰጥቷቸዋል፡፡ ግልጽ ያልሆነላቸውንም በመጠየቅ ተብራርቶላቸዋል፡፡

ድርሰቶቹ ለገምጋሚዎቹ (አራሚዎቹ) ሲሰጡ እያንዳንዱ በሶስት ቅጅ ተባዝቶ ነው፡፡ ድርሰቶቹ አማርኛ ቋንቋ በማስተማር የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያም በላይ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ሶስት መምህራን የታረሙ ሲሆኑ ለእያንዳንዱ ድርሰት

ውጤት የተሰጠው በሶስቱ አራሚዎች በግል የተሰጡት ነጥቦች ተደምረው ለ3 እንዲካፈሉ በማድረግ ነው፡፡

### 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በድርሰት መልመጃና በመጠይቅ አማካኝነት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቀሪው ስራ መረጃዎቹን መተንተን በመሆኑ ትንታኔው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 3.3.1. የድርሰት መልመጃዎች አተናተን

ኖሪሽ /1990፡81-97/ ስህተቶቹን በአይነት ለመከፋፈልና ለመተንተን 1) ቅደመ ግንዛቤን መሰረት ባደረገ ምደባ/ቀደም ሲል በተመረጡና በታወቁ የስህተት ምድቦች ስር መመደብ ና 2) ስህተቶቹን መሰረት ባደረገ የስህተት አከፋፈል ምደባ/በጽህፈት ላይ ከተፈጸሙት ስህተቶች/በመነሳት የስህተት ምድቦችን መመስረት እንደሚቻል ይገለጻሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት በተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ የተገኙት ስህተቶች በየስህተት አይነቶቹ የተከፋፈሉት ወይም በየምድቡ የተቀመጡት ቀደም ሲል በተመረጡ በታወቁ የስህተት አይነቶቹ ምድብ ስር ነው፡፡

በዚህም አይነት መንገድ ስህተቶች በአይነት ተለይተው እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ በየምድብ አይነታቸው ተቆጥረዋል፡፡ አቆጣጠሩም፡-

1. በየገጹ ቃላቱን መቁጠርና ድርሰቱ የተጻፈበትን የቃላት ብዛት ማወቅ፥
2. የተገኙትን የቃላት ብዛት ተጠኚ ተማሪዎቹ ለጻፏቸው የድርሰቶች ቁጥር ማካፈልና እያንዳንዱ ድርሰት የተጻፈበትን አማካይ የቃላት መጠን ማወቅ፥
3. በየገጹ ስህተቶቹን መቁጠርና አጠቃላይ የስህተቶቹን ብዛት ማወቅና
4. በአጠቃላይ የተገኙትን የስህተቶች አጠቃላይ ብዛት ለተጻፈው የድርሰት ብዛት በማካፈል አማካይ ስህተቱን ማግኘት ነው፡፡

ለምሳሌ፡ አማካይ ስህተት = $\frac{\text{አጠቃላይ የስህተት ቁጥር}}{\text{ተጠኝ ተማሪዎቹ የጻፉት አጠቃላይ ድርሰት ብዛት}}$

5. አማካይ የስህተት ድግግሞሹንም /በመቶኛ/ ለማወቅ ቀደም ሲል ተቆጥሮ የተገኘውን አጠቃላይ የስህተት ቁጥር አጠቃላይ ድርሰቱ ለተጻፈበት የቃላት መጠን ከተካፈለ በኋላ በአንድ መቶ ማባዛት ነው።

ኖሪሽ /1990:103-4/ የስህተት ድግግሞሽን(1) "ፍጹም" የሆነ ድግግሞሽ /ስህተቱ በተደጋጋሚ የሚታይ ስህተት/ና 2) በጽህፈት ውስጥ ከተገኙት የቃላት ብዛት አንጻር የሚታዩ የስህተቶች ብዛት በማለት ገልጸውታል። ለምሳሌ ተማሪው በ250 ቃላት ድርሰት ቢጽፍና 10 ስህተት ቢፈጽም የተፈጸሙት ስህተቶች በቀላሉ 10 እንደሆኑ ይመዘገባሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ተዛማጅ የሆነ ድግግሞሽ ሊሰላ ይችላል። ይህም የተገኘውን የስህተት አይነት ቁጥር/ ብዛት/ በአንድ መቶ በማባዛት እንደገና የተባዛውን ለአጠቃላይ የቃላት መጠን በማካፈል አማካዩ ይገኛል።

ለምሳሌ ድርሰቱ የተጻፈበት አጠቃላይ የቃላት ብዛት 44000 ቢሆንና የተጻፉት ድርሰቶች 440 ቢሆኑ አማካዩ የቃላት መጠን 100 ይሆናል። በዚህም አንድ ድርሰት የተጻፈበት የቃላት መጠን ይታወቃል።

የተቆጠረው አጠቃላይ የስህተት መጠን 9818 ነበር። በድርሰት አንድና ሁለት የተጻፉት ድርሰቶች ብዛት 440 ቢሆኑ በአንድ ድርሰት በአማካይ የተፈጸመው ስህተት የሚከተለውን ይመስላል። አማካይ ስህተት = 9818÷- 440 = 22.31 ይሆናል።

አማካይ የቃላት መጠን = 36135÷-440 = 82.13

አማካይ የስህተት ድግግሞሽ = $\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}}$ X100

$$ምሳሌ = \frac{22.31}{82.13} \times 100 = 27.17$$

በዚህ አይነት መንገድም የስህተት አይነቶቹ ድግግሞሽ ይገኛል። የዚህ አይነቱ መለኪያም በድርሰቱ የተገኙትን የስህተት አይነቶች ለማነጻጸር ይጠቅማል። ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ ስህተቶቹን በአይነት ለመመደብ ስህተቶቹንም ለመቁጠርና ድግግሞሻቸውንም ለማወቅ የዚህ ጥናት አቅራቢ ከላይ የቀረበውን የኖሪሽ /1990፡103-4/ የስህተት አተናተን ስልት ትጠቀማለች።

### 3.3.2. የስህተት ምንጭ መላምቶች ትንበያ

በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ ከተሰሩ ስራዎች ከተቃኙ ጥናቶች እንዲሁም ከመምህራንና ከተማሪዎች የመጠይቅ ምላሾች ከተገኙት ሀሳቦች በመነሳት የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ መላምቶች ተሰንዝረዋል። በነዚህ በተጠቀሱት መረጃዎች መሰረትም ዋና  የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ፥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፥ የመማር ማስተማር ሂደቱ፣ ስነልቡናዊ ሁኔታዎችና ሌሎችም ናቸው።

# ምዕራፍ አራት

## 4. የጥናቱ ውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት አላማ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ የስህተት ዓይነቶችን፣ ድግግሞሻቸውንና የስህተት ምንጮችን ማመልከት ሲሆን የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የታቀደ መሆኑ በምዕራፍ አንድ ላይ ተገልጿል፡፡

1. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው የስህተት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
   - የስህተቶቹ ብዛት ምን ያህል ነው?
   - ድግግሞሻቸውስ ምን ያህል ነው?
2. የስህተት ምንጮች ምን ምን ናቸው?

በዚህ ምዕራፍ ለጥናቱ በተመረጡ መሣሪያዎች አማካይነት የተገኙትን መረጃዎች በመተንተን ከላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞከራል፡፡ ለመረጃ አቀራረብና አተናተን ያመች ዘንድ ምዕ ራፉ በሁለት ተከፍሏል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎቹ በፃፉዋቸው ድርሰቶች ውስጥ የተፈፀሙትን ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና በነሱም ሥር ያሉ ንዑሳን የስህተት ዓይነቶች ብዛትና መቶኛ፣ አማካይ የስህተት መጠንና ድግግሞሻቸውን የተመለከተበት ነው፡፡

ሁለተኛው ክፍል ተጠኝ ተማሪዎች በፃፉዋቸው ድርሰቶች ለተፈፀሙት ስህተቶች የስህተት ምንጭ መላ ምቶች የተገለፁበት ነው፡፡

### 4.1 አጠቃላይ የስህተት ብዛትና የመልመጃ ዓይነት

ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ፅሁፍ የሚነሳው የስህተት ዓይነቶቹ ብዛትና ድግግሞሻቸው ሲሆን ከተገኘው መረጃም በመነሳት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡የመልመጃዎቹ ዓይነት፣ ድርሰቶቹ የተፃፉባቸው የቃላት ብዛት፣ የስህተት ብዛትና መቶኛ፣ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ

| የመልመጃው አይነት | የድርሰቱ ብዛት | ድርሰቱ የተፃፈበት የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት | | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ በ100 ቃላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ብዛት | መቶኛ | | |
| ድርሰት አንድ | 240 | 19081 | 79.50 | 7082 | 72.13 | 29.51 | 37.11 |
| ድርሰት ሁለት | 200 | 17054 | 85.27 | 2736 | 27.87 | 13.68 | 16.04 |
| ድርሰት አንድና ሁለት | 440 | 36135 | 82.13 | 9818 | 100 | 22.31 | 27.17 |

በሠንጠረዥ አንድ እንደተገለፀው የስህተት መረጃዎቹ የተቆጠሩት በድርሰት አንድና ሁለት መልመጃዎች በተፃፉት 440 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ ድርሰቶቹ የተፃፉት በ36135 ቃላት ሲሆን ከአንድ በላይ በሆኑ የስህተት ዓይነት ምድቦች የተቆጠሩ ስህተቶችም ብዛት 9818 ነው፡፡

ተማሪዎቹ ሁለት ድርሰቶች ለመፃፍ በአማካይ የተጠቀሙባቸው ቃላት መጠን 82.13 ሲሆን ይህም በሌላ አባባል አንድ ድርሰት በአማካይ በ82.13 ቃላት ተፅፏል ማለት ነው፡፡ ከ440 ድርሰቶች ውስጥ የተገኙት የስህተት መጠን 9818 ሲሆን በአንድ ድርሰት ውስጥ የተገኘው አማካይ ስህተትም 22.31 ነው፡፡ ስለሆነም ከ82.13 አማካይ ቃላት ውስጥ የተገኘው የስህተት ድግግሞሽ 27.17 መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ድርሰቶቹ በሁለት ጊዜ የተፃፉት በአንድ ጊዜ ሥራ ከመገምገም ይልቅ በሁለት ጊዜ ማየቱ የተሻለ ይሆናል በሚል ሲሆን በቤት ሥራ እንዳይሰሩ የተደረገውም ተማሪዎቹ ሌሎች ሰዎችን አሰርተው ይመጣሉ ከሚል ፍርሀት የተነሳ ነው፡፡

በሁለት ጊዜ የተፃፉ ቢሆኑም እንኳን ሁለቱን ድርሰቶች ለማነፃፀር ተብሎ የተዘጋጀ ባለመሆኑ ወደውስጥ በዝርዝር ለመግባት አልተሞከረም፡፡ ስለዚህ አጠቃላይ ስህተቶችን በተመለከተ የቀረበው መረጃ የሚያመለክተው ከላይ እንደተገለፀው በአጠቃላይ ድርሰቶችና ስህተቶች ላይ በመንተራስ ነው፡፡

### 4.1.1 ዋና ዋና የስህተት ዓይነት ምድቦች

ቀደም ሲል በክፍል ሦስት የድርሰት መልመጃ አተናተን ላይ እንደተገለፀው ስህተቶች በዓይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምደባ የስህተት ዓይነት ምድቦች መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የተተኮረባቸው የስህተት ዓይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው፡፡ ስለሆነም በነዚህ ዋና ዋና የስህተት ዓይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠረ የስህተት ብዛት መቶኛ አማካይ የስህተት መጠን እንዲሁም በመቶ ቃላት ውስጥ የተፈፀመዉ አማካይ ድግግሞሽ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡<u>በዋና የስህተት ዓይነት ምድቦች ውስጥ የተቆጠሩ ስህተቶች ብዛትና መቶኛ አማካይ ስህተትና ድግግሞሽ በመልመጃዎች ዓይነት</u>

| የስህተት ዓይነት ምድቦች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት | | አማካይ | አማካይ የስህተት | የስህተት | | አማካይ | አማካይ የስህተት | የስህተት | | አማካይ | አማካይ የስህተት |
| | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ |
| የቋንቋ አጠቃቀም | 3268 | 46.15 | 13.62 | 17.11 | 1220 | 44.59 | 6.1 | 7.15 | 4488 | 45.70 | 10.20 | 12.42 |
| የቋንቋ አወቃቃር | 1572 | 22.20 | 6.55 | 8.24 | 348 | 12.71 | 1.74 | 2.04 | 1920 | 19.56 | 4.36 | 5.31 |
| ስርአተ ነጥቦች | 1270 | 17.93 | 5.30 | 6.66 | 632 | 23.09 | 3.16 | 3.71 | 1902 | 19.37 | 4.32 | 5.26 |
| ጽንሰ ሃሳብ | 464 | 6.55 | 1.93 | 2.43 | 256 | 9.36 | 1.28 | 1.50 | 720 | 7.33 | 1.64 | 2.0 |
| መለየት ያልተቻሉ | 508 | 7.17 | 2.11 | 2.66 | 280 | 10.23 | 1.4 | 1.64 | 788 | 8.03 | 1.79 | 2.18 |
| ድምር | 7082 | 100 | 29.51 | 37.11 | 2736 | 100 | 13.68 | 16.04 | 9818 | 100 | 22.31 | 27.17 |

ከሠንጠረዥ 2 መረዳት እንደተቻለው የስህተት ዓይነት ምድቦቹ እንደየቅድም ተከተላቸው በደረጃ ሲቀመጡ፣

1. የቋንቋ አጠቃቀም
2. የቋንቋ አወቃቀር
3. ሥርዓተ ነጥቦች
4. መለየት ያልተቻሉና
5. የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተቶች ናቸው፡፡

በሁለቱም ድርሰቶች ከፍተኛ ስህተት የተቆጠረው በቋንቋ አጠቃቀም ነው፡፡ በሁሉም የስህተት ዓይነት ምድቦች ከተቆጠሩት 9818 ስህተቶች መካከል በቋንቋ አጠቃቀም በኩል የተፈፀመው የስህተት ብዛት 4488 ሲሆን

ይህም በመቶኛ ሲሰላ 45.71 ነው፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት አማካይ የስህተት መጠን 10.2 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 12.42 ሆኗል፡፡ ይህም በመቶ ቃላት ውስጥ የተገኘውን የስህተት ድግግሞሽ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በተገኙት መረጃዎች መሠረት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ተቀዳሚውን ስፍራ ይዟል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ የስህተት መጠን የተቆጠረው በቋንቋ አወቃቀር የስህተት ዓይነት ምድብ ሲሆን በሁለቱም ድርሰት መልመጃዎች ከተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 1920 ያህል ስህተት የተገኘበት ነው፡፡ ይህ የስህተት ዓይነት ምድብ በመቶኛ ሲሰላ 19.56 ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ 4.36 ነው፡፡ አማካይ ድግግሞሹ ደግሞ 5.31 ሊሆን ችሏል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የስህተት መጠን የተቆጠረው በስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 9818 ስህተቶች መካከል 1902 ያህሉ ስህተት የተቆጠረው በዚሁ ነው፡፡ የዚህ የስህተት ዓይነት መቶኛ 1937፣ አማካይ የስህተቱ መጠን 4.32፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 5.26 ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተቆጠረው የስህተት ዓይነት ምድብ መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ተብለው የተሰየሙ ስህተቶችን የሚያካትተው ሲሆን የስህተት ብዛቱ 788 ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 8.03 ሲሆን አማካይ የስህተቱ መጠን 1.79 እንዲሁም አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 2.18 ሊሆን ችሏል፡፡

በመጨረሻ ደረጃ የተገኘው የስህተት ምድብ በፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ላይ የታየው ሲሆን የስህተት ብዛቱም 720 ነው፤ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 7.33 ሲሆን አማካይ የስህተቱ መጠን 1.64 የስህተት ድግግሞሹ 2.0 ሊሆን ችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ የመጨረሻውን ደረጃ ሊይዝ ችሏል፡፡

ከሠንጠረዥ 1 እና 2 መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በመረጃ አንድ በተፃፉት ድርሰቶች በርካታ ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆኑ በመልመጃ ሁለት የተፃፉት ድርሰቶች ግን እንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ሲታዩ አነስተኛ ስህተቶች ሊቆጠሩ እንደቻሉ ነው፡፡ በሁለቱም ድርሰቶች ከተፈፀሙ 9818 ስህተቶች መካከል በድርሰት አንድ የተፈፀሙት የስህተቶች ብዛት 7082 ነው፡፡ ይህም

72.13 በመቶ ሲሆን አማካይ ስህተቱ 29.51፣ የስህተቱ ድግግሞሽ ደግሞ በመቶ ቃላት ውስጥ 37.11 ሊሆን ችሏል።

በሌላ በኩል በመልመጃ ሁለት የተፈፀሙት ስህተቶች ብዛት 2736 ሲሆን በመቶኛ 27.87 አማካይ ስህተቱ 13.68፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 16.04 ሊሆን ችሏል። በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሚፅፉበት ጊዜ ከድርሰት አንድ ይልቅ በድርሰት ሁለት ላይ አንፃራዊ የሆነ መሻሻል አሳይተዋል ሊባል ይቻላል። ሆኖም ይህንኑ እውነታ እስታትስቲካዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ ሳይንሳዊ በሆነ የልዩነት ብቃት ማረጋገጫ ዘዴ መጠቀም አስፈልጓል። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ "ቲ-ቴስት" (T-Test) ተግባራዊ ሆኗል።

በሁለቱ ድርሰቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለማረጋገጥ በተጠቀሰው ዘዴ ሙከራ ከተደረገ በኋላ የተገኘውን ውጤት እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል። (ዝርዝሩን በአባሪ 4 በገፅ 140 ይመልከቱ።)

ሠንጠረዥ 3. <u>በድርሰት አንድና ሁለት መካከል ያለ ንፅፅራዊ የስህተት ውጤት</u>

| ተላውጦ | የስህተት ዓይነቶች ብዛት | አማካይ ስህተት | መደበኛ ልዩነት | የነፃነት ደረጃ | የቲ-ስሌት ዋጋ | የቲ-ወሳኝ ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 7082 | 29.42 | 6.795 | 438 | 28.688 | 1.95 |
| ድርሰት ሁለት | 2736 | 13.68 | 4.169 | | | |

በሠንጠረዥ 3 በቀረበው መረጃ መሠረት "በቲ-ቴስት" (T-Test) እስታትስቲካዊ ስሌት ከተሰላ በኋላ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የቲ-ስሌት (T-Calculated) ዋጋ 28.69 ዋጋ ከቲ-ወሳኝ ዋጋ (T-critical) ማለትም (1.95) በልጦ የተገኘ በመሆኑ በሁለቱ ድርሰቶች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት (Significant difference) ታይቷል። ልዩነቱም በሚታይበት ጊዜ በድርሰት አንድ ከተፈፀሙት ስህተቶች በአነሰ ሁኔታ በድርሰት ሁለት ላይ የተፈፀመ ሲሆን ተማሪዎቹም ብዙ ስህተት እንዳይፈፅሙ ያስቻላቸው ጉዳይ ምናልባትም ከአስተማሪዎቻቸው በተሰጣቸው የማበረታቻ ሀሳብና አንዳንድ መመሪያዎች ካልሆነ በስተቀር ይህንን በተመለከተ በጥናቱ አቅራቢ አማካይነት የተደረገ ጥናት የለም። የዚህም ጥናት ትኩረት የሁለቱን የልዩነት ምንጭ ለማጥናትና

ለማቅረብ አለመሆኑ ቀደም ሲል የተገለፀ በመሆኑ የልዩነቱን ምንጭ ለማቅረብ ትኩረት አልተደረገም፡፡

በተራ ቁጥር 4.1.1 የተጠቀሱት ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች ምድቦች በውስጣቸው ያካተቷቸው የተለያዩ ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች ያሉዋቸው ሲሆን እነዚህንም በዝርዝር ለማመልከት ይቻል ዘንድ በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ የአቢይና ንዑስ የስህተት ዓይነት ምድቦች የስህተት ብዛት፣ መቶኛ አማካይ ስህተትና የስህተት ድግግሞሽ በመልመጃዎች አይነት

| አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ | ንዑስ የስህተት ዓይነት ምድብ | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የስህተት | | አማካይ | የስህተት | የስህተት | | አማካይ | የስህተት | የስህተት | | አማካይ | የስህተት |
| | | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ | ብዛት | % | ስህተት | ድግግሞሽ |
| የቋንቋ አጠቃቀም | የቃላት ኣጠቃቀም | 2092 | 29.53 | 8.71 | 10.96 | 740 | 27.04 | 3.70 | 4.34 | 2832 | 28.84 | 6.44 | 7.84 |
| | ግድፈት | 388 | 5.47 | 1.62 | 2.03 | 108 | 3.95 | 1.54 | 0.63 | 496 | 5.05 | 1.13 | 1.37 |
| | ኢ-መደበኛ ቃልትና ሀረጋት | 204 | 2.88 | 0.85 | 1.07 | 192 | 7.02 | 0.96 | 1.13 | 396 | 4.03 | 0.9 | 1.10 |
| | የቃላት አደራደር አደም ተከተል | 244 | 3.45 | 1.02 | 1.29 | 140 | 5.11 | 0.7 | 0.82 | 384 | 3.91 | 0.87 | 1.06 |
| | ተደጋጋሚነት | 340 | 4.80 | 1.42 | 1.78 | 40 | 1.46 | 0.2 | 0.23 | 380 | 3.87 | 0.86 | 1.05 |
| የቋንቋ አውቃቀር | የዓ/ነገር ስምምነት | 676 | 9.55 | 2.81 | 32.54 | 208 | 7.60 | 1.04 | 1.22 | 884 | 9.00 | 2 | 2.45 |
| | የመስተአምር መስተዋድድና ተሳቢ አገባብ | 664 | 9.38 | 2.77 | 3.48 | 100 | 3.65 | 0.5 | 0.59 | 764 | 7.78 | 1.74 | 2.11 |
| | የአጣማሪዎች አገባብ | 232 | 3.28 | 0.97 | 1.22 | 40 | 1.46 | 0.2 | 0.23 | 272 | 2.77 | 0.61 | 0.75 |
| የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም | የአራት ነጥብ አጠቃቀም | 948 | 13.38 | 3.95 | 4.97 | 544 | 19.88 | 2.72 | 3.19 | 1492 | 15.20 | 3.39 | 4.13 |
| | የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም | 322 | 4.55 | 1.34 | 1.69 | 88 | 3.21 | 0.44 | 0.52 | 410 | 4.19 | 0.93 | 1.13 |
| ለመለየት ያልተቻሉ | - | 508 | 7.17 | 2.11 | 2.66 | 280 | 10.23 | 11.4 | 1.64 | 788 | 8.03 | 1.79 | 2.18 |
| የጽንሰ-ሃሳብ ግንዛቤ | - | 464 | 6.55 | 1.93 | 2.43 | 256 | 9.36 | 1.28 | 1.50 | 720 | 7.33 | 1.64 | 1.99 |
| | ጠቅላላ ድምር | 7082 | 100 | 29.51 | 37.12 | 2736 | 100 | 13.68 | 16.04 | 9818 | 100 | 22.31 | 27.17 |

#### 4.1.2 የቋንቋ አጠቃቀም

አለማየሁ /1986፡60/ የሌዋስ (1977)ና ኩፐር (1997)ን ሐሳብ ጠቅሰው እንደሚሉት በፅሁፍ የመግባባት ሂደት ሊሳካ የሚችለው ፅሁፉ የሚቀርብበትን የቋንቋ አጠቃቀም ደንብና ሥርዓት ተከትሎ ሐሳብን ግልፅና ተገቢ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ሲቻል ነው፡፡ ሃሳብ ሊተላለፍ የሚችለው በቃላት አማካይነት በመሆኑ አንድ ፀሀፊ ለማስተላለፍ የሚፈልገውን ጉዳይ ለመግለፅ የሚያስችሉ ቃላትን በመምረጥ፣ በተገቢው አውደ ንባብ በመጠቀም አላስፈላጊ ተደጋጋሚነትንና በሌላ ቋንቋ ተፅዕኖ ምክንያት የሚገቡ ቃላትን በማስቀረት፣ የቃላት አደራደር ቅደም ተከተልን በመጠበቅ፣ ሃሳቡን በማያሻማና ግልፅ በሆነ መንገድ ሲያቀርብ ከታለመው የመግባባት ግብ ሊደርስ ይችላል፡፡ ሆኖም ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ከሆነ መግባባቱን ሊያደናቅፈው ይችላል፡፡

ስለሆነም በዚህ የጥናት ክፍል ውስጥ መግባባትን ሊያግዱ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና በእነሱ ስር ያሉ ንዑሳን ስህተቶች ከላይ ከፍ ብሎ በገጽ 47 በሠንጠረዥ 4 የተመለከቱ ሲሆን ከቀረቡት መረጃዎችም መገንዘብ የተቻለው በዋናው የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ከተዘረዘሩት 5 ስህተቶች መካከል በስህተት ድግግሞሻቸው መጠን ከፍተኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ዋና የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ የሚነሱት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች የቃላት አጠቃቀምና ግድፈት፣ ተደጋጋሚነት፣ የቃላት አደራደርና ኢ-መደበኛ የሆኑ ቃላትና ሐረጋትን መጠቀም ነው፡፡

##### 4.1.2.1 የቃላት አጠቃቀም

ከላይ እንደተገለፀው በቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ከሚገኙት ንዑሳን የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት ዓይነቶች መካከል በርካታ ስህተት የታየው በቃላት አጠቃቀም (ምርጫ) ላይ ነው፡፡ በድርሰቱ ውስጥ በአጠቃላይ ከተፈፀሙት 9818 ስህተቶች መካከል 2832 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ ነው፡፡ የስህተት መቶኛውም 28.84 ሲሆን አማካይ የስህተት መጠኑ ከአጠቃላዩ የስህተት አማካይ (22.31) ውስጥ 6.44 ሊሆን ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ድርሰቱ ከተቆጠሩት 27.17 ድግግሞሾች ውስጥ 7.48 ያህሉ በዚህ ውስጥ

የተቆጠረ በመሆኑ ከንዑሳን የስህተት ዓይነቶች ምድቦች መካከል የቀዳሚነቱን ስፍራ ይዟል፡፡

ሐሳብን ወይም ስሜትን በፅሁፍ አቀናብሮ ለመግለፅ ቃላት መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በመሣሪያነታቸውም ለመጠቀምም አገባባቸውንና የአገባብ ቅርፃቸውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም አንድን ሐሳብ ለመግለፅ፣ ለማስረዳት፣ ለማብራራት የሚመረጡ ቃላት የተፈለገውን ሐሳብ በትክክል ማንፀባረቅ ስለሚኖርባቸው ነው፡፡ ካልሆነ ግን መልዕክቱን ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

የጥናቱ መረጃዎች እንደሚያመለክቱም አብዛኞዎቹ ስህተቶች የሚፈፀሙት መደበኛ ያልሆነ ቃላትን በመምረጥ፣ የቃላቱን ትክክለኛ ፍቺ ካለማወቅና ለዓ/ነገሩ ዐውደ ንባባዊ አገባብ ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉትን ለምሳሌ ያህል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሀ. <u>የቃላት ምርጫ</u> |ከጠቃቀም|

በቃላት አመራረጥ የሚፈፀሙ ስህተቶች የተለያዩ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ ለአብነት ያህል ቢጠቀሱ፡-

1. ለቃላት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ፍቺ በመስጠት የሚፈፀም

<u>ለምሳሌ፡-</u>

- አስተዋይ ተማሪ እንደማንኛውም ተማሪ <u>ልናስተውለው</u> አይገባም፡፡
- ብዙ ሰዎች የወደፊት ምኞታቸውን በተለያዩ <u>የአስተሳሰብ ሁኔታ</u> ያያሉ፡፡
- ብዙ ሰዎች ራሳቸውን እያሻሻሉ ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳሉ፣ እኔም እንደዚሁ <u>ከራስ በመትረፍ</u> ወላጆቼን በከፍተኛ ደረጃ <u>አየዋለሁ</u>፡፡
- ... ኤድስን ለማጥፋት መንግሥታዊ በሆነው ድርጅት ጎን በመሰለፍ <u>እድሜዬ እስካለ ድረስ</u> ከሃገራችን ይህንን <u>አሰቃቂ</u> በሽታ ለማጥፋት እመኛለሁ፡፡
- <u>ይሁን እንጂ</u> ቢሆንም እኔ ደግሞ በበኩሌ ት/ቤት ገብቼ መማርን ጀምሬ እንደነበር <u>የአእምሮዬ ክፍል</u> ይመሰክራል፡፡
- ይኸውም በበኩሌ <u>የማስቀምጠው</u> ምኞት ....

• የፈተናው ሰሞን ሲያልፍ ደግሞ ያንን ልጅ እንደዚያው የለመንችው የእግዚያብሄር ሰላምታ አትጠይቅም፡፡

ከእነዚህ ምሳሌዎች መረዳት የተቻለው ተማሪዎቹ በሚፅፉበት ጊዜ የሚፈልጉትን ሃሳብ ለማስተላለፍ ተቀራራቢ ፍቺ ያለውን ቃል የመምረጥ ወይም ግንኙነት የሌለውን ለመተካት መጠቀማቸውን ነው፡፡ በመጀመሪያ የቀረበው ምሳሌ ከሌሎች ተማሪዎች ይልቅ አስተዋይ ተማሪን ለየት ባለ ሁኔታ መመልከት እንደሚገባ ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል፡፡ ሆኖም ከስሩ የተሰመረበት ልናስተውለው የሚለው ቃል ያለቦታው የገባ በመሆኑ አስተዋይ ተማሪን እንደማንኛውም ተማሪ ልናየው አይገባም ቢባል ይሻል ይሆናል፡፡ "ብዙ ሰዎች የወደፊት ምኞታቸውን በተለያዩ የአስተሰሰብ ሁኔታ ያያሉ" የሚለው የሰዎች ምኞት የተለያየ መሆኑን ለመግለፅ የቀረበ መስሎ ይታያል፡፡ እንደዚህም ከሆነ የብዙ ሰዎች ምኞት የተለያየ ነው ወይም ብዙ ሰዎች ምኞታቸውን በተለያየ መንገድ ይገልፃሉ... ቢባል የተሻለ ነበር፡፡ "እኔም እንደዚሁ ከራስ በመትረፍ ወላጆቼንና ዘመዶቼን በከፍተኛ ደረጃ እየዋለሁ" የሚለው ብዙ ሰዎች ራሳቸውን አሻሽለው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ከራሳቸው አልፈው ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ሀሳቡ ይህ ከሆነ "እኔም ራሴን አሻሽዬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ስደርስ ከራሴ አልፎ ወላጆቼንና ዘመዶቼን የመርዳቱን ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ የማስበው ነው" ተብሎ ቢፃፍ ይሻላል "... ኤድስን ለማጥፋት መንግሥታዊ በሆነው ድርጅት ጎን በመሰለፍ እድሜዬ እስካለ ድረስ ከሃገራችንን ይህንን አሰቃቅ በሽታ ለማጥፋት እመኛለሁ፡፡" የሚለው "እኔ ከመንግሥት ጎን በመሰለፍ ኤድስ የተባለውን አሰቃቂ በሽታ ለማጥፋት እመኛለሁ፡፡" በሌላ በኩል ደግሞ በህይወት የመኖሩን ጉዳይ መግለፅ አስፈላጊ ከሆነ "ዕድሜዬ እስካለ ድረስ" የሚለው "በህይወት እስካለሁ ድረስ" በሚለው ቢተካ ጥሩ ነበር፡፡ "ይሁን እንጂ ቢሆንም እኔ ደግሞ በበኩሌ ት/ቤት ገብቼ መማርን ጀምሬ እንደነበር የአእምሮዬ ክፍል ይመሰክራል፡፡" የሚለው ተደራራቢ ስህተቶችን የያዘ ነው፡፡ ይኸውም (1) የተሳቢ ምልክት ያለቦታው ገብቷል (2) ሁለት አጣማሪዎች "ይሁን እንጂ" ቢሆንም" አንድ ላይ ገብተዋል፡፡ (3) "የአእምሮዬ" የሚለው ሀረግ በተገቢው ሁኔታ ያልተመረጠ ነው፡፡ "እኔ ደግሞ በበኩሌ" በሚለው ውስጥ ከሁለት አንዱ "ደግሞ" ወይም "በበኩሌ" መቅረት የሚችሉ ነበሩ፡፡ ስለሆነም ዓ/ነገሩ "እኔም በበኩሌ ት/ቤት ገብቼ መማር ጀምሬ እንደነበር የሚታወስ ነው" ቢባል ወይም "ይሁን እንጂ ት/ቤት ገብቼ ስማር እንደነበር መመስከር ይቻላል ..."

ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ "ይኸውም በበኩሌ የማስቀምጠው ምኞት ..." በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል በተቀራራቢ የገባ ነው፡፡ ስለሆነም "ይኸውም በበኩሌ የሚኖረኝ ምኞት ..." ቢሆን ደህና ነው፡፡ "የፈተናው ሰሞን ሲያልፍ ደግሞ ያንን ልጅ እንደዚያው የለመነችው የእግዚያብሄር ሰላምታ አትጠይቅም፡፡" የሚለው ዓ/ነገር "ልጇን እንደዚያ የለመነችውን ያህል ፈተናው ሲያልፍ የእግዚያብሄር ሰላምታ ትነፍገዋለች" ቢባል ሊስተካከል ይችላል፡፡

2. ሌላው በዚህ ክፍል የታየው ስህተት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካይነት ቃላትን በተሳሳተ መንገድ የመጠቀም ጉዳይ ነው፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 5 በገፅ 141 ይመልከቱ)፡፡
   - እንግዲህ ቃሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ከመስረቅና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መሄዱ ጥሩ ይመስለኛል፡፡
   - አንዳንድ ተማሪዎች ... አላስኮርጅም ብለው ከደበቃ ልጅዬውን መደብደብ የምያስቡ ቦሰኔ (ድርዬ) ተማሪዎች አሉ፡፡
   - የፈተና አላማ ተማሪው ምን ያህል የተማረውን ትምህርት አጥንቶ ራሱን የምለካበት መሳሪያ ... ለዚህ አይዘጋጅም፡፡
   - የእያንዳንዱማ የሚገርም ነው፡፡ ልክ ፈተናው ስደርስ ... ጎበዙን ጠብቆ ስረዳ ምንም ሳያንገራግር ወደ ጎበዙ ተማሪ ጋ ይሄድና "እሄንን ፈተና ካላስኮረጅከኝ በህይወትህ ፍረድ" እያሉ... በፍርሃት ውስጥ እንድወድቅ ያደርጋል፡፡
   - ጥፈት ቢፈፅምና እንድቀጣ /እንድገረፍ/ በቤተሰቡ ቢወሰን የእናት ሆድ ገር በመሆኑ ... በማለት ከግርፈት ያድኑታል፡፡
   - በዘንድሮው ዓመት የጊዜው ያልጠበቀ ስናብ በመስነብ አማካኝነት የተከሰተው ጎርፍ ... ሃብትና ንብረት ሊያጠፋ ችሏል፡፡
   - ይኸውም ወቅቱ የአዝመራ ወቅት ስለነበር እስመራውም በተለያዩ ሐገሮች ወደ መድረስ ደረጃ ደርሰው ስለነበረ በዝናቡ አማካኝነት በፊት ከምገኘው ገብ አዝመራው በእጥፍ እንደቄነስ ይነገራል፡፡

- እኛም ደግሞ ... ጥሬታችን ብቻ ሳይሆን መንግስትም ጥሮ ማለትም በእርዳታም ሆኔ በለለም ጥራቱ የጠነከሬ መሆን አለበት፡፡
- አሁን እየተማርኩት ያለውት ... 9 ወር ሙሉ በሄድ ... በእናቴ እገዛ ስለለውት ... ባገኘውት ደሞስ እኋ እንዳደረገችልኝ ውለታዋን ይከፍልላታለው፡፡
- ስለጸታ ትምህርት ባለመኖሩ እንድኖር ብደረግ ሰው ሁሉ የተለያዩ በሽታዎችን ይከለከላል ማለት ነው፡፡
- አንዱ በአእምሮ የያዘውን ስናገር ሌላው ደግሞ ... በቁራጭ ወረቀት ጽፎ ይገባል፡፡
- ወብነሽ የምትባል ነበረች፡፡ በጣም ወደድኩት፡፡ ... ብዬ ልነግራት አልቻልኩም እፈራ ነበር

እነዚህ ለአብነት ያህል የቀረቡ ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑት ተጠኝ ተማሪዎች ሳልስና ሳድስን፣ ግዕዝና ራብዕን፣ ሀምስና ግዕዝን፣ "እ" ና "ይ" ን እንዲሁም "ዞ"ና "ሰ"ን "ሀ" ና "ወ"ን እያለዋወጡ በመጠቀማቸው የተነሳ ሊከሰቱ የቻሉ ናቸው፡፡ ይኸንን አስመልክቶ ይልማ /1956፡3-17/ እንደሚሉት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ያሉዋቸው አናባቢዎች 5 ብቻ በመሆናቸው በእነሱ ቋንቋ ውስጥ የሌሉትን አናባቢዎች በሚጠቀሙበት ጊዜ በራሳቸው ካሉት ጋር የማጋጨትና በዚያም ሳቢያ ስህተት የመፈጠር ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "ዘ" ና "ዠ" የሌሉ በመሆናቸው በ"ዘ" ፋንታ "ሰ"ን በ"ዠ" ፋንታ "ጀ"ን ይጠቀማሉ፡፡ በሌላም በኩል የአማርኛ ቋንቋ ግሶች ፣ በሥሶተኛው መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ጾታ ሲነገሩ መድረሻቸው "አ" ይሆናል፡፡ የኦሮምኛው ግስ ደግሞ በ"ኤ" ድምፅ የመድረስ ፀባይ አለው፡፡ በዚህም የተነሳ ወደ ሃምስ ይለውጡታል፡፡ ለምሳሌ "የጠነከረ" ለማለት "የጠነከሬ" ይሉታል፡፡ ተባዕታይና አንስታይ ጾታን መለያ የሚሆን የጠበቀ ህግ በኦሮምኛ ቋንቋ የሌለ በመሆኑ ሴቱን እንደወንድ የመጥራቱ ጉዳይም ታይቷል፡፡ ስለሆነም በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ስህተቶች ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡ /ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1987፡7-9)

እነዚህ ከስራቸው የተሰመረባቸው ስህተቶችም ከላይ በተገለፀው መንገድ በመጠቀም የተከሰቱ ስህተቶች ሲሆኑ በሚከተለው መንገድ ተስተካክለው ቢፃፉ

ለመግለፅ የተፈለገውን ሀሳብ በትክክል ሊያስተላልፉ ይችሉ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

- እንግዲህ ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ከመስረቅና የማያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት ተቆጥቦ በደንብ ተዘጋጅቶ መሄዱ ጥሩ ይመስለኛል፡፡
- አንዳንድ ተማሪዎችን ... አላስኮርጅም ብሎ ከደበቀ ልጁን ለመደብደብ የሚያስቡ ቦዘኔ (ዱርዬ) ተማሪዎች አሉ፡፡
- የፈተና አላማ ተማሪው ምን ያህል የተማረውን ትምህርት እንዳጠና ራሱን የሚለካበት መሳሪያ ... ለዚህ አይዘጋጁም፡፡
- የአንዳንዱማ የሚገርም ነው፡፡ ልክ ፈተናው ሲደርስ ... ያለምንም ማንገራገር ወደ ጎበዙ ተማሪ በመሄድ "ይህን ፈተና ካላስኮረጅከኝ በህይወትህ ፍረድበት" እያለ በማስፈራራት ልጁን በፍርሃት እንዲወድቅ ያደርገዋል፡፡
- ጥፋት ቢፈፅምና እንዲቀጣ /እንዲገረፍ/ በቤተሰቡ ቢወሰን የእናት ሆድ ገር በመሆኑ ... በማለት ልጁ ን ከግርፋት ታድነዋለች፡፡
- በዘንድሮው ዓመት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመዝነቡ አማካኝነት የተከሰተው ጎርፍ ... ሃብትና ንብረት ሊያጠፋ ችሏል፡፡
- የአዝመራ ወቅት ስለነበር በተለያዩ አገሮች ደርሶ የነበረው አዝመራ በጎርፍ አማካኝነት በመጠራረጉና በመበላሸቱ ቀደም ሲል ይገኝ ከነበረው ገቢ በእጥፍ ቀንሷል፡፡
- የእኛ ጥረት ብቻ በቂ ባለመሆኑ በእርዳታም ሆነ በሌላ መንገድ የመንግሥት ጥረት የጠነከረ መሆን አለበት፡፡
- አሁን በእናቴ እርዳታ እየተማርኩ በመሆኑ ሥራ ይገኝ ደመወዝ ሳገኝ እሷ ላደረገችልኝ እገዛ ውለታዋን እከፍላለሁ፡፡
- የጾታ ትምህርት ባለመኖሩ ለወደፊቱ እንዲኖር ቢደረግ ሰው ሁሉ የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል ይችላል ማለት ነው፡፡
- አንዱ በአእምሮው የያዘውን ሲናገር ወይም ሲፅፍ ሌላው ደግሞ ... በቁራጭ ወረቀት ጽፎ ይገባል፡፡
- ወብነሽ የምትባል ነበረች፡፡ በጣም ወደድኳት ... ብዬ ልነግራት አልቻልኩም፡፡ እፈራ ነበር፡፡

ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሚፅፉበት ጊዜ በአንድ ዓ/ነገር ውስጥ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ከአንድ በላይ በመሆናቸው ዓ/ ነገሩ ሲስተካከል እነዚህንም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ሌላው ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው በአንድ ዓ/ነገር ውስጥ ተደራራቢ ስህተቶች በመኖራቸው ለአንድ የስህተት ዓይነት ምድብ የተቆጠረው ለሌላው የስህተት ዓይነት ምድብ የሚቆጠር ሲሆን በምሳሌ አቀራረቡም በኩል አንድ ዓ/ነገር በተለያየ አጋጣሚ ሊነሳ ይችላል።

ከላይ ከቀረቡት የናሙና ምሳሌዎች መገንዘብ የተቻለው በአናባቢ መለዋወጥ የተነሳ የተከሰቱ ስህተቶች ለምሳሌ፡-

"ቢሰጥ" ለማለት "ብሰጥ" ወይም "ብሰጥ" ለማለት "ቢሰጥ"
"የሚለካበት" "የምለካበት" ወይም "የምለካበት" ለማለት "የሚለካበት"
"ሲረዳ" "ስረዳ" ወይም "ስረዳ" ለማለት "ሲረዳ"
"እንዲቀጣ" "እንድቀጣ" ወይም "እንድቀጣ" ለማለት "እንዲቀጣ"
"ኢንዲገረፍ" "እንድገረፍ"... መባላቸው

በዓ/ነገሩ ውስጥ በእሱ ድርጊት ፈፃሚነት የተመለከተው ሃሳብ በእኔ ባይ ድርጊት ፈፃሚ የተፈፀመ እንደሆነ በእኔ ባይ ድርጊት ፈፃሚ የተመለከተው በእሱ ባይ ድርጊት ፈፃሚነት የተመለከተ እንደሆነ ተደርጎ እንዲቀርብ አድርገውታል።

በሌላም በኩል በዓ/ነገሩ ውስጥ እንዲገለፅ የተፈለገውን ሀሳብ በተቃራኒው እንዲገለፅ አድርጎታል።

<u>ለምሳሌ፡-</u> "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ከመስረቅና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መሄድ ጥሩ ይመስለኛል" የሚለው "... አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና የማያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መሄድ ጥሩ ይመስለኛል።" ለማለት ታስቦ የተፃፈ ነው። ሆኖም ከላይ በተገለፀው መንገድ መፃፍ ችግሩን እንዲከሰት አድርጎታል።

ሌላው ደመወዝ ለማለት በግማሽ አናባቢ "ወ" ምክንያት ወደ "ደሞዝ" የተለወጠው ቃል <u>"ደሞስ"</u> ተብሎ መፃፍ ቃሉ ሌሎች ፍቺዎችን እንዲይዝ አስችሎታል።

3. በአማርኛ ቋንቋ መድበለ ቃላት እውቅናን ያላገኙ አህጽሮተ ቃላትን የመጠቀም ጉዳይ ሌላው የቃላት አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ ተጠኝ ተማሪዎቹ ምህፃረ ቃል ፈጥረው ቢጠቀሙም እንኳን ያልተለመዱ በመሆናቸው በጽሑፍ የመግባባቱን ሂደት ያግዳሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- በአሁኑ ጊዜ ያለው ህዝብ ስለበሽታው ግንዛቤ ስለሌለው መ/ት ይህንን አስከፊ በሽታ ለመቋቋም ... ማበርከት ይኖርብናል፡፡
- እንዲሁም ለመላው ኢ/ያ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡
- ስለዚህ ዋና ተግባሩ ህ/ቡን ከዚህ ደዌ በሽታ ለማላቀቅ ... ህ/ቡ ጉልህ ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡
- በ1990 ዓ.ም. የተማሪዎች ዝግጅት ወ/ም የፈተና አቀባበል ምን ይመስል እንደነበር ለመግለፅ ያህል ...
- እ/ር ካለ በሚቀጥለው እንገናኛለን፡፡

እነዚህ የጥናቱ መረጃዎች በሚታዩበት ጊዜ አንባቢ ወይም ተደራሲ ለምህፃረ ቃላቱ የተለያዩ ፍችዎችን መስጠት ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡-

- መ/ት ለሚለው - መሠረተ ትምህርት፣ መንግስት፣ መስሪያ ቤት፣ መምህርት፣
- ህ/ቡ ለሚለው - ህዝቡ፣ ህብረተሰቡ፣ ህዝባዊ ቡድኑ .....
- እ/ር " - እግር፣ እግዚአብሔር፣ እስር ... ሊባል ይችላል፡፡ ስለዚህ አንባቢው እንደነዚህ ዓይነት ቃላትን በሚያገኝበት ጊዜ ፍቻቸውን ባለማወቁና ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም ውጭ በመሆናቸው የዓ/ነገሩን ሃሳብ ሳይገነዘብ ሊቀር ይችላል፡፡

4. ከዓ/ነገሩ ዐውደ-ንባብ ውጭ የሆኑ ቃላትን የመጠቀም ጉዳይ ሌላው በቃላት አመራረጥ ላይ የሚታይ ስህተት ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

1. ዶክተር <u>አከሉ</u> <u>አከሉ</u> ዛሬ በዚኛው ቦታ ሄዶ ጎብኝት ሲያደርግ <u>የሬድዮ ፔፒስ</u> ዘግቧል እያለ ይናገራል፡፡
2. እንዲሁም ራሴን ለፈተና ካዘጋጀሁት የወደፊት ምኞቱ <u>የማላጣበት</u> ምክንያት የለም፡፡

3. ውጤቱ ከመጣልኝ በቀጥታ ፕሮፌሰር ዶክትሬሽና ከፍተኛ የቁልፋ ቦታ ለመግባት እፈልጋለሁ፡፡

4. ሁለቱም ደግማ ይህንን ነገር የግድ መፈፀም አለብን ብሎ ብያስቡም እንኳ የፆታ ትምህርት በሳይንስ በተረጋገጠላቸው መንገዶች ይጠቀማሉ፡፡

5. ኤድስ በፆታ ብቻ ይተላለፋል ለማለት ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ ግን የምተላለፈው በግብረ ስጋ ግንኙነት ስለሆነ ነው፡፡

6. አሁን ደግሞ ተስፋውን ያወቀ ስፈንድቅ ተስፋ ያስቆረጠው መርክ ለመለመን አውቆ ቲቸር ከመቶ ስንት አለኝ እያለ ትህትናን በመነናፀፍ ይጠይቃል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የጥናቱ መረጃዎች የሚጠቁሙት ተጠኝዎቹ በዓ/ነገር አማካኝነት ሐሳብ ለማስተላለፍ በሚፈልጉበት ጊዜ የሚመርጧቸውን ቃላት ፍችዎች ካለመገንዘብ የተነሳ ከዓ/ነገሩ ዐውደ-ንባብ ጋር አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ቃላትን ለምሳሌ /ካላይ የተሰመረባቸውን/ በመጠቀማቸው ለማስተላለፍ የፈለጉት ሀሳብ በግልፅ እንዳይተላለፍ መሰናክል መሆናቸውን ነው፡፡

የመጀመሪያው ዓ/ነገር ሲታይ ተማሪው ለመግለፅ የፈለገው ዶክተሩ በተለያዩ ቦታዎች ሄዶ ጉብኝት ያደረገ ለመሆኑ በሬዲዮ የተገለፀ መሆኑን ለመንገር ነው፡፡ ሆኖም "የሬዲዮ ፕሬስ" ትርጉሙን ባለመረዳቱና "ፕሬስ" የሚለው ቃልና "ፔፕስ" የሚለውን ቃል ለይቶ ባለማወቁ ስህተቱን ሊፈፀም ችሏል፡፡ ስለዚህ "ዶ/ር እከሌ (ተሰማ፣ ከበደ፣ ብርሃኑ...) በዛሬው ዕለት ሰበታ፣ አቃቂ ... ሄዶ ጉብኝት ያደረገ ለመሆኑ በሬዲዮ ዜና አጠናቃሪ ወይም በኢትዮጵያ ሬድዮ አገልግሎት ተዘግቧል" ቢሆን ሊስተካከል ይችላል፡፡

በተራ ቁጥር 2 የቀረበው ሃሳብ "ራሴን ለፈተና ካዘጋጀሁ የተመኘሁትን የማላገኝበት ምክንያት አይኖርም" ለማለት ታስቦ የተፈፀመ ሲሆን "የማላጣበት" የሚለው ቃል በመመረጡና ይህ የተመረጠውም ቃል ራስን ለፈተና ከማዘጋጀት ሀሳብ ጋር አብሮ ባለመሄዱ እንዲገለፅ የተፈለገው ሀሳብ በተቃራኒው እንዲሆን አስችሎታል፡፡ ስለዚህ የዓ/ነገሩን ሀሳብ እንዳይለቅ ለማድረግ "ራሴን ለፈተና ካዘጋጀሁት የወደፊት ምኞቴን የማላገኝበት ምክንያት የለም" ወይም "የወደፊት ምኞቴን የማጣበት ምክንያት የለም" ቢሆን ጥሩ ነው፡፡

ሌላው በዚሁ ዓ/ነገር ውስጥ ስህተቱን እንዲከሰት ያደረገው ጉዳይ ተማሪው "የማላጣበት" በሚለው ቃል ውስጥ አፍራሽ ቅጥያ መኖሩን ካለመገንዘቡ የተነሳ ነው።

በተራ ቁጥር 3 ከቀረበው ዓ/ነገር ለመገንዘብ የሚቻለው ተማሪው የ12ኛ ክፍልን ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ካለፈ ለፕሮፌሰርነት ለዶክተርነት ...የሚያበቃውን ትምህርት ለመማር ዩኒቨርስቲ መግባት እንደሚፈልግና ተመርቆ ከወጣ በኋላም በሚሰማራበት የሥራ መስክ የኃላፊነት ቦታ ለመያዝ የፈለገ መሆኑን ነው። ሆኖም ፕሮፌሰር፣ ዶክትሬትና ቁልፍ ቦታ የተሰኙትን ቃላት ፍቺ ካለመገንዘቡ የተነሳ እነዚህን ያለ ዐውደ ሲጠቀምባቸው ታይቷል። ስለዚህ የዓ/ነገሩን ሃሳብ በትክክል ለመግለፅ "ውጤቱ ከመጣልኝ ዩኒቨርስቲ ገብቼ ለዶክተርነት የሚያበቃኝን ትምህርት በመማር ከተመረቅሁ በኋላ ቁልፍ ቦታ ላይ ለመቀመጥ እፈልጋለሁ" ቢል የተሻለ ይሆናል።

በተራ ቁጥር 4 "ሁለቱም ደግማ ይህን ነገር የግድ መፈፀም አለብን ብሎ ቢያስቡም እንኳ የፆታ ትምህርት በሳይንስ በተረጋገጠላቸው መንገዶች ይጠቀማሉ።" ተብሎ የቀረበው የዓ/ነገሩ ሀሳብ ባልና ሚስት ይሁኑ ወይም ሌሎች ተቃራኒ ፆታዎች የግብረ ስጋ ግንኙነት እንፈፅማለን የሚሉ ከሆነ በፆታ ትምህርት አማካኝነት እርግዝናንም ሆነ በሽታን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎች ስለተገለጹ በነሱ ለመጠቀም ይችላሉ ለማለት የታሰበ ይመስላል። ሆኖም የፆታ ትምህርትን ፍቺ ካለመገንዘብ የተነሳ ያለ ዐውዱ በመግባቱ ሀሳቡን ግልፅ እንዳይሆን አድርጎታል።

በተራ ቁጥር 5 በቀረበው ዓ/ነገር ውስጥ ለመግለፅ የተፈለገው የኤድስ በሽታ አብዛኛውን ጊዜ የሚተላለፈው በግብረ ስጋ ግንኙነት ስለመሆኑ ነው። ሆኖም ተማሪው የፆታ ግንኙነት ማለት ምን እንደሆነ ባለመገንዘቡ "ኤድስ በፆታ ብቻ ይተላለፋል ለማለት ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ የምተላለፈው በግብረ ስጋ ግንኙነት ስለሆነ ነው" ብሎ ሊፅፍ ችሏል። ስለዚህ ይህ ዓ/ነገር "ኤድስ ባልተቀቀለ መርፌና ምላጭ በመጠቀም የሚተላለፍ ቢሆንም በአብዛኛው ግን በግብረ ስጋ ግንኙነት ይተላለፋል" ቢባል ወይም "ኤድስ አብሮ በመብላት፣ በመጠጣት፣ በመሳሳም የሚተላለፍ ሳይሆን በአብዛኛው በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ ነው" ቢባል የተሻለ ይሆናል።

በተራ ቁጥር 6 "አሁን ደግማ ተስፋውን ያወቀ ስፈንድቅ ተስፋ ያስቆረጠው መርከ ለመለመን አውቆ ከመቶ ስንት አለኝ እያለ ትህትናን በመጎናፀፍ ይጠይቃል" የሚለው ዓ/ነገር የያዘው ሀሳብ ደህና ውጤት ያገኘ ተማሪ ሲደሰት የወደቀ ተማሪ ግን ተስፋ በመቁረጥ ከመምህሩ ፊት አንገቱን በማቅለስለስ ማርክ ለማስጨመር የሚለምን መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል:: ሆኖም ተስፋውን ያወቀ የሚለው ሀረግ "ተስፋ የቆረጠው" ከሚለው የተለየ ፍቺ አይኖረውም:: ምክንያቱም "ተስፋውን አወቀ" ሲል በሁለቱ ጎን ማለትም በጥሩም ሆነ በመጥፎ ሊሆን ይችላልና ነው:: ስለዚህ "ደህና ውጤት ያገኘ ተማሪ ሲፈንድቅ ያላገነ ግን ተስፋ በመቁረጥ በትህትና አስተማሪውን ማርክ ይለምናል" ቢሆን የተሻለ ይሆን ነበር::

#### 4.1.2.2 ግድፈት

በሠንጠረዥ 4 በገፅ 47 በቀረበው መረጃ መሠረት ሁለተኛው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ግድፈት ነው:: በተጠኝ ተማሪዎቹ ከተፈፀሙት 4488 የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች መካከል 496 ስህተቶች የተፈፀሙት በዚሁ ሲሆን ይኸም 5.05 በመቶ ሊሆን ችሏል:: አማካይ ስህተቱ 1.13 ሲሆን በ100 ቃላት ውስጥ የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽም 1.37 ነው::

በጥናቱ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰቱን በሚፅፉበት ጊዜ መግባት ያለባቸውን ነገሮች የሚገድፉ በመሆናቸው በጽሀፈት የመግባባቱን ሂደት ሊያደናቅፈው እንደቻለ ነው:: ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ለመጥቀስ ተሞክሯል:: (ግድፈት ያለበትን ቦታ በቅንፍ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል::)

- የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች የሚባሉት መካከል () የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው::
- ሆኖም የአገራችን ህዝብ ስለበሽታው ያለው አመለካከት እጅግ ኋላ ( ) ነው::
- ሥራውን ከጀመርኩ በኋላ በተማርኩት ደንብ ( ) ስራዬን መስራት እጀምራለሁ::
- ኤድስ የሚተላለፍባቸው ዋና ዋና ( ) ከሆኑት ውስጥ ባልተቀቀለ መርፌ ንፅህና በሌለው ስለት ( ) በግብረ ስጋ ግንኙነት ነው::

- አንድ ተማሪ አስተዋይ ( ) ማለት የሚቻለው ካየውና ከሰማው ነገር እንዲሁም ደግሞ ( ) ስራ ማስታወስ መገንዘብ የሚችል ተማሪ ማለት ነው፡፡
- በአጠቃላይ ሃኪም ለነዚህ ሁሉ መፍትሔ ( ) አለበት፡፡

እነዚህ የተገደፉት ቃላት በዓ/ነገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ዓ/ነገሩ እንደሚከተለው ሊስተካከል ይችላል፡፡

የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ከሚባሉት መካከል አንዱ የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ ሆኖም የአገራችን ህዝብ ስለበሽታው ያለው አመለካከት እጅግ ኋላቀር ነው፡፡ ስራውን ከጀመርኩ በኋላ በተማርኩት ደንብ መሠረት እሰራለሁ፡፡ የኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ከሆኑት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ባልተቀቀለ መርፌና ስለት መጠቀምና የግብረ ስጋ ግንኙነት ናቸው፡፡ አንድ ተማሪ አስተዋይ ነው ማለት የሚቻለው ከአየውና ከሰማው መገንዘብ ሲችል ነው፡፡ በአጠቃላይ ሀኪም ለዚህ ሁሉ መፍትሄ መሻት አለበት፡፡

### 4.1.2.3 ኢ-መደበኛ አጠቃቀም

ሒተን /1988:135/ እንደሚሉት ሀሳብን በፅሁፈት አማካኝነት ለማስተላለፍ ተቀባይነት ባለው መደበኛ ቃላትና ሀረጋት መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ኢ-መደበኛ የሆነ አጠቃቀም ግን እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ግልፅነት ያሳጣዋል፡፡ ይሁን እንጅ በጥናቱ የተገኘው መረጃ ኢ-መደበኛ የሆነ አጠቃቀም እንዳለ ያመለክታል፡፡

በቋንቋ አጠቃቀም ከተፈፀሙት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች መካከል በሶስተኛ ደረጃ የሚገኘው ኢ-መደበኛ የሆነ ቃላትን የመጠቀም ጉዳይ ነው፡፡ በሠንጠረዥ 4 በገፅ 47 በተገኘው መረጃ መሠረት ከአጠቃላዩ ስህተቶች 396 ያህሉ የተቆጠረው በዚሁ ንዑስ ክፍል ሲሆን ይህም በተጠኝ ተማሪዎቹ ከተፈፀሙት ስህተቶች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 4.03 ሆኗል፡፡ አማካይ ስህተቱም 0.9 ሲሆን አማካይ የስህተት ድግግሞሽም 1.10 ሊሆን ችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡ (ስህተት ያለበት ቦታ ተሰምሮበታል)

1. ከእናታችን ተወልደን ብንተብት ጥሩ አይደለም፡፡
2. እናት እህልም ከለለ የትም ገብታ አፈርደበወነ ልጅዋን ታሳድጋለች፡፡

3. ልቤን በተለያየ የአእምሮ ብስጭት <u>እበረዛለሁ</u>፡፡

4. እንደእሷ በታመመች ቁጥር ጠይቀን በተቸገረች ጊዜ <u>ችግሯን አውለን</u> በጠራችን ጊዜ ደርሰንላት <u>የምንለበኛት</u>

ከቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ የመጀመሪያው ዓ/ነገር በእናት ላይ መኩራራት አስፈላጊ አለመሆኑን የሚገልፅ ይመስላል፡፡ ሆኖም "ብንተብት" የሚለው ቃል ራሳቸውን አራዳ አድርገው በሚቆጥሩት ዘንድ ትክክለኛ አጠቃቀም እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ስለዚህ "ወልዳ ባሳደገችን እናታችን ላይ ብንኩራራ ጥሩ አይደለም" ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡ በተራ ቁጥር ሁለት የቀረበው ዓ/ነገር እናት በእጅዋ ምንም ነገር ባይኖራትም እንኳ መከራዋን አይታ ተሰቃይታ ለምናም ቢሆን ልጅዋን የምታሳድግ መሆኗን ለመግለፅ የቀረበ ይመስላል፡፡ ሆኖም "አፈርድበወነ" የሚለው ዘዬ ወይም ኢ-መደበኛ አባባል በመሆኑ ስህተቱ ሊመጣ ችሏል፡፡ ስለሆነም "እናት ምንም ነገር ባይኖራትም ተቸግራና ተሰቃይታ ልጅዋን ታሳድጋለች" ቢባል ይሻል ነበር፡፡ በተራ ቁጥር 3 የቀረበው ዓ/ነገር ተደጋጋሚ ስህተት ታይቶበታል፡፡ 1) የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ስህተት ያለበት ሲሆን ሲስተካከል "ልቤ በተለያየ የአእምሮ ብስጭት ይበረዛል" ወይም "በተለያየ የአእምሮ ብስጭት ልቤን እበርዘዋለሁ" ይሆናል፡፡ 2) ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ፍቺ ባለው ቃል "ብስጭት" የመጠቀም ጉዳይ ታይቷል፡፡ ይህም ሲስተካከል "ልቤ በተለያየ የአእምሮ ጭንቀት ይበረዛል" ሊሆን ይችላል፡፡ 3) "እበረዛለሁ" የሚለው ኢ-መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ነው፡፡ በዓ/ነገሩ አማካይነት ለመግለፅ የተፈለገው ጉዳይ በተለያዩ ነገሮች ሳቢያ ልቡ የተረበሸ መሆኑን ይመስላል፡፡ እንደዚህ ከሆነ "ልቤ በተለያዩ ነገሮች ሳቢያ ይረበሻል" .... ቢባል ሊስተካከል ይችላል፡፡ በተራ ቁጥር 4 የቀረበው ዓ/ነገር የቋንቋ አወቃቀር ስህተትና ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት ሲሆን የቋንቋ አወቃቀሩ ስህተት በስፍራው ሲደረስበት ይገለፃል፡፡በዓ/ነገሩ አማካይነት ለመግለፅ የተፈለገው ጉዳይ "እኛ በታመምን ጊዜ የምትጠይቀንና በተቸገርን ጊዜ የምትረዳን እናታችን በመሆኗ እሷ በታመመችና በተቸገረች ጊዜ እንደእሷ ሆነን ችግሯን የምናስወግድላት እኛ መሆን አለብን" ለማለት ተፈልጎ ይመስላል፡፡ "..... ችግሯን አውለውን በጠራችን ጊዜ ደርሰንላት የምንለበኛት" ሊባል ይቻለው፡፡ ስለዚህ ዓ/ነገሩን ለማስተካከል "የእናታችንን ችግር ተረድተን ልንረዳት ወይም ልንንከባከባት የምንችለው እኛ መሆን አለብን" ተብሎ ቢስተካከል ደህና ይሆናል፡፡

4.1.2.4 <u>የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል</u>

በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ካሉት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች መካከል ከኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ የሚገኘው የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ስህተት ነው።

በሠንጠረዥ 4 በቀረበው መረጃ መሰረትም ተማሪዎቹ ከፈፀሟቸው 9818 አጠቃላይ ስህተቶች መካከል የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ስህተት 384 ሲሆን ይህም በመቶኛ 3.91፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 0.87ና አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 1.06 ያህል ሆኗል። ለአብነት ያህልም የሚከተሉት መረጃዎች ቀርበዋል። (ዝርዝሩን በአባሪ 5 ይመልከቱ)

- የፆታ ልዩነት አይል የዘር ልዩነት አያውቅ በመደዳ የሚጨፈጭፍ እንደሰደድ እሳት
- ይህን ያህል ትብብር ይህን ያህል ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ ምድርን ለማጥፋት
- ... ነገር ግን ያንን የተመኙትን በተግባር ላይ ማሳየቱ ነው ቁም ነገሩ
- ማነው ይህን ዓይነት እቅድ አውጥቶ የሚያሰራው ብዬ ብጠይቅ ኢንጅነር ከሆንክ መስራት ትችላለህ አለኝ አንድ አዲስ አበባ የሚኖር ወንድሜ
- አንዳንድ ሰዎች ታመው ሳያቸው ... ማረፊያ ቦታ ሰጥቼ ነበር የማስተናግዳቸው

እነዚህ የቃላት አደራደር ስህተቶች ከተለመደው የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ቅንብር ብሎም የዓ/ነገር አመሰራረት ውጭ የተሰለፉ በመሆናቸው የዓ/ነገሩ ሀሳብ ሳይቋጭ በተንጠልጠል ላይ እንዳለ እንዲቀር አድርገውታል። በዚህም የተነሳ በፅሁፍ የመግባባቱን ሂደት ሊያደናቅፈው ችሏል። ስለዚህ እነዚህ ከላይ በማስረጃነት የቀረቡት ዓ/ነገሮች በሚከተለው መንገድ ቢስተካከሉ ሙሉ ስሜት ሊሰጥ የሚችል ዓ/ነገር ሊመሰረት ይቻላል።

የፆታና የዘር ልዩነት ሳይል ሁሉንም በመደዳ እንደሰደድ እሳት የሚጨፈጭፍ ነው። ይህን ያህል ትብብርና ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ

ምድርን ባዶ ለማድረግ ነው:: ይህንን ዓይነት እቅድ አውጥቶ የሚያሰራው ማነው? ብዬ ስጠይቅ አንድ አዲስ አበባ የሚኖር ወንድሜ ኢንጅነር ከሆንክ መስራት ትችላለህ አለኝ:: አንዳንድ የታመሙ ሰዎች ባየሁ ጊዜ ማረፊያ ቦታ ሰጥቼ አስተናግዳቸው ነበር:: እግዚአብሄር ለዚያው ካደረሰን የኔ ምኞት ገደብ የለውም:: ቁም ነገሩ ያንን የተመኙትን በተግባር ማሳየቱ ላይ ነው::

4.1.2.5 ተደጋጋሚነት

ከቋንቋ አደራደር ቅደም ተከተል ንዑስ የስህተት ዓይነት ቀጥሎ የሚገኝ ሲሆን እሱም የመጨረሻውን ደረጃ የያዘ ነው:: በመሆኑም በተማሪዎቹ ድርሰቶች ከተቆጠሩት አጠቃላይ ስህተቶች መካከል 380 ያህሉ የተፈፀሙት በዚሁ ሲሆን ይህም በመቶኛ 3.87፣ አማካይ ስህተቱ 0.86 እና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ደግሞ 1.05 ሊሆን ችሏል::

አንዳንድ ጊዜ ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት ሲባል የተደጋጋሚነት መኖር የሚፈቀድ ቢሆንም አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ መደጋገሙ ግን ከማሰልቸቱም በላይ በዓ/ነገሩ አማካይነት እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ግልፅነት ያሳጣዋል:: ሆኖም ተጠኝ ተማሪዎቹ በፃፉዋቸው ድርሰቶች ውስጥ የዚህ ዓይነቱ ችግር ሊታይ በመቻሉ የሚከተሉት ለአብነት ያህል ሊጠቀሱ ችለዋል (አባሪ 5 "ሐ"ን በገፅ 144 ይመልከቱ::)

- አንድ ተማሪ የወደፊት ምኞት ብዙ ነገር ይመኛል::
- ስራውን ከጀመርኩ በኋላ በተማርኩት ደንብ ስራውን መስራት እጀምራለሁ::
- ይህን ያህል ትብብር ይህን ያህል ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ ምድርን ለማጣራት
- የሰው ልጅ የወደፊት አላማ ልስተካከልላቸው የምቻለው በራሳቸው ጥሬትና አካባቢያቸውን በመልማት የወደፊት አላማቸው እንድሳካለቸውም ከህብረተሰቡ ጋር ተባብሬው ሰርተዋል::

እነዚህ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከስራቸው የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በተደጋጋሚነት የታዩ ናቸው:: ሆኖም አጣማሪዎቹን በመጠቀምና ዓ/ነገሩን እንደገና በማቀናጀት ተደጋጋሚነቱን ለማስወገድ ይቻላል:: ስለሆነም በሚከተለው ሁኔታ ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናል::

"አንድ ተማሪ ለወደፊቱ ብዙ ነገር ይመኛል":: "በተማርኩት ደንብ መሰረት ስራውን መስራት እጀምራለሁ::" "ይህንን ያህል ትብብርና ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ ምድርን ለማጥፋት ነው::" "የሰው ልጅ የወደፊት ዓላማ ሊሳካ የሚችለው ሰዎች በአንድ ላይ ተባብረው አካባቢያቸውን ሲያለሙ ነው::" ወይም "ሰዎች የወደፊቱ ዓላማቸው እንዲሳካላቸው በማሰብ አካባቢያቸውን ለማልማት በአንድ ላይ ተባብረው ሰርተዋል::..."

### 4.1.3 <u>የቋንቋ አወቃቀር ስህተት</u>

በሠንጠረዥ 4 በቀረበው የጥናቱ መረጃ መሠረት በዓቢይ የስህተት ዓይነትነት ከተመደቡት አምስት ስህተቶች መካከል በ2ኛ ደረጃ የሚገኘው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው:: በአጠቃላይ የናሙና ድርሰቶቹ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 1920 ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን በመቶኛ 19.56 ነው:: አማካይ የስህተቱ መጠን 4.36፣ አማካይ ስህተት ድግግሞሽም 5.31 ሆኗል::

ማንኛውም ድርሰት የሚገነባው ከዓ/ነገር ጀምሮ ነው:: ስሜትን ወይም ሀሳብን ስፋትና ጥልቀት ባለው ሁኔታ በማስተላለፍ መግባባት የሚቻለው በዓ/ነገር አማካይነት በመግለፅ ነው:: በፅሁፍ የሚገለፅ ሀሳብም በማያሻማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ሊተላለፍ የሚችለው ስዋሰዋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ሲፃፍ ነው:: ፅህፈት ከንግግር የሚለየው በቋንቋ አወቃቀር ደንብ በመሆኑ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን ጠብቆ ለመፃፍ የቋንቋ አወቃቀር ደንብን ማወቅ የግዴታ ይሆናል:: /ዊዶውሰን፣ 1979:118ና ኖሪሽ 1990:65-6/

ስለዚህ የቋንቋ አወቃቀር ደንቡን ጠብቆ ለመፃፍ የመዋቅሩ ስሙሙነት የተጠበቀ መሆን ይኖርበታል::

በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት ዓይነት ውስጥ የዓ/ነገር ስሙሙነት፣ የአጣማሪዎች አጠቃቀም እንዲሁም የመስተአምር፣ የመስተዋድድና የተሳቢ አገባብ ንዑሳን የስህተት ዓይነቶች ተነስተዋል::

#### 4.1.3.1 የዓ/ነገር ስሙሙነት

ይህ ንዑስ የስህተት ዓይነት ምድብ በቋንቋ አወቃቀር ስህተትነት ከተነሱት ንዑሳን ክፍሎች መካከል የቀዳሚነቱን ስፍራ የያዘ ነው:: በአጠቃላይ በተፃፉት ድርሰቶች ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 884 ያህል ተቆጥሮበታል:: ይህም በመቶኛ 9 አማካይ የስህተት መጠን 2 እና አማካይ የስህተት ድግግሞሹም 2.45 ነው:: በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች የቁጥር የፆታ የጊዜና የመደብ ስምምነት ስህተቶች ሲሆኑ ለአብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል::

ሀ) የቁጥር ስሙሙነት

- ይህንን ለማስወገድ ቀላል ዘዴ አሉ
- ከዚያም ደግሞ ህፃኖቻቸው ያሳድጉትና
- ግን ከዚያም በፊት የምደረጉ ዝግጅቶች መኖር አለበት
- የፆታ ትምህርት አለመሰጠቱ ብዙ በሽታዎች ሰው እያጠቃ ነው::
- የገጠር ህዝብ በጣም ችግረኞች ስለሆኑ ልጆቹን ወደ ከተማ ወስዶ ማስተማር ስለማይችል ... ልጆቹን ሳይስተምሩ መሀይም ሆኖ ያስቀራሉ
- የፈተናው ቀን አንድ ሳምንት ሲቀር የትምህርት ዓይነቶች ተጠንተው ማለቅ አለበት::

እነዚህ ለቁጥር ስምምነት ስህተት የቀረቡት ምሳሌዎች በሚከተለው ዓይነት ቢስተካከሉ የተሻለ ሊሆኑ ይችላሉ::

"ይህንን ለማስወገድ ቀላል ዘዴ አለ::" "ከዚያም ደግሞ ህፃኖቻቸውን ሊያሳድጉአቸውና ...::" "... ግን ከዚያ በፊት የሚደረጉ ብዙ ዝግጅቶች መኖር አለባቸው::" "የፆታ ትምህርት ባለመሰጠቱ ብዙ በሽታዎች ሰዎችን እያጠቁ ነው::" "የገጠር ህዝቦች በጣም ችግረኞች ስለሆኑና ልጆቻቸውን ወደ ከተማ ልከው ማስተማር ባለመቻላቸው መሀይም አድርገዋቸው ቀሩ" ወይም "የገጠር ህዝብ በጣም ችግረኛ ስለሆነ ልጆቹን ወደ ከተማ ልኮ ባለማስተማሩ ማሀይም ሆነው ቀሩ::" "ለፈተናው ቀን አንድ ሳምንት ሲቀር የየትምህርቱ ዓይነቶች ተጠንተው ማለቅ አለባቸው" ወይም "ለፈተናው አንድ ሳምንት ሲቀር እያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ተጠንቶ ማለቅ አለበት::"

ለ. <u>የዖታ ስሙሙነት</u>

- አንድ ታላቅ እህተ ሁልጊዜ .... አታጠናም ይሻልሃል ወዮልህ ትወርቅና ...ትለኝ ነበር፡፡ እኔ የዛን ጊዜ ጠለቅ ብዬ ስለማላውቅ <u>የሱ</u> ምክርና <u>የሱ</u> ቁጣ ምንም አይመስለኝም ነበር፡፡
- አባትየው ወደውጭ ስወጣ ከበደች በሩጨ ወደቤት ገባች፡፡ ደራርቱም! ምን አጠፋሽ ዛሬ ደግሞ አለችው፡፡
- ከበደች ኮቦት ለቀማ ስትሄድ ከአንድ ልጅ ጋር እያወራች በምትሄድበት ጊዜ ቶላ ከጋራ ቤት ወጥቶ ብቅ አለበት፡፡
- ... ውብነሽ የምትባል ልጅ ነበረች፡፡ በጣም ወደድኩት፡፡ ወደድኩሽ ብዬ ልነግራት አልቻልኩም በጣም ይፈራ ነበር፡፡
- ለሰው ልጅ መሰረቱ እናት ከመሆኑ የተነሳ ማንኛውም ፍጡር ያለአባት ያለእናት መገኘት አይችሉም፡፡

በእነዚህ በዖታ ስምምነት ስህተት በተነሱት ዓ/ነገሮች ውስጥ ተጠኚ ተማሪዎቹ የአንስታይ ዖታ አመልካች ምዕላድን ባለመጠቀማቸው የድርጊት ባለቤት የሆኑትን ሴቶች በተባዕታይ ዖታ ሊጠሩዋቸው ችለዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዓ/ነገሮች እንደሚከተለው ቢስተካከሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

“አንዲት ታላቅ እህቴ ሁልጊዜ ... አታጠናም ትወድቅና ወዮውልህ!... ትለኝ ነበር፡፡” “እኔ ግን ጠለቅ ብዬ ስለማላውቅ የሷ ምክርና ቁጣ ምንም አይመስለኝም ነበር፡፡” “አባትዬው ወደ ውጭ ሲወጣ ከበደች በሩጫ ወደ ቤት ገባች፡፡” “ደራርቱም አንቺ ዛሬ ደግሞ ምን አጠፋሽ?!” አለቻት፡፡ “ከበደች ከአንድ ልጅ ጋር እያወራች ኩበት ለቀማ በምትሄድበት ጊዜ ቶላ ከጎረቤት ወጥቶ ብቅ አለባት፡፡” “ውብነሽ የምትባል ልጅ ነበረች፡፡ በጣም ወደድኳት፡፡ በጣም እፈራ ስለነበር ወደድኩሽ ብዬ ልነግራት አልቻልኩም፡፡” “ለሰው ልጅ መሰረቱ እናቱ በመሆኗ ማንኛውም ፍጡር ያለእሷ መገኘት አይችልም...”

ሐ. <u>የጊዜ ስሙሙነት</u>

- ... ከዩኒቨርሲቲ ተመርቄ በተሰጠን የስራ ድርሻዬ በተሰቦቼን <u>የረዳኋቸውን</u> እመኛለሁ፡፡

- ... እኔ ሀኪም ብሆን ኑሮ ለቤተሰቦቼም ሆነ ለእናት ሀገሪቱ <u>ጠቅሜያለሁ</u> ነበር፡፡
- ስለዚህ የወደፊት ምኞቴ ዶክተር <u>ነበር በማለት</u> እገልፃለሁ፡፡
- የሰው ልጅ የወደፊት ዓላማ ልስተካከልላቸው የምቻለው በራሳቸው ጥሬትና አካባቢያቸውን በመልማት የወደፊት ዓላማቸው ከህብሬተሰቡ ጋር ተባብሬው <u>ሰርተዋል</u>፡፡

ከእነዚህ መረጃዎች መገንዘብ እንደተቻለው ተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሚፅፉበት ጊዜ ስህተት ሊፈፅሙ የቻሉት ድርጊቱ የተፈፀመበትን ወይም የሚፈፀምበትን ጊዜ በአግባቡ ሊገልፁ ባለመቻላቸው ነው፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያው ዓ/ነገር ሲታይ ተማሪው ከዩኒቨርስቲ ከተመረቀ በኋላ ባለው አቅም ቤተሰቦቹን ለመርዳት የመመኘት ፍላጎት ያለው መሆኑን ሲገልፅ ድርጊቱ ገና ወደፊት የሚፈፀም እንጂ ያለፈ አይደለም፡፡ ሆኖም ... "የስራ ድርሻዬ ቤተሰቦቼ የረዳኋቸው" ማለቱ ደግሞ ድርጊቱ የቆየ፣ የተፈፀመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የተፈፀመውን ድርጊትና ጊዜ፣ የሚፈፀመውን ድርጊትና ጊዜ ወይም በመፈፀም ላይ ያለው ድርጊትና ጊዜን የሚያመለክቱ ቃላት ተጣጥመው በስርዓት ባለመቀናጀታቸው ስህተት ሊፈፀም ችሏል፡፡ ስለዚህ ከስራቸው የተሰመረባቸው ቃላት በሚከተለው መንገድ ተስተካክለው ቢፃፉ ዓ/ነገሩ ሊቃና ይችላል፡፡

"ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ በማገኘው ገንዘብ ቤተሰቦቼን ለመርዳት እመኛለሁ፡፡" ወይም "ከዩኒቨርስቲ ከተመረቅሁ በኋላ የኔ የስራ ድርሻ ቤተሰቦቼን መርዳት ነው፡፡" እኔ ሀኪም ብሆን ኖሮ ለቤተሰቦቼም ሆነ ለእናት ሀገሬ እጠቅም ነበር፡፡" "ስለዚህ የወደፊት ምኞቴ ዶክተር ለመሆን ነው፡፡" "የሰው ልጆች የወደፊት ምኞት ሊሳካ የሚችለው በራሳቸው ጥረት ከህብረተሰቡ ጋር ተባብረው ሲሰሩ ነው ወይም የሰው ልጆች ምኞት ሊሳካ የሚችለው ከህብረተሰቡ ጋር ተባብረው በመስራት ሲያለሙ ነው፡፡"

መ. <u>የመደብ ስሙሙነት</u>

- ከዚህም በተረፈ በዚያን ወቅት በሥርዓት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይዞ <u>አዘጋጅተን</u> መሄድ

- ... ከዚያም ደግሞ ህፃኖቻቸውን በጥሩ ሁኔታ ያሳድጉትና ራሳቸውን እስከቻሉ ድረስ በስነ ሥርዓት እያንከበከቡ ምንም አደጋ እንዳይደርስባቸው ታንከበክባለህ
- ... የወደፊት ምኞት ተማሪዎች ትምህርትን በደንብ ተከታትሎ ለጥሩ ውጤት የሚያበቃ ከሆነ ለወደፊት ክስተቶች ልመኝ ስለምችል ነው፡፡

እነዚህ የመደብ ስምምነት የሌላቸው ዓ/ነገሮች በሚታዩበት ጊዜ ስህተቱ የመደብ አለመስማማት ችግር ብቻ ሳይሆን የፅንስ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተትም ያለበት ነው፡፡ ሆኖም ይህ በሚመለከተው ስፍራ ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለፁት ዓ/ነገሮች በሚታዩበት ጊዜ በመጀመሪያው ዓ/ነገር ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና አንደኛ መደብ የብዙ ቁጥር፣ በሁለተኛው ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ስሞችን፣ በሶስተኛው ዓ/ነገር ሶስተኛና አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስሞችን የሚያመለክቱ ቃላትን በመጠቀም የዓ/ነገሩ ባለቤት ሁለት የተለያዩ ሰዎች እንደሆኑ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ዓ/ነገሮች በሚከተለው መንገድ ቢስተካከሉ የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡

“ከእዚህ በተረፈ በዚያ ወቅት የሚያስፈልጉ ነገሮችን በሥርዓት አዘጋጅቶ ይዞ መሄድ ተገቢ ነው፡፡” “...ከዚያም በህፃኖቻቸው ላይ ምንም አደጋ እንዳይደርስባቸው በጥሩ ሁኔታ ይንከባከባሉ፡፡” “ትምህርቴን በደንብ ተከታትዬ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ከበቃሁ ለወደፊቱ ብዙ ነገሮችን ልመኝ እችላለሁ፡፡”

#### 4.1.3.2 <u>የመስተአምር የመስተዋድድና የተሳቢ አገባብ ስህተት</u>

በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ካሉት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች መካከል በሁለተኛ ደረጃ የተገኙት የመስተአምር፣ የመስተዋድድና የተሳቢ አገባብ ስህተቶች ሲሆኑ እነዚህም በጥናቱ ከተቆጠረው ከአጠቃላዩ ስህተት ውስጥ 764 ያህሉን ይዘዋል፡፡ የእነዚህ ስህተቶች መቶኛ 7.78፣ አማካይ ስህተቱ 1.74 እና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ 2.11 ነው፡፡

ሀ. <u>የመስተአምር አገባብ</u>

ተማሪዎቹ መስተአምርን በሚጠቀሙበት ጊዜ ስህተት ይፈፅማሉ፡፡ አፈፃፀማቸውም ያለቦታው በመጠቀም ወይም ተገቢ በሆነ ቦታ ደግሞ በተሳሳተ ሁኔታ በማስገባት ነው፡፡ ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡-

- የፈተናው ሰሞን ሲያልፍ ደግሞ ያንን <u>ልጅ</u> እንደዚያ የለመነችው የእግዚያብሄር ሰላምታ አትጠይቅም፡፡
- በዚህ በአካባቢያችን <u>አንድ</u> የተለመዱ የኋላቀር አስተሳሰቦች አሉ፡፡ <u>ይህም</u> ቃላት በፆታ ተለይቶ የሚነገሩ አነጋገሮች ናቸው፡፡

ከነዚህ ከተሰመረባቸው መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በመጀመሪያው ዓ/ነገር አላስፈላጊ የመስተዓምር ቅጥያ ተጨምሮበት "ልጅ" መሆን የሚገባው "ልጁ" ሊሆን ችሏል፡፡ በሁለተኛው ዓ/ነገር ደግሞ ከአራት ነጥብ ቀጥሎ መግባት ያለበት የብዙ ቁጥር አመልካች የሆነው "እነዚህም" የሚለው ሲሆን "ይህም" የሚለው በተሳሳተ ሁኔታ ሊገባ ችሏል፡፡ የማብዛት ምልክት የሆነው ቁጥርም አንዳንድ መሆን ሲገባው "አንድ" ሆኗል፡፡ ስለዚህ "ያንን ልጅ እንደዚያ የለመነችውን ያህል ፈተናው ሲያልፍ የእግዚአብሄር ሰላምታ አትሰጠውም፡፡" "በአካባቢያችን አንዳንድ የተለመዱ ኋላቀር አስተሳሰቦች አሉ፡፡ እነዚህም በፆታ ተለይተው የሚነገሩ አነጋገሮች ናቸው፡፡ ወዘተ" ተብሎ በዚህ ወይም በሌላ መንገድ ቢስተካከል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

ለ. <u>የመስተዋድድ አገባብ</u>

... በዚህ አይነቱ ከላይ <u>እንደበተጠቀሰው</u> አሰተማሪው በሚያስተምርበት ጊዜ ...

- አንድ ተማሪ <u>የ</u>ወደፊት ብዙ ነገር ይመኛል፡፡
- በተማሪነት ደረጃ ብዙ <u>አ</u>ለማስተዋል ት/ቤት ውስጥ ብዙ ጥፋቶች ሊጠፉ ይችላሉ፡፡
- ... ሰነፉ ግን መቅበጥበጥ ይጀምራል <u>ወደመልስፍለጋ</u> ካገኘም አገኘ ካላገኘም የሆነ ያልሆነውን ሞልተው ይወጣሉ
- ... አንድ ላይ በሚቀመጡበት ጊዜ <u>ከ10ኛ ክፍል ተማሪ ላይ</u> 8ኛ ክፍል የሆነው ተማሪ ይፅፍለታል፡፡

- ይህ በሽታ በሀገራችን በ1968 በአ.አ. መገኘቱ ብዙ መፅሀፎች ያስረዳሉ
- ለምሳሌ በግብርና ትምህርት ሆኖ የተመረቅኩኝ ለም አፈራችን በጎርፍ ተሸርሽሮ ወደሌላው እንዳይሄድ ችግኝ መትከል፣ እርከን መስራት ... የራሴን የወደፊት ምኞት እገልፃለሁ

ከላይ እንደሚታየው ተጠኝ ተማሪዎቹ በመሰረቷቸው ዓ/ነገሮች ውስጥ በመስተዋድድ አጠቃቀም በኩል የተለያዩ ስህተቶችን ፈፅመዋል፡፡ ይኸውም ከተለመደው የቋንቋው አገባብ ውጭ ሁለት መስተዋድዶች በአንድ ላይ በማስገባት፣ መግባት በነበረበት ቦታ በመግደፍ (በመተው) ወይም አንዱ በሚገባበት ቦታ ሌላውን በማስገባት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ከላይ የተሰመረባቸው ስህተቶች ተወግደው ዓ/ነገሩ ቢፃፍ የሚከተለውን ሊመስል ይችላል፡፡ "... በዚህ ዓይነት ከላይ እንደተጠቀሰው አስተማሪው በሚያስተምርበት ጊዜ ..." "... አንድ ተማሪ ለወደፊት ብዙ ነገር ይመኛል፡፡"

"... በተማሪነት ደረጃ ብዙ ካለማስተዋል የተነሳ በት/ቤት ውስጥ ብዙ ጥፋቶች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡" "አንድ ተማሪ ለወደፊት ብዙ ነገር ይመኛል፡፡ ... ሰነፍ ግን መልስ ፍለጋ መቅበጥበጥ ይጀምራል፡፡ ካገኘም አገኘ ካላገኘም የሆነ ያልሆነውን ሞልቶ ይወጣል፡፡" "በአንድ ላይ በሚቀመጡበት ጊዜ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ለ8ኛው ክፍል ይፅፍለታል፡፡" "ይህ በሽታ በ1968 በሀገራችን በተለይም በአ.አ. ስለመገኘቱ ብዙ ፅሁፎች ያስረዳሉ፡፡" "ለምሳሌ በግብርና ትምህርት የተመረቅኩ ቢሆን ኖሮ እርከን በመስራት፣ችግኝ በመትከል ... ለም አፈራችን በጎርፍ ተሸርሽሮ ወደ ሌላው እንዳይሄድ አደርግ ነበር፡፡"

## ሐ. <u>የተሳቢ አገባብ</u>

በሚከተሉት ዓ/ነገሮች ውስጥ የተሳቢ አገባብ ስህተቶች የተፈፀሙ ሲሆን ስህተት ያለበትን ስፍራ ለመጠቆምም በቅንፍ ( ) ተመልክቷል፡፡

- ከነዚህም ውስጥ ልዷ ( ) ከብዙ ዓይነት አደጋ ለማዳን ጠቃሚ ምክሮችን ትለግሳለች፡፡
- የተማረ ሰው ጠፍቶ አይጠፋምና እውቀቴን ወደ ተግባር በማዞር አገር ቤት ሄጄ እርሻዬ ) በጥሩ ሁኔታ እቀጥላለሁ፡፡
- በመቀጠልም ያንን መከረኛ ጎበዝ ተማሪ (ን) ማስፈራራት ይጀምራሉ፡፡

- እኔ ዶክተር ( ን ) እሆናለሁ ብዬ የምገምተው ለደመዙ ብቻ ሳይሆን የሚሰራውን የሱን ስራ ብቻ ነው፡፡
- ለ12ኛ ማለቂያ ፈተና ላይ ቆንጆ ውጤት አምጥቼ ሥራ(ን) ለመያዝ እችላለሁ፡፡

ከመረጃዎቹ መረዳት እንደተቻለው ተጠኝ ተማሪዎቹ ተሳቢዎቹን በሚጠቀሙብት ጊዜ መግባት ባለባቸው ቦታ ላይ የመግደፍ፣ አላስፈላጊ በሆነው ቦታ ደግሞ የመጨመር ሁኔታ ታይቷል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ዓ/ነገሮች እንደሚከተለው ቢፃፉ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

"... ከነዚህም ውስጥ ልጇን ከብዙ ዓይነት አደጋ ለማዳን ጠቃሚ ምክሮችን ትለግሳለች፡፡" "የተማረ ሰው ወድቆ አይወድቅምና ዕውቀቴን ወደ ተግባር ለመለወጥ ሀገር ቤት ሄጄ እርሻዬን በጥሩ ሁኔታ እቀጥላለሁ፡፡" "በመቀጠልም ያንን መከረኛ ኅበዝ ተማሪ ማስፈራራት ይጀምራሉ፡፡" "እኔ ዶ/ር እሆናለሁ ብዬ የምገምተው ለደመወዙ ብቻ ሳይሆን ለሙያውም ጭምር ነው፡፡" "በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና ጥሩ ውጤት አምጥቼ ስራ ለመያዝ እችላለሁ፡፡"

#### 4.1.3.3 <u>የአጣማሪዎች አገባብ</u>

በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ከተነሱት አንዱ የአጣማሪዎች አጠቃቀም ነው፡፡ በአጣማሪዎች አጠቃቀም የተፈፀመው ስህተት ብዛት 272 በመቶኛ 2.77፣ አማካይ ስህተቱ 0.61፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 0.75 ሊሆን ችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህልም፡-

- <u>ይሁን እንጂ ነገር ግን</u> የወደፊቱ ምኞቱ ዶክተር ለመሆን እፈልጋለሁ
- <u>ይሁን እንጂ ቢሆንም</u> እኔ ደግሞ በበኩሌ ት/ቤት ገብቼ መማርን ጀምሬ መመኘትን ጀምሬ እንደነበር የአእምሮዬ ከፍል ይመሰክራል፡፡
- በገጠር አካባቢ ከሰኔ እስከጥር ሰዎች ከብቶቻቸውን ይጠብቃሉ፡፡ <u>ያንን</u> ከብቶች የሚጠብቀው ልጆች ሲሆን እድሜያቸው ከስድስት እስከ 12 ያላቸው ልጆች ናቸው፡፡
- ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን <u>ነገር ግን</u> በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ማስተዋል እንዳሌባቸው ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

- ከነዚህም ችግሮች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ፡፡ እርሱም ሀገራችን መሌት እትዮጵያ በአብዛኛው የሚተዳደረው በግብር ነው፡፡

እነዚህ ከስራቸው የተሰመረባቸው አጣማሪዎች በሚታዩበት ጊዜ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓ/ነገሮች ውስጥ "ይሁን እንጅ"፣ "ነገር ግን"ና "ይሁን እንጅ" "ቢሆንም" የተባሉት በአንድ ላይ በመግባታቸው፣ በሌሎቹ ዓ/ነገሮች ውስጥ ያሉት ደግሞ ከቀረበው የዓ/ነገሩ ዓውደ ንባብ ውጭ በመግባታቸው ስህተቱን ሊያመጡ ችለዋል፡፡ ስለዚህ እንደሚከተለው ቢስተካከሉ ሳይሻል አይቀርም፡፡

"ይሁን እንጅ ለወደፊት ዶክተር ለመሆን እፈልጋለሁ፡፡" "ይሁን እንጅ እኔ ደግሞ ትምህርት ቤት ገብቼ ለመማር ተመኝቼ እንደነበር ህሊናዬ ይመሰክራል፡፡" "ገጠር አካባቢ ... ከብቶቻቸውን ይጠብቃሉ፡፡" "እነዚህንም ከብቶች የሚጠብቁት ከስድስት - አሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች ናቸው፡፡" "ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎቹ እንዲያስተውሉ ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡" "ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ፡፡" "ለምሳሌ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትተዳደረው በግብርና ነው፡፡"

### 4.1.4 የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም

መደበኛ የሆነ የሥርዓት ነጥብ አጠቃቀም ባይኖርም በፅሁፍ የሚቀርብን ሀሳብ በዓ/ነገሮች ከፋፍሎ ለማቅረብ፣ የዓ/ነገሩ ሀሳብ መቋጨቱን ለማመልከት፣ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት፣ የዓ/ነገሩ ሀሳብ ጠያቂ ወይም ሀሳብ ሰጭ መሆኑንና በፅሁፉ ውስጥ የተገለፀው ሀሳብ የራስ አለመሆኑን ለማመልከት ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት አለው፡፡ ስለዚህ ፀሀፊው የፃፈውን ነገር አንባቢያን እንዲረዱለት ለማድረግ በተገቢው ቦታ ሥርዓት ነጥቦችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ካልሆነ ግን የአንባቢያንን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ ይችላል /ሺልና አሙጇዋ፣1985:34፤150፤ ዴይ፤1984:137/

በዚህ ጥናት ውስጥ በስህተትነት ከታዩት አቢይ የስህተት ዓይነት ምድቦች መካከል አንዱና በሶስተኛ ደረጃ ከፍተኛ ስህተት የታየበት የሥርዓት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተተኮረባቸው በአብዛኛው

በተደጋጋሚ በግልጋሎት ላይ የሚውሉት አራት ነጥብና ነጠላ ሰረዝ ሲሆኑ እነሱንም እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### 4.1.4.1 <u>አራት ነጥብ</u>

በሠንጠረዥ 4 በገፅ 47 በቀረበው መረጃ መሰረት በአራት ነጥብ ንዑስ የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ 1492 ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ድርሰቱ ውስጥ ከተፈፀሙት ስህተቶች አንፃር ሲታይ 15.20% ሊሆን ችሏል፡፡ አማካይ የስህተቱ መጠን 3.39 ና የስህተት ድግግሞሹም 4.13 ነው፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ይመልከቱ)

ሀ. በተገቢው ቦታ አራት ነጥብ ባለመጠቀም የሚፈፀም

እናት ለልጇ የምታስበው ብዙ ነው ( ) ልጅ ግን እንደ እንደ እናት አያስብም ( ) ልጇ ወደ ውጭ ሲወጡ ከሰው ጋር የሚጋጩ እየመሰላት ብዙ ነገር ታስባለች ( ) የእናት ጥቅም ብዙ ነው ( ) ይሁን እንጅ እናት ለልጅዋ እንደምታስበው ደግሞ አባት የእናት ያህል ለልጆቹ አያስብም ( ) እናት ለልጇ የምትሰጠው ጥቅም ብዙ ነው ( ) ለምሳሌ ልጇ ምናልባት ፍታቸው ያልፀዳ እንዳሆነ ፍታቸውን እያየች የተራቡና የተጠሙ እየመሰላት ብዙ ነገር ታስባለች ( )...

በቀላሉ ከላይ ከተጠቀሰው አንቀፅ ውስጥ ብቻ 7 ያህል የአራት ነጥብ ስህተቶች የተቆጠሩ ሲሆን ስህተቱ ያለበትን ቦታ ለመጠቆም የቅንፍ ምልክቱ ገብቷል፡፡

ለ. አራት ነጥብ በመጠቀም ፋንታ የእንግሊዝኛውን ሥርዓት ነጠብ በመጠቀም የሚፈፀም

የመተለፊኛ ሁኔታና የመጥኛ ምልክት በክተርያ ሳይሆን በዓይን የመታየት ... ልታይ በማይችል ጥቃቅን በይረስ ነው (.) ይህ ባይረስ ልታይ የሚችለው በዓይን ሳይሆን በማስከረስኮብ ማሰር ነው (.) የመተለፉበት ዘዴ አንድ በአንድ ተወስነው ያልኖሩትን በሁለቱ ያታዎች መሀከል ነው (.)

ሐ. በአራት ነጥብ ፋንታ ሁለት ነጥብ በመጠቀም የሚፈፀም

... ፈተና ላይ ለመቀመጥ እየፈሩ አመመኝ ብለው ቤተሰብ እያታለሉ ቤት የምተኛ ተማሪዎችም አይታጡም: መቸም ያጠነው ተማር ፋተን ቀረበ ስቡል ልቡ ምንም ያክል አይደነግጥም: ያላጠናው ግን የምይዘውን የምለቀውን እያጠ ይርበተበታል:

ከላይ በ"ሀ" የተመለከቱት ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ የአራት ነጥብን ጠቀሜታና አገባብ ካለመገንዘብ የተነሳ ነጥቡ ሊገባበት በሚችለው ቦታ በቅንፍ እንደተመለከተው ምንም ባለማስገባት፣ በ"ለ" የተመለከተው የእንግሊዝኛውን ቋንቋ ሥርዓተ ነጥብ ከአማርኛው ጋር በማጋጨት ለአማርኛው አራት ነጥብ አቻ በመፈለግ በቅንፉ እንደተመለከተው አንድ ነጥብን በመጠቀምና በ"ሐ" የተመለከተው ደግሞ በአራት ነጥብ ፋንታ ሁለት ነጥብን በመጠቀም ሊፈፀሙ ችለዋል:: ስለሆነም እነዚህ ስህተት ተፈፅሞባቸዋል ተብሎ በተመለከቱት ቦታዎች አራት ነጥብ ቢገባ ሊስተካከል ይችላል::

### 4.1.4.2 ነጠላ ሰረዝ

በጥናቱ በቀረበው መረጃ መሰረት 410 የነጠላ ሰረዝ ስህተቶች ተፈፅመዋል:: በአጠቃላይ በድርሰቱ ውስጥ ከተፈፀሙት ስህተቶች አንፃር ሲታይም በመቶኛ 4.18 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.93 እና አማካይ የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 1.13 ሆኗል:: ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል:: (ዝርዝሩን በአባሪ 9 ገፅ 153 እና 154 ይመልከቱ::)

"... እንድሁም ከወንድ ወደ ሴት የምተላለፍበት ዘዴ በግብረስጋ ግንኙነት, ባልተቀቀለ መርፌ መወጋት, በጥርስ ማስነቀል ጥንቃቄ ያልተደረገ ብረት መጠቀም, እንጥል በማስቀረጥ, በአንድ ምላጭ በመጠቀም ስሆን ሰው በመሳሳም አብረው በመብላት አይተላለፍም."

"... የተባበሩት መንግሥታት ርዳታ ኮሚሽነርም በተከሰተው ጉዳይ የመርዳት ወይም ርዳታ የመስጠት ግድ አለበት. በተለይ በሀገራችን በደቡብ ኢትዮጵያ ብዙ ንብረት አውድሟል, የመኪና መንገድ አበላሽቷል, ሰብል አውድሟል , የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ በአካባቢው ያሉትን የወንጂ ሸንኮራና

ሌሎችን ልማቶች ከጥቅም ውጭ አድርጓል, ብዙ ሰዎችን ያለመጠለያ አስቀርቷል, የብዙ ሰዎችን ህይወት አጥፍቷል፡፡ ብዙ ሰዎችን ለረሀብ ዳርጓል, በሄሊኮፕተር እንኳን ለመርዳት በጣም አስቸጋሪ ነበር ..."

"በዚያን ወቅት ከፊተኝ መምህር ጋር ያምጣሉ ተማሪዎች በርከት ናቸው፡ እዚህ አልቀመጥም፡ ይህ ወረቀት ማስደገፊያ ነው፡ ይገፔ ልፊተን፡ ደብተር ላስደግፍ፡ መሰቢያ ልያዝ ምኑ ቅጡ ብቻ ፊታኝ መምህርና ሰነፍ ተማሪ በጣም ይጨቃጨቃሉ"

ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት የተቻለው በነጠላ ሰረዝ ፋንታ የእንግሊዝኛውን ኮማ በማስገባት፣ በተገቢው ቦታ መግባት ያለበትን በመተውና በተሳሳተ መንገድ ሁለት ነጥብ በመጠቀም ስህተቱ ሊፈፀም እንደቻለ ነው፡፡ ስለዚህ በነዚህ ከላይ በቀረቡት አጠቃቀሞች ሳቢያ የተፈፀመውን ስህተት ለማስተካከል የእንግሊዝኛውን ስርዓት ነጥብና ሁለት ነጥብ አስወግዶ ነጠላ ሰረዙን በመጠቀም እንደሚከተለው ማስተካከል ይቻላል፡፡

"... እንዲሁም የመተላለፊያው መንገድ በግብረስጋ ግንኙነት፣ ባልተቀቀለ መርፌ በመወጋት፣ ጥንቃቄ ባልተደረገለት ብረት በመጠቀምና እንጥል በማስቀረጥ፣ ባልተቀቀለ ምላጭ በመጠቀም ሲሆን በመሳሳምና አብሮ በመብላት ግን አይተላለፍም፡፡"

"... የተባበሩት መንግሥታት የእርዳታ ኮሚሽነርም ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ዕርዳታ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ በተለይ በሀገራችን በደቡብ ኢትዮጵያ ብዙ ንብረት አውድሟል፣ የመኪና መንገድ አበላሽቷል፣ ሰብል አውድሟል፣ የአዋሽ ወንዝ በመሙላቱ በአካባቢው ያሉትን የወንጂ ሸንኮራና ሌሎች ልማቶችን ከጥቅም ውጭ አድርጓል፣ ብዙ ሰዎችን ያለመጠለያ አስቀርቷል፣ የብዙ ሰዎችም ህይወት እንዲጠፋና ከሞት የተረፉትንም ሰዎች ለረሀብ እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡"

"በዚያ ወቅት ከፊታኙ መምህር ጋር የሚጣሉ በርካታ ናቸው፡፡ እዚህ አልቀመጥም፣ ማስደገፊያ ወረቀት ልያዝ፣ ደብተር ላስደግፍ፣ ማሰቢያ ልያዝ ... ምን ቅጡ ብቻ ሰነፉ ተማሪና ፊታኙ መምህር በጣም ይጨቃጨቃሉ፡፡"

### 4.1.5 ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች

ለመለየት ያልተቻለ አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ተብሎ በስህተት ዓይነትነት ሊቆጠር የቻለበት ምክንያት የተለያዩ የስህተት ዓይነቶችን ይዞ በመገኘቱና በቀላሉ ስህተቱን ለይቶ ለማውጣት በማያስችል ሁኔታ ተዘበራርቆ በመገኘቱ ነው፡፡

ይህ የስህተት ዓይነት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች የሌሉት ሲሆን በጥናቱ ውስጥ በአቢይ ስህተትነት ከተመደቡት አምስት የስህተት ዓይነቶች መካከል በአራተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 9818 ስህተቶች ውስጥ 788 ያህሉን የሚሸፍን ሲሆን በአጠቃላይ ከተፈፀሙት ስህተቶች አንፃርም ሲታይ በመቶኛ 8.03፣ የአማካይ ስህተቱ መጠን 1.79 እና አማካይ ድግግሞሹም 2.18 ሊሆን ችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ (አባሪ 7ን በገፅ 149 እና 150 ይመልከቱ፡፡)

- እና ይህ የፈተና ሰሞን በእኛ አካባቢ ሳይሆን በሁሉም ነገር የሚከናወን መሆኑን ሃገርንም ሆነ ሰውን ሳይለይ እንደፈተናው ሁሉ ቀኑ (ሰሞኑ) ይጨንቃል
- ሁሉም ለእናተ ያስባል ለማለት በጣም ያስደፍራል፡፡ ስለሆነም ያሳለፋችሁ ጣጣ ሁሉ ለማስተዋል ለወደፊቱ ትውልድ ማስተዋል በጣም አስፈለግ ነው፡፡
- ከዝያን በኋላ በኳለጅ እንድ እንደስኩ ቤተሰቦቻችንና አገራች በከፍተኛ ደረጃ እንደደረሱና እኔም በራሴ ከፍተኛ ስራ ይዜን ከፍተኛ ጥቅም እንደነገኝ በልባች ከግዝሄቤር ጋር ከፍተኛ ምኞት በልበ አለው
- መምህር ለመሆን ይመኛለሁ፤ ስለሆነም ብዙ እውቀቶች መምህራኖች ለማያካፍሉት እኔ ደግሞ አሁን መምህራን በኩል ብዙ ችግር ስላለበት ለሚመጡት ተወላጆች እንደዚህ ዓይነት ችግሮች እንዳይጋጠሙ ለዚህ ስራ መስክ ለመሰማራት ይፈልጋለሁ
- ፈተና ሰሞን ለመምጣት የራቀ ከሆነ ተማሪው ቶሎ እንደማይመጣና ቢመጣም እንደሚሰራው ሁሉ ሽላ ብሎት ልክ የፈተና ሰሞን ስደርስ ቀን ከለሊቱ የቱን ሰርቶ እንደሚተው ያሳጣዋል፡፡

### 4.1.5 ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች

ለመለየት ያልተቻለ አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ተብሎ በስህተት ዓይነትነት ሊቆጠር የቻለበት ምክንያት የተለያዩ የስህተት ዓይነቶችን ይዞ በመገኘቱና በቀላሉ ስህተቱን ለይቶ ለማውጣት በማያስችል ሁኔታ ተዘበራርቆ በመገኘቱ ነው፡፡

ይህ የስህተት ዓይነት ንዑሳን የስህተት ዓይነት ምድቦች የሌሉት ሲሆን በጥናቱ ውስጥ በአቢይ ስህተትነት ከተመደቡት አምስት የስህተት ዓይነቶች መካከል በአራተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው፡፡ በአጠቃላይ በስህተትነት ከተቆጠሩት 9818 ስህተቶች ውስጥ 788 ያህሉን የሚሸፍን ሲሆን በአጠቃላይ ከተፈፀሙት ስህተቶች አንፃርም ሲታይ በመቶኛ 8.03፣ የአማካይ ስህተቱ መጠን 1.79 እና አማካይ ድግግሞሹም 2.18 ሊሆን ችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ (አባሪ 7ን በገፅ 149 እና 150 ይመልከቱ፡፡)

- እና ይህ የፈተና ሰሞን በእኛ አካባቢ ሳይሆን በሁሉም ነገር የሚከናወን መሆኑን ሃገርንም ሆነ ሰውን ሳይለይ እንደፈተናው ሁሉ ቀኑ (ሰሞኑ) ይጨንቃል
- ሁሉም ለእናተ ያስባል ለማለት በጣም ያስደፍራል፡፡ ስለሆነም ያሳለፉችሁ ጣጣ ሁሉ ለማስተዋል ለወደፊቱ ትውልድ ማስተዋል በጣም አስፈለግ ነው፡፡
- ከዝያን በኋላ በኳለጅ እንድ እንደስኩ ቤተሰቦቻችንና አገራች በከፍተኛ ደረጃ እንደደረሱና እኔም በራሴ ከፍተኛ ስራ ይዜን በከፍተኛ ደረጃ እንደደረሱና ... ከፍተኛ ጥቅም እንደነገኝ በልባች ከግዝሄቤር ጋር ከፍተኛ ምኞት በልበ አለው
- መምህር ለመሆን ይመኛለሁ፤ ስለሆነም ብዙ እውቀቶች መምህራኖች ለማያካፍሉት እኔ ደግሞ አሁን መምህራን በኩል ብዙ ችግር ስላለበት ለሚመጡት ተወላጆች እንደዚህ ዓይነት ችግሮች እንዳይጋጠሙ ለዚህ ስራ መስክ ለመሰማራት ይፈልጋለሁ
- ፈተና ሰሞን ለመምጣት የራቀ ከሆነ ተማሪው ቶሎ እንደማይመጣና ቢመጣም እንደሚሰራው ሁሉ ሽላ ብሎት ልክ የፈተና ሰሞን ስደርስ ቀን ከለሊቱ የቱን ሰርቶ እንደሚተው ያሳጣዋል፡፡

እነዚህ በምሳሌነት የቀረቡት ስህተቶች እንደሚጠቁሙት ዓረፍተ ነገሮቹ ውስብስብ ያሉ በመሆናቸው የየስህተት ዓይነቶቹን ለይቶ ለማውጣት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡

በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ፈተና በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በሁሉም አካባቢ እንደሚሰጥና ሁሉንም የሚያስጨንቅ መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል፡፡ እንደዚህም ከሆነ "ፈተና በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይወሰን በሁሉም አካባቢ የሚሰጥ ሲሆን በፈተናው ሰሞንም ፈተናው ብቻ ሳይሆን ቀኑም ጭምር ያስጨንቃል" ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ በሁለተኛው ዓ/ነገር ለመግለፅ የታሰበው ተቸግራና ተሰቃይታ ለምታሳድገው እናቱ ሁሉም ሰው እኩል እንደማያስብላትና ተተኪው ትውልድ ግን ቸል ሊለው የማይገባ እንደሆነ ለማሳሰብ ነው፡፡ ስለሆነም "ሁሉም ሰው ለእናቱ እኩል ያስባል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሆኖም ተተኪው ትውልድ ወደ ኋላ ዞር ብሎ እናቱ ያሳለፈቻውን ችግር መመልከት ይኖርበታል" ተብሎ ቢገለፅ ሊስተካከል ይችላል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው ዓ/ነገር ከኮሌጅ ከተመረቅኩ በኋላ ደህና ቦታ ደርሼ ቤተሰቦቼንና ሀገሬን ለመርዳት ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ ለማለት የታሰበ ይመስላል፡፡ እንደዚህ ከሆነ ደግሞ "ከኮሌጅ እንደተመረቅኩ ደህና ስራ ይዤ ቤተሰቦቼንና ሀገሬንም ለማሻሻል እመኛለሁ" ተብሎ ቢገለፅ ወይም በሌላ መንገድ ቢገለፅ ሳይሻል አይቀርም፡፡

በአራተኛ ደረጃ የቀረበው የመምህራን ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በየአቅጣጫው እውቀታቸውን እንዳያካፍሉ ችግር ስላስከተለ ይህንን ችግር ለመቀነስ እኔ መምህር ሆኜ እውቀቴን ለማካፈል እመኛለሁ የሚል ሀሳብ የያዘ ይመስላል፡፡ ስለሆነም "በመምህራን እጥረት ሳቢያ የሚከሰተውን ችግር ለመቀነስ መምህር ሆኜ እውቀቴን ለማካፈል እመኛለሁ" ቢባል ጥሩ ነበር፡፡

በመጨረሻ የቀረበው ዓ/ነገር አንዳንድ ተማሪዎች የፈተና ጊዜ የማይደርስ መስሏቸው እንደሚዝናኑና መድረሱንም ቢያውቁ እንኳን ችላ ብለውት ከቆዩ በኋላ ቀኑ ሲደርስ ግን የትኛውን አጥንተው የትኛውን እንደሚተውት ግራ የሚጋቡ መሆኑን የሚገልፅ ሀሳብ የያዘ ይመስላል፡፡ እንዲህም ከሆነ "አንዳንድ ተማሪዎች ፈተና የማይደርስ መስሏቸው ሲዝናኑ

ከቆዩ በኋላ የፈተና ጊዜ ሲደርስ የትኛውን አጥንተው የትኛውን እንደሚተውት ግራ ይጋባሉ" ቢሆን የተሻለ ይሆን ነበር።

4.1.6 <u>የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት</u>

በዚህ ጥናት ውስጥ የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተት ሲባል የቃሉን ትክክለኛ ፍቺ ካለማወቅ ወይም ቃሉ የያዘውን ፅንሰ ሀሳብ ካለመረዳት የተነሳ በተሳሳተ መንገድ በመጠቀም የሚመጣ ስህተት ማለት ነው።

ከጥናቱ በተገኘው መረጃ መሰረት በዓቢይ የስህተት ዓይነትነት ከተመደቡት ስህተቶች ውስጥ የመጨረሻውን ደረጃ የያዘ ሲሆን በአጠቃላይ በተጠኝ ተማሪዎቹ በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል 720 ያህሉን ይዟል። የስህተት መቶኛው 7.33 ሲሆን፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.64 እና የስህተት ድግግሞሹም 1.99 ነው። ለአብነት ያህልም የሚከተሉት ዓ/ነገሮች ቀርበዋል። (ከስር የተሰመረባቸው ስህተቱን የሚያመለክቱ ናቸው።) (ዝርዝር መረጃዎቹን በአባሪ 8 ገፅ 151 እና 152 ይመልከቱ።)

- <u>ፓይለት አብራሪ</u>፣ <u>ዶክትሬት</u>፣ <u>አስተማሪነት</u>፣ ተመራማሪ ለመሆን እፈልጋለሁ።
- ትምህርት የሰው ልጅ መሰረታዊ <u>የህይወት ኑሮ</u> ነው።
- የኤድስ በሽታ አሌማችንን እያንቀጣቀጠ ያለው <u>መንስዔው</u> የለለው በተቻለ መጠን የአለሞችን ህዝቦች በለው ዘዴ ተቅማችሁ መኖር ከኤድስ ነፃ መሆን ትችላላችሁ።
- ማንኛውም ሰው ሆነ ተማሪ አንድንድ ነገር ለመስራት ወይም ለመንገርም ሆነ ለመፃፍ ከፍተኛ የሆነ ማስተዋል <u>ይጠይቀዋል</u>።
- የማትሪክን ውጤት አጥጋቢ በማምጣት ወደ ሌላ <u>ካምፓስ ትምህርት</u> ቤት ለመግባት አስባለሁ።

በመጀመሪያው ዓ/ነገር እንዲገለፅ የታሰበው ጉዳይ ፓይለት፣ ዶክተር፣ አስተማሪና ተመራማሪ ለመሆን የፈለገ መሆኑን ይመስላል። ሆኖም ፓይለትና አስተማሪና አስተማሪነት ያላቸውን አብራሪ፣ ዶክተርና ዶክትሬት፣ እንዲሁም አስተማሪና አስተማሪነት ያላቸውን የፅንሰ ሃሳብ ልዩነት ካለመገንዘብ የተነሳ ፓይለት የሚለውን እንደሚበረው እንደ አውሮፕላኑ፣ አብራሪ የሚለውን ቃል እንደ ባለሙያ አድርጎ

ወስዶታል። አስተማሪነት ሙያውን የሚገልፅ ሲሆን የሙያው ባለቤት ግን አስተማሪ መባሉን ባለመረዳቱ ቃሉን መርጦታል። በዚህም የተነሳ ስህተቱ ሊፈፀም ችሏል። ስለዚህ "አውሮፕላን አብራሪ፣ ዶክተር፣ አስተማሪና ተመራማሪ መሆን እፈልጋለሁ" ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር።

በሁለተኛ ደረጃ በቀረበው ዓ/ነገር ውስጥ ትምህርት በሰው ልጆች ህይወት አኗኗር ላይ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል። ሆኖም ህይወትና ኑሮ እየተተካኩ የሚገቡ መሆናቸውን ካለመገንዘብ የተነሳ አንዱ ያንዱ ገላጭ እንደሆነ ተደርጎ በመቅረቡ ስህተቱ ሊፈፀም ችሏል። ስለዚህ ለመግለፅ የታሰበውን ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የቀረበው ስህተት ያለበት ዓ/ነገር "ትምህርት የህይወት ዋስትና ነው" ተብሎ ቢፃፍ የተሻለ ይሆናል።

በሦስተኛ ደረጃ በቀረበው ዓ/ነገር አማካይነት ማንኛውም ሰው ሆነ ተማሪ አንድ ነገር ከመስራቱ በፊት ማስተዋል ያለበት መሆኑን ለመግለፅ የታሰበ ይመስላል። እንደዚህም ከሆነ "ማንኛውም ሰው አንድን ነገር ከመስራቱ፣ ከመንገሩ ወይም ከመፃፉ በፊት ማስተዋል ይኖርበታል" ወይም "ማንኛውም ሰው አንድን ነገር ከመስራቱ፣ ከመንገሩ ... በፊት እንዲያስተውል ይጠበቃል" ቢባል የተሻለ ይሆናል። በመጨረሻ የቀረበው ዓ/ነገር የያዘው ሀሳብ በማትሪክ ፈተና አጥጋቢ ውጤት ካመጣ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ለመግባት ያሰበ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ሆኖም ተማሪዎች የሚማሩበትን የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ "ካምፓስ" እያሉ መጥራታቸው በተደጋጋሚ የሚሰማ በመሆኑ "ካምፓስ" የሚለውን ቃል እንደኮሌጅ ወይም ዩኑቨርስቲ ስም በመቁጠር በተሳሳተ መንገድ ሊጠቀምበት ችሏል። ስለዚህ "በማትሪክ አጥጋቢ ውጤት አምጥቼ ዩኒቨርስቲ ወይም ኮሌጅ ለመግባት እፈልጋለሁ" ተብሎ ቢፃፍ ሊስተካከል ይችላል።

## 4.2 የስህተት ምንጭ መላምቶች

ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ መግቢያ እንደተገለፀው በዚህ ክፍል ትኩረት የሚደረገው ሁለተኛውን መሠረታዊ የጥናት ጥያቄ ለመመለስ ነው:: በዚህ ጥናት ውስጥ በተጠኝ ተማሪዎቹ በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ የተፈፀሙት ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ አማካይነት ተጠንተው ከተለዩ፣ ከተተነተኑና ተተንትነውም የስህተት ድግግሞሻቸው ከተወቀ በኋላ ቀሪው ስራ ለእነዚህ ስህተቶች መፈጠር ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ማመልከት ነው:: በመሆኑም በተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ከተፈፀሙት ስህተቶች ትንተና፣ ከመምህራንና ከተማሪዎቹ መጠይቅ መልሶችና ከሌሎችም ተዛማጅ ጽሑፎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን አገናዝቦ በመውሰድ በዋነኛነት የታሰቡት የስህተት ምንጮች:-

1. ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ
2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ
3. የመማር ማስተማሩ ሂደትና
4. የስነልቡናዊ ሁኔታዎች ናቸው::

### 4.2.1 ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

በተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ ለተፈፀሙት ስህተቶች የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከታሰቡት መላምቶች ውስጥ አንዱ ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ነው:: ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ስህተተ-ብያኔ በመባል የሚታወቀው ሲሆን ይህም ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን አዲስ ስርአት ከለመደ በኋላ የታላሚውን ቋንቋ አጠቃላይ ህግ በማስፋፋት የመጠቀም ጉዳይ ነው:: /ብራውን፣ 1994 214ሀ፡ ሊትልውድ፣ 1986 23ና ነጋራ፣ 1983 36/:: ስለሆነም በተማሪዎቹ ድርሰቶች ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከልም የታላሚውን ቋንቋ /አማርኛ/ አጠቃላይ ህግ አስፋፍቶ በመጠቀም የተከሰቱ ስህተቶች አሉ:: እነዚህ ስህተቶች በዚህ ምዕራፍ በክፍል 4.1.2 የቋንቋ አጠቃቀም ተብሎ በቀረበው አቢይ ስህተት አይነት ምድብ ስር ካሉት ንዑስን የስህተት ምድቦች መካከል በቃላት ምርጫ ስህተት ላይ ተነስተዋል:: ስህተቶቹ በአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ውስጥ ዕውቅናን ያላገኙ ያልተለመዱ ቃላትን በእዝባር /ምህፃረ ቃል/ አሳጥሮ በመፃፍ የተከሰቱ ናቸው:: ለአብነት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል::

- በአሁኑ ጊዜ ያለው ሕዝብ ስለበሽታው ግንዛቤ ስለሌለው መ/ት ይህንን

አስከፊ በሽታ ለመቋቋም ... ማበርከት ይኖርብናል::

- በ1990 ዓ.ም. የተማሪዎች ዝግጅት ወ/ም የፈተና አቀባበል ምን ይመስል እንደነበር ለመግለጽ ያህል ...
- ስለዚህ ዋና ተግባሩ ህ/ቡን ከዚህ ደዌ በሽታ ለማላቀቅ ... ህ/ቡ ጉልህ ሚና መጫወት ይኖርበታል::
- እ/ር ካለ መሆኑ አይቀርም::

እነዚህና ሌሎችም ተመሳሳይ መረጃዎች በሚታዩበት ጊዜ የተለመዱ ባለመሆናቸው የተለያዩ አንባቢያን በምህፃረ ቃል ለተፃፉት ቃላት የተለያየ ፍች ሊሰጡ ይችላሉ:: ለምሳሌ:-

"መ/ት" ለሚለው -- መሠረተ ትምህርት፣ መንግስት፣ መሥሪያ ቤት፣ መከላከያ ትምህርት

"ወ/ም" " -- ወርም፣ ወሳኙም፣ ወይም ...

"ህ/ቡ" " -- ህዝቡ፣ ህብረተሰቡ፣ ህዝባዊ ቡድኑ ...

"እ/ር" " -- እስር፣ እግር፣ እግዚአብሔር፣ ... ተብሎ ሊተረጐም ይችላል::

በመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር የተገለፀው ምህፃረ ቃል በአረፍተ ነገር ሲገባም:-

በአሁኑ ጊዜ ... ስለሌለው የመሠረተ ትምህርት ይህን አስከፊ በሽታ ለመቋቋም ... ማበርከት ይኖርበታል::

በአሁኑ ጊዜ ... ስለሌለው የመከላከያ ትምህርት ይህን አስከፊ በሽታ ለመቋቋም ... ማበርከት ይኖርበታል

በአሁኑ ጊዜ ... ስለሌለው የመንግስት ይህን አስከፊ በሽታ ለመቋቋም ... ማበርከት ይኖርበታል የሚል ሊሆን ይችላል::

ታዲያ በምህፃረ ቃል የቀረበው ቃል የትኛው ነው? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ግራ የሚያጋባ ይሆናል:: በተመሳሳይ ሁኔታ "ወ/ም"፣ "ህ/ቡ"፣ "እ/ር" የተባሉት ምህፃረ ቃላትም የዚሁ አይነት ችግር የሚታይባቸው ናቸው:: ተማሪዎቹ እነዚህን ምህፃረ ቃላት ሊያፈልቁ የቻሉትም የታላሚውን ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ ዓመተ ምህረት ለማለት — "ዓ.ም."

"አዲስ አበባ"— "አ.አ"

"እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር" —"እ.ኤ.አ" ህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን → ህ.ቤ.ቆ.ኮ ..." እየተባለ በመማራቸው ነው:: እነሱም በተመሳሳይ ሁኔታ

ቃላቱን አፍልቀው በመጠቀማቸው ስህተቶቹ ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡

ያልተሟላ ትምህርት የተሳሳተ ቅንጅትና ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም ለውስጠ ቋንቋ ስህተት መፈጠር ምክንያቶች ናቸው፡፡ ያልተሟላ ትምህርት ሲባል ያልተሟላ የቋንቋ አወቃቀር፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤና ሌሎችንም ፍቻቸውን ወይም ትርጉማቸውን በቀላሉ ለመረዳት የሚያዳግቱ የቃላት አሰላለፍና አጠቃቀም ነው፡፡ /ነጋራ፣ 1983፡ 36-9/

በጥናቱ ውስጥ በተደረገው የስህተት ትንተና መሰረት ተጠኝ ተማሪዎቹ የፃፏቸው ድርሰቶች በተመረመሩበት ጊዜ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሳቢያ የተከሰቱ የሰዋሰው አገባብ /የቋንቋ አወቃቀር/ ስህተቶች እንደነበሩ በዚሁ ምዕ ራፍ ንዑስ ክፍል 4.1.3 የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች ተብሎ የቀረበ መሆኑ ይታወሳል፡፡ በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥም የዐረፍተ ነገር ስሙሙነት፣ የአጣማሪዎች አጠቃቀም፣ የመስተዋድድና ሌሎችም ንዑሳን የስህተት ምድቦች ተነስተዋል፡፡ ከየንዑሳን የስህተት አይነቶች ውስጥም፡-

ሀ. ለዐ.ነገር ስምምነት ከቀረቡት ስህተቶች መካከል

1. የፈተና ቀን አንድ ሳምንት ሲቀር የትምህርት አይነቶች ተጠንተው ማለቅ አለበት፡፡
2. አንድ ታላቅ እህት ሁልጊዜ ... ትለኝ ነበር፡፡ እኔ የዛን ጊዜ ... ስለማለውቅ የሱ ምክርና የሱ ቁጣ ምንም አይመስለኝም ነበር፡፡
3. ከዩኒቨርሲቲ ተመርቄ በተሰጠኝ የስራ ድርሻዬ ቤተሰቦቹን የረዳኋቸውን እመኛለሁ፡፡ ... የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች በሚታዩበት ጊዜ በመጀመሪያው ዐ.ነገር የቁጥር፣ በሁለተኛው የፆታ፣ በሦስተኛው የጊዜ ስሙሙነት የጐደላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ለ. ለአጣማሪዎች አጠቃቀም ስህተት ከተጠቀሱት መካከልም

- “ይሁን እንጅ ነገር ግን የወደፊት ምኞቴ ዶክተር ለመሆን ይፈልጋለሁ” የሚለው ይገኝበታል፡፡

ይህ አረፍተ ነገር በሚታይበት ጊዜ ተማሪው ሁለቱን አፍራሽ አጣማሪዎች "ይሁን እንጂ" ና "ነገር ግን" የሚሉትን በአንድ ላይ በመጠቀሙ ስህተቱን እንዲፈፅም አድርጐታል፡፡

ሐ. ለመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች ከተጠቀሱት መካከልም፡-

1. "... ሰነፍ ግን መቅበጥበጥ ይጀምራል ወደ መልስ ፍለጋ ካገኘም አገኘ ካላገኘም የሆነ ያልሆነውን ሞልተው ይወጣሉ"
2. "ይህ በሽታ በሃገራችን በ1968 ዓ.ም. በአ.አ - መገኘቱ ብዙ መጽሐፎች ያስረዳሉ ..." የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ዓ.ነገሮች ሲታዩ የመጀመሪያው ሰነፍ ተማሪ ከጐበዝ ተማሪ መልስ ለመፈለግ የሚቅበጠበጥ እንደሆነና ካገኘም አገኘ ካላገኘ ግን የሆነ ያልሆነውን ሞልቶ የሚወጣ መሆኑን ለመግለፅ በማሰብ "ወደ መልስ ፍለጋ" በማለት ለመገስገሻ የሚውለን መስተዋደድ "ወደ" ን ተጠቅሟል፡፡ በሁለተኛው ዐ.ነገር በሽታው በአ.አበባ የተገኘ መሆኑን የሚያስረዱ ጽሑፎች ያሉ መሆናቸውን ለመግለፅ የታሰበ ቢሆንም "ስለ" ወይም "ለ" የሚሉ መስተዋድዶች የጐደሉት በመሆኑ ስህተቱ ተፈፅሟል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ከላይ በዐ.ነገር ስሙሙነት በአጣማሪዎች አጠቃቀምና በመስተዋድድ አገባብ የተጠቀሱት ስህተቶችና ሌሎችም ሲታዩ የሰዋሰው አገባብ ወይም የቋንቋ አወቃቀር ትምህርት በተሟላ መንገድ ባለመሰጠቱ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው ሊባል ይችላል፡፡

ሌላው በዚሁ ምዕራፍ በንዑስ ምዕራፍ 4.1.2 የተነሳው የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ሲሆን በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ ኢመደበኛ ቃላት የመጠቀም፣ የቃላት አደራደር ስህተቶችና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡ ለአብነት ያህልም፡-

ሀ. ለቃላት ምርጫ ከቀረቡት ስህተቶች መካከል፡-

- "አስተዋይ ተማሪ እንደ ማንኛውም ተማሪ ልናስተውለው አይገባም"
- "... ይኸውም በበኩሌ የማስቀምጠው ምኞት ... " የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች በሚታዩበት ጊዜም በመጀመሪያው ዐ.ነገር አስተዋይ ተማሪ ከሌሎች ተማሪዎች በበለጠ መታየት ያለበት እንጅ ቸል ሊባል የማይገባው መሆኑን ለመግለጽ ታስቦ የቀረበ ሲሆን፤ በሁለተኛው ዐ.ነገርም ተማሪው ለወደፊት አገኘዋለሁ ብሎ ስለሚመኘው ነገር ለመግለፅ የተፈለገ ይመስላል፡፡ ሆኖም የቃላት አመራረጡ ሲታዩ አስተዋለ ለሚለው→ተገነዘበ፣ በትኩረት አየ ከሚለው ፍች በመነሳት "ልናየው" የሚለውን ቃል ተቀራራቢ ፍች ባለው ቃል "ልናስተውለው" በሚለው በመተካት ሲጠቀምበት ታይቷል፡፡ "የማስቀምጠው" የሚለውም በተመሳሳይ ሁኔታ "የምገልፀው"፣"የሚኖረኝ" ... የተባሉትን ቃላት ለመጠቀም በተቸገረበት ጊዜ ተቀራራቢ ፍች ያለውን ቃል በመፈለግ የተመረጠ በመሆኑ ስህተቱን እንዲከሰት አድርጎታል፡፡

ለ. ለኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀም ከቀረቡት ስህተቶች መካከል:-

- "እንደ እሷ በታመመች ቁጥር ጠይቀን በተቸገረች ጊዜ ችግሯን አውለን በጠራችን ጊዜ ደርሰንላት "የምንለበኛት" የሚለው ይገኝበታል፡፡

በዚህ ዐ.ነገር አማካኝነት ለመግለፅ ያተሰበው ጉዳይ እናት ልጆቿ ሲታመሙ ሆነ ሲቸገሩ ዝም ብላ የማታይ በመሆኗ እሷ በታመመችና በተቸገረት ጊዜ ደግሞ ልጆቿ ብድር መላሾች መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ ሆኖም "አውለን" ና "የምንለበኛት" የሚሉት ቃላት ኢመደበኛ የሆኑ የአካባቢ ዘዬዎች በመሆናቸው የዐ.ነገሩን መንፈስ ለመረዳት በመጠኑም ቢሆን አስቸጋሪነት ታይቶበታል፡፡

ሐ. ለቃላት አደራደር ስህተቶች ካቀረቡት መካከልም:-

- አንዳንድ ሰዎች ታመው ሳያቸው ... ማረፊያ ቦታ ሰጥቼ ነበር የማስተናግዳቸው
- በመሆኑም ቶሎ አይገድልም አሰቃይቶ የአልጋ ቁራኛ አድርጎነው የሚያሳርፈው አፅሙን ከጉድጓድ ... የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እነዚህ በምሳሌ የቀረቡ ዐ.ነገሮችና ሌሎችም በሚታዩበት ጊዜ የቃላትን ቅደም ተከተል ብሎም የዐ.ነገሩን አመሰራረት ያልተከተሉና የተዘበራረቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ያልታሰሩ ማለትም በተንጠልጠል የቀሩና መደበኛውን የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ያልተከተሉ በመሆናቸው አንባቢው መልዕ

ክቱን ለመጨበጥ ግራ ይጋባል፡፡ ስለሆነም እነዚህና ሌሎችም ተመሳሳይ ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ ያልተሟላ የቋንቋ አጠቃቀም ትምህርት ለቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ባልተሟላ ትምህርት ምክንያት ከሚከሰቱት ስህተቶች አንዱ የቃላትን ትክክለኛ ፍች ካለማወቅ የተነሳ የሚፈፀም የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም በተጠኝ ተማሪዎቹ በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ በአይነት ተለይተው ከተቆጠሩት ስህተቶች መካከል አንዱ የፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ እንደነበር በዚሁም ምዕራፍ ንዑስ ቁጥር 4.1.6 የቀረበ መሆኑ ይታወሳል፡፡ ለምሳሌ ያህልም፡-

- ይህ ተማሪ የሚጽጣው ፈተናውን ለመፈተን ቀርቶ አንድ ፊደል የማይጭር ነው፡፡ እንግዲህ ይህ ተማሪ <u>እንደ መደበኛው ተማሪ</u> ክፍል ይገባና ከተማሪዎቹ ጋር ተቀላቅሎ ፈተናውን ሊፈተን ይዘጋጃል፡፡
- ኤድስ የሚባለው <u>ቀልጣፋ</u> በሽታ የመጣው እንደሚሉት ከሆነ ከዝንጀሮ ሲሆን ... እስት ተገንዘቡ የማይረባ ነገር ለመባዛት፣ ለመሠራጭ፣ ከቦታ ቦታ <u>መጋዝ</u> በጣም ፈጣን ነው፡፡
- ሆኖም ይህ በሽታ በጣም አስከፊና ... መሆኑን እናውቃለን፡፡ ግን ሰዎች ከዚህ በሽታ ለመከላከል የምያደርጉት <u>አስተዋይነት</u> አይኖርም፡፡ ... የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በሦስቱም ዐ.ነገሮች ውስጥ ከስራቸው የተሰመረባቸው "መደበኛ ተማሪ"፣ "ቀልጣፋ"፣ "መጋዝ"ና "አስተዋይነት" የተባሉት ቃላት ከዐ.ነገሩ አውደንባብ ውጭ የገቡ ሲሆን ተማሪዎቹ እነዚህን ቃላት የተጠቀሙት ቃላቱ የያዙትን ፅንሰ ሐሳብ ካለመገንዘብ የተነሳ በተሳሳተ መንገድ ነው፡፡ የእነዚህ ቃላት ትክክለኛ ፍች፡-

- መደበኛ ተማሪ - በቀኑ የትምህርት ፕሮግራም የሚከታተል
- ቀልጣፋ - ንቁ፣ ፈጣን
- አስተዋይነት - አመዛዛኝነት፣ ብልህነት
- መጋዝ - ከስፍራ ስፍራ መተላለፍ ሲሆን፣

እየቀረ የሚመጣ ወይም ሰነፍ ተማሪን እንደ ኢመደበኛ ወይም የማታ ተማሪ በመቁጠር፣ ቀልጣፋ የሚለውን የሰው ህይወት ቀሳፊ፣ ቀጣፊ አድርጎ በመውሰድ፣ መጋዝ የሚለውን የበሽታው መተላለፊያ መንገድ አድርጎ በመውሰድ፣ አስተዋይነት የሚለውንም እንደ ጥረት ወይም አድርጎ፣ በመውሰድና አስተዋይነት የሚለውንም እንደ ጥረት ወይም

አስተዋጽኦ አድርጐ በመመልከት ስህተቶቹ ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡ በነዚህ ምሳሌዎችና ሌሎችም ስህተቶች የተነሳ ያልተሟላ የፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ትምህርት ለፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ስህተት መፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

መምህራንና ተማሪዎች በመጠይቆቹ ውስጥ ከሰነዘሯቸው አስተያየቶች መካከል አብዛኞቹ እስካሁን የተገለፁትን ሐሳቦች የሚያዳብሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በክፍል ሦስት ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ስትፅፍ በአብዛኛው የምትፈፅሚቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው? ተብለው ተማሪዎቹ ለተጠየቁት ሲመልሱ 107 የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ 52 የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ 42 የዐ.ነገር አመሰራረት፣ 21 የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ፣ 10 የሆሄያት አጠቃቀምና 8 ተማሪዎች የአንቀጽ አመሰራረት ስህተቶች ናቸው ብለዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለምትፈፅሚቸው ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ብላችሁ የምታስቧቸውን ግለፁ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄም ሲመልሱ የሁለተኛ ቋንቋውን ስርአት አለመረዳት፣ ከአንድ በላይ ፍች ያላቸው ቃላት መብዛት፣ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት መኖር መምህራን ለጽህፈት ልምምዱ ትኩረት አለመስጠት፣ የመምህሩ በቂ ዕውቀት አለመኖርና በዚህም የተነሳ በደንብ አለማስተማርና የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማነስ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም ተማሪዎቹ ለሚፈፅሚቸው የስህተት አይነቶች መምህራኑ በክፍል ሦስት ተጠይቀው ሲመልሱም የፅንሰ ሃሳብ ግንዛቤ፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የዐ.ነገር አሰካክ፣ የሳድስና የስርአተ ነጥቦች አጠቃቀም፣ የመስተዋድዶችና የማሰሪያ አንቀጽ አጠቃቀም ስህተቶች እንደሚፈፅሙ ገልፀዋል፡፡

ተማሪዎቹ ይፈፅሚቸዋል ተብለው ለቀረቡት ስህተቶች የስህተት ምንጩን እንዲገልፁ በተጠየቁት መሰረት ከመለሷቸው መልሶች መካከል ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋውን ስርአት አለመልመዳቸውና በቂና የሰለጠነ የሰው ሃይል ያለመኖር ናቸው የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ስለሆነም ቀደም ሲል በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች እንዲሁም በተማሪዎቹና በመምህራኑ በተሰጡት አስተያየቶችና በሌሎችም ተዛማጅ ጽሑፎች መሰረት ይፈፀማሉ ተብለው የታሰቡትና የተፈፀሙት ስህተቶች ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ፣ የቀረቡት መረጃዎች፣ የተሰጡት አስተያየቶችና ተዛማጅ ጽሑፎች እንዳመለከቱት በዚህ ጥናት ውስጥ ለስህተቶቹ መፈጠር ምክንያት ሆነው ከቀረቡት ነገሮች መካከል አንዱ የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

### 4.2.2 <u>የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ</u>

እንደሚታወቀው ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ እየተማረው ሲሄድ የአፍመፍቻ ቋንቋው ከታላሚው ቋንቋ ጋር ይበልጥ እየተዋሀደ የሚሄድ በመሆኑ ስህተቶቹም ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ሆኖም ፈፅሞ ሊጠፉ አይችሉም፡፡ እንደነዚህ አይነት ስህተቶችም ፎሲላይዝድ በመባል የሚገለፁ ሲሆኑ እነዚህም የተማሪው ንግግር ወይም ጽህፈት ቋሚ ባህሪያት እየሆኑ ይሄዳሉ፡፡ /ሊትልውድ፣ 1986፡ 34ና ብራውን፣ 1994፡ 217/ ስለሆነም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ ተጠኝ ተማሪዎች ላይ የዚህ አይነቱ ባህርይ ሊታይ ችሏል፡፡

የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን ሲማሩ ከሚያጋጥሟቸው የጽምፅ አፈላለቅ ችግሮች መካከል የ'ዠ' የ'ኘ' ድምፆች ጉዳይ አንዱ ነው፡፡ እነዚህ ድምፆች በኦሮምኛው የድምፅ አፈላለቅ ስርአት የማይታወቁ በመሆናቸው ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ሲፅፉ ወይም ሲናገሩ 'ዠ' በ'ሰ'፣ የ'ኘ' ን በ'ጀ' እያተካኩ ይጠቀማሉ፡፡ /ትምህርት ሚኒስቴር 1987፡ 7/

<u>ለምሳሌ፡-</u> አንዳንድ ተማሪዎች ... ልጅዬውን መደብደብ የምያስቡ ቦሰኔ ተማሪዎች አሉ

- በዘንድሮው አመት የጊዜው ያለጠበቀ ስናብ በመስነብ አማካኝነት የተከሰተው ጉርፍ ... ሃብትና ንብረት ሊያጠፋ ችሏል፡፡
- ይኸውም ወቅቱ የአዝመራ ወቅት ስለነበር አስመራውም በተለያዩ ሐገሮች ወደ መድረሱ ደረጃ ደርሰው ስለነበር በዝናቡ አማካኝነት በፊት ከምገኘው ገብ አስመራው በእጥፉ እንደቄነሰ ይነገራል

- ገበሬው በአሁኑ ሰዓት ማስመር ነበረበት
- ... ባገኘውት ደሞስ እሷ እንዳደረገችልኝ ውለታውን እከፈልለታለው::

በእነዚህ ዐ.ነገሮች ውስጥ ቦሰኔ፣ አስመራውም፣ ስናቡ፣ በመስነቡም ማስመር ደሞስ የሚሉት ቃላት ቦዘኔ፣ አዝመራውም፣ ዝናቡ፣ በመዝነብ፣ ደመወዝ ለማለተ ታሰበው የገቡ ሲሆኑ በገቡበት ቦታም ስህተት እንዲከሰት ያደርጉ መሆናቸው ቀደም ሲልም በዚሁ ምዕራፍ በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ የስህተት አይነት ውስጥ ተነስተዋል::

የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያሏቸው አናባቢዎች አምስት በመሆናቸው ኧ ና 'እ' የተባሉ አናባቢዎች የሏቸውም:: በመሆኑም 'እ' የተባለችውን ሳድስ አናባቢ በአማርኛ ቋንቋ በሚጠቀሙበትጊዜ ከሳልሱ አናባቢ 'ኢ' ጋር ያተካኩታል:: በአጠቃቀማቸውም እነዚህን አናባቢዎች እንደሁለት አናባቢ በመቁጠር ሳይሆን እንደ አንድ አድርገው የሚቀጠሙበቸው በመሆኑ ስህተት ይፈፅማሉ/ይልማ፣ 1956:3 ና ት/ሚኒስቴር፣ 1987:7/ለዚህም የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል::

- ስለሆነም መንግስት ... ባለሙያዎችን እያሳተፈ የጾታ ትምህርትን ብሰጥ ይመርጣል::
- ጥፋት ቢፈፅምና እንድቀጣ/እንድገረፍ/ በቤተሰቡ ቢወሰን የእናት ሆድ ገር በመሆኑ ... በማለት ልጁን ከግርፈት ያድኑታል::
- ስለፆታ ትምህርት ባለመኖሩ ለወደፊቱ እንድኖር ብደረግ ሰው ሁሉ የተለያዩ በሽታዎችን ይከለከላል ማለት ነው::
- አንዱ በአእምሮው የያዘውን ስናገር... ሌላው ደግሞ ... በቁራጭ ወረቅት ጽፎ ይገባል::
- እንግዲህ ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ነውና ከመስረቅና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መሄዱ ጥሩ ይመስለኛል::

እነዚህ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ሳልሱን ለሳድስ፣ ሳድሱን ለሣልስ በመተካት የተፃፉ ሲሆኑ በቃላቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በዐ.ነገሩ ሃሳብ ላይም ለውጥን ሊያስከትሉ ችለዋል:: ለውጡም በመጀመሪያው ዐ.ነገር የጾታ ትምህርቱ በመንግስት ይሰጥ የሚል መንፈስ ቢኖረውም በአናባቢው ምክንያት

ሰጭው 'እኔ' እንድሆን፣ በሁለተኛው "ጥፋት" የሚለው ወደ ጥፊት ከመለወጡም በላይ ልጁ በቤተሰቡ እንዲቀጣ፣ እንዲገረፍ" የተወሰነበት መሆኑን ለመግለፅ ታስቦ ሲፃፍ ግን "እኔ" እንድቀጣና እንድገረፍ፣ በሦስተኛው አረፍተ ነገር እንዲኖር የተፈለገው የጸታ ትምህርት ሆኖ እያለ በአፃፃፍ "እኔ እንድኖር ብደረግ፣ በአራተኛው ተናጋሪው እሱ ሆኖ እያለ በአፃፃፍ ምክንያት እሱ በአእምሮው የያዘውን "እኔ ስናገረው"፣ በአምስተኛው ዐ.ነገር "... ከመስረቅና የማያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት ለማለት ታስቦ ከመስረቅና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መኖሩ ጥሩ ይመስለኛል በማለት ድርጊት ፈፃሚው ወይም ተቀባዩ የታሰበው ወይም የፈፀመው ሳይሆን ሌላ እንዲሆን አድርጉታል:: በጥቅሉ እነዚህና በተመሳሳይ ሁኔታ የተፈፀሙ ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ በ3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የሚነገሩ ቃላት በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንዲነገሩ ወይም እንዲፃፉ ምክንያት ሆኗል:: በዚህም ምክንያት የተነሳ ስህተት ሊፈፀም ችሏል::

ይልማ/1956: 32/ ኖርድፌልትን ጠቅሰው እንደሚሉት በኦሮምኛ ቋንቋ ተባዕታይና አንስታይ ጾታን መለያ የሚሆን የጠበቀ ህግ የሌለ በመሆኑ እነዚህ ተጠኝ ተማሪዎች አንስታይ ፆታን የሚያመለክቱ ስሞችንም ሆነ ግሶችን ሲፅፍ በተባዕታይ ነው:: ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል::

- ስለዚህ እናት ለምንም ጊዜ የማትገኝ ስለሆነች እናታችን በደንብ አንከብክበን ሊሞት እስክያበቃ ድረስ ማስደሰት ያስፈልገናል
- ውብነሽ የምትባል ልጅ ነበረች:: በጣም ወደድኩት:: ወደድኩሽ ብሎ ልነግራት አልቻልኩም::
- እናት ተርቤን ስታየን ተርባ ተጠምተን ስታየን ተጠምታ ታሳድገናለች:: በመሆኑም እንደዚህ አይነት ውለታ ለምውል ሰው አፀፋውን የምመልስ ልጅ መሆኑ ግልጽ ነው::
- አንድ ታላቅ እህተ ሁልጊዜ ... አታጠናም፣ ይሻልሃል ወዬውልህ ትወድቅና ትለኝ ነበር:: እኔ የዛን ጊዜ ... ጠለቅ ብሎ ስለማላውቅ የሱ ምክርና የሱ ቁጣ ምንም አይመስለኝም ነበር::
- ከበደች ኮቦት ለቀማ ስትሔድ ከአንድ ልጅ ጋር እያወራች በምትሔድበት ጊዜ ቶላ ከጋራ ቤት ወጥቶ ብቅ አለበት::

ሰጭው 'እኔ' እንድሆን፣ በሁለተኛው "ጥፋት" የሚለው ወደ ጥፌት ከመለወጡም በላይ ልጁ በቤተሰቡ እንዲቀጣ፣ እንዲገረፍ" የተወሰነበት መሆኑን ለመግለፅ ታስቦ ሲፃፍ ግን "እኔ" እንድቀጣና እንድገረፍ፣ በሦስተኛው አረፍተ ነገር እንዲኖር የተፈለገው የጸታ ትምህርት ሆኖ እያለ በአፃፃፍ "እኔ እንድኖር ብደረግ፣ በአራተኛው ተናጋሪው እሱ ሆኖ እያለ በአፃፃፍ ምክንያት እሱ በአእምሮው የያዘውን "እኔ ስናገረው"፣ በአምስተኛው ዐ.ነገር "... ከመስረቅና የማያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት ለማለት ታስቦ ከመስረቅና የሚያስፈልጉ ነገሮችን ከመስራት በደንብ ተዘጋጅቶ መኖሩ ጥሩ ይመስለኛል በማለት ድርጊት ፈፃሚው ወይም ተቀባዩ የታሰበው ወይም የፈፀመው ሳይሆን ሌላ እንዲሆን አድርጉታል:: በጥቅሉ እነዚህና በተመሳሳይ ሁኔታ የተፈፀሙ ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ በ3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የሚነገሩ ቃላት በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንዲነገሩ ወይም እንዲፃፉ ምክንያት ሆኗል:: በዚህም ምክንያት የተነሳ ስህተት ሊፈፀም ችሏል::

ይልማ/1956፡ 32/ ኖርድፌልትን ጠቅሰው እንደሚሉት በኦሮምኛ ቋንቋ ተባዕታይና አንስታይ ጾታን መለያ የሚሆን የጠበቀ ህግ የሌለ በመሆኑ እነዚህ ተጠኝ ተማሪዎች አንስታይ ፆታን የሚያመለክቱ ስሞችንም ሆነ ግሶችን ሲፅፍ በተባዕታይ ነው:: ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል::

- ስለዚህ እናት ለምንም ጊዜ የማትገኝ ስለሆነች እናታችን በደንብ አንከብክበን ሊሞት <u>እስክያበቃ</u> ድረስ ማስደሰት ያስፈልገናል
- ውብነሽ የምትባል ልጅ ነበረች:: በጣም <u>ወደድኩት</u>:: ወደድኩሽ ብሎ ልነግራት አልቻልኩም::
- እናት ተርቤን ስታየን ተርባ ተጠምተን ስታየን ተጠምታ ታሳድገናለች:: በመሆኑም እንደዚህ አይነት ውለታ <u>ለምውል ሰው አፀፋውን</u> የምመልስ ልጅ መሆኑ ግልጽ ነው::
- አንድ ታላቅ እህተ ሁልጊዜ ... አታጠናም፣ ይሻልሃል ወዬውልህ ትወድቅና ትለኝ ነበር:: እኔ የዛን ጊዜ ... ጠለቅ ብሎ ስለማላውቅ <u>የሱ ምክርና የሱ ቁጣ</u> ምንም አይመስለኝም ነበር::
- ከበደች ኮቦት ለቀማ ስትሔድ ከአንድ ልጅ ጋር እያወራች በምትሔድበት ጊዜ ቶላ ከጋራ ቤት ወጥቶ ብቅ <u>አለበት</u>::

በእነዚህ በተሰመረባቸውና ሌሎችም ቃላት ምክንያት የጾታ ለውጥ እንዲኖር በመደረጉ አንባቢው የድርጊቱ ፈፃሚ ወይም ድርጊት ተቀባዩ ወንድ ይሁን ሴት ለመለየት ችግር ይፈጥርበታል::

የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች 'አ' ድምፅ የሌላቸው በመሆኑ በስተመድረሻ ሆነ መሃል ላይ ሲመጣ ወደ ኣ ይለውጡታል:: እንዲሁም የአማርኛ ግሦች በሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ሲነገሩ መድረሻቸው አናባቢ 'አ' ይሆናል:: የኦሮምኛው ግስ ደግሞ በ'ኤ' ድምፀ የመድረስ ጠባይ ስላለው ተማሪው በዚያው በለመደው ስርአት በመጠቀሙ ስህተት ይፈፅማል /ትምህርት ሚኒስቴር 1987፣ 7-9/ ስለሆነም ተጠኝ ተማሪዎቹ በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ የነዚህ አይነት ስህተቶች ተፈፅመዋል:: ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ቀርበዋል::

"... ከጋራ ቤት ወጥቶ ብቅ አለበት" -- መባል የሚገባው ከጉረቤት

"... አንድ ታላቅ እህተ" -- አንዲት ታላቅ እህቴ

"... በእርዳታም ሆኔ በለላም ጥራቱ የጠነከሬ መሆን አለበት" -- በእርዳታም ሆነ በሌላም ጥረቱ የጠነከረ መሆን አለበት

"ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ባልተቀቀለ መርፌና ስሌት ሀ/ቡን ለአስከፊ አደጋ ... ነው" -- ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ባልተቀቀለ መርፌና ስለት ሀ/ቡን ለአስከፊ አደጋ ... ነው::

"... የተለያዩ መጻህፍት እየፃፍኩ ለአገሪቱ ህዝብ ለመበርከት ከፍ ያለ ፍላጐት አለኝ" -- የተለያዩ መጻህፍትን እየፃፍኩ ለአገሪቱ ህዝብ ለማበርከት ከፍ ያለፍላጐት አለኝ::

እነዚህ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ሲታዩ ተጠኝ ተማሪዎቹ ሐምሱን -- ግዕዙ፣ ግዕዙን -- ሐምስ፣ ራብዕን -- ግዕዝ፣ ግዕዙን -- ራብዕ በማለዋወጥ የተፃፍ ሲሆኑ፣ በመለዋወጣቸው ምክንያት ስህተት እንዲከሰት አድርገዋል::

ይልማ /1956 ፡ 32/ ምንጭ ጠቅሰው እንደሚሉት መስተዋድዶች በኦሮምኛ ቋንቋ በቃላት መጨረሻ እንጅ መጀመሪያ ላይ ባለመግባታቸው በአማርኛው ቋንቋ ሲጠቀሙባቸው ይዘሏቸዋል ወይም ያለቦታው ያስገቧቸዋል::

ስለዚህ ይኸው ጉዳይ በተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ያህልም በምዕራፍ አራት በ4.1.3.2 ለ ከቀረቡት የመስተዋድ አገባብ ስህተቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ... አንድ ላይ በሚቀመጡበት ጊዜ ከ10ኛ ክፍል ተማሪ ላይ 8ኛ ክፍል የሆነው ተማሪ ይፅፍለታል
- ለምሳሌ በግብርና ትምህርት ሆኖ የተመረቅኩኝ ለም አፈራችን ተሸርሽሮ ወደ ሌላው እንዳይሄድ አደርጋለው ነበርኩ፡፡

በመጀመሪያው ዐ.ነገር "ከ - ላይ የ - የሚሉት መስተዋድዶች ያለቦታቸው የገቡ ናቸው፡፡ መሆን የነበረበትም አንድ ላይ በሚቀመጡበት ጊዜ የአስረኛ ክፍሉ ተማሪ ለ8ኛ ክፍሉ ይፅፍለታል የሚል ነበር፡፡

በሁለተኛው ዐ.ነገር ሆኖ "የተመረቅኩኝ" የሚለው የተሳሳተ ነው፡፡ መሆን የነበረበት ለምሳሌ በግብርና ትምህርት ብመረቅ ኖሮ ለም አፈራችን ተሸርሽሮ ወደ ሌላው እንዳይሄድ አደርግ ነበር የሚለው ነው፡፡ ሆኖም ከላይ በተገለፀው መንገድ የመስተዋድድ አጠቃቀም ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ስህተት ሊፈፀም ችሏል፡፡

ኖሪሽ/1990 : 41-21/ እንደሚሉት የአፍመፍቻ ቋንቋ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ሲሆን በውጭ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚፈፀሙት ስህተቶች ምክንያቱ ተማሪው በክፍል ውስጥ ለተጋለጠበትና ይማረዋል ተብሎ በታሰበው ቋንቋ የሚወሰን ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው የሚፈፅመው ስህተት ምክንያቱ ተማሪው ከክፍል ውጭ በሚያጋጥመው ተፅዕኖ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም እስካሁን ድረስ የተጠቀሱት ስህተቶች ተማሪው ከክፍል ውጭ ለሚያጋጥመው ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በሰፊው የተጋለጠ በመሆኑ የተፈፀሙ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በሚማረው የውጭ ቋንቋ /እንግሊዝኛ/ ምክንያት የተፈፀሙ ስህተቶች አሉ፡፡ እነዚህ ስህተቶች በአፍመፍቻ ቋንቋቸው አማካኝነት የተገለፁትን ስህተቶች ያህል ጉልተው ባይታዩም ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ በንዑስ ምዕራፍ 4.1.4 በቀረቡት የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ላይ በምሳሌነት ቀርበዋል፡፡ እነዚህ በምሳሌነት የቀረቡት የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ፡-

- አራት ነጥብን ለመጠቀም -- የእንግሊዝኛውን Fullstop /./
- ነጠላ ሰረዝን ለመጠቀም - የእንግሊዝኛውን Comma /,/

በመጠቀም የተፈፀሙ ናቸው፡፡

ስለሆነም ከፍ ሲል በምሳሌነት የቀረቡትና ሌሎችም አይነት ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ለስህተት መፈጠር ምክንያት መሆኑን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ናቸው፡፡

መምህራንና ተጠኝ ተማሪዎቹ በመጠይቁቹ ውስጥ ከሰነዘሩዋቸው አስተያየቶች አብዛኞቹ ይህንኑ የሚያጠነክሩ ናቸው፡፡

ለመምህራን ባቀረበው መጠይቅ ክፍል ሁለት መመሪያ ሁለት ተራ ቁጥር 9 ላይ በጽህፈት ልምምዱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለው ተፅዕኖ ምን ያህል ነው? ተብለው ተጠይቀው ሲመልሱ ካሉት ሦስት መምህራን መካከል አንዱ በ33.33% ከፍተኛ ነው ሲል፣ ሁለቱ ደግሞ በ66.66% መካከለኛ ብለው መልሰዋል፡፡ እነዚሁ መምህራን የመምህራኑን ነፃ አስተያየት በሚጠይቀው ክፍል ሦስት ተራ ቁጥር 9 የስህተት ምንጭ ብለው የሚያስቧቸውን እንዲገልፁ በተጠየቁት መሰረት ከሦስቱ ሁለቱ ለቋንቋው ሁለተኛ ሰው ሆነው በመቅረባቸው የአፍመፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ እየገባ ነው ብለው ሲመልሱ አንዱ ደግሞ የተለየ መልስ ሰጥቷል፡፡

ሠንጠረዥ 5. <u>ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶችና ምክንያት በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ</u>

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመምህራን ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 21 | አብዛኞቹ ተማሪዎች ይበልጥ ስህተት የሚፈፅሙት ምን ላይ ነው? | | |
| | ስርአተ ነጥብ | - | - |
| | የቃላት አገባብና አጠቃቀም | 2 | 66.66 |
| | የዐ.ነገር አመሰራረት | 1 | 33.33 |
| | የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ | - | - |
| | በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ | - | - |
| 22 | ለተማሪዎቹ ስህተት መፈፀም ምክንያቱ ምን ይመስለዋታል? | | |
| | የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ | 1 | 33.33 |
| | የተማሪዎቹ ግዴለሽነት | - | |
| | የሁለተኛ ቋንቋው ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪነት | 1 | 33.33 |
| | የመምህራን የአስተራም ጉድለት | - | |
| | የመረሃ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ ብቃት ማነስ | 1 | 33.33 |

በሠንጠረዥ 5 እንደተገለፀው ለመምህራኑ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልሶች መረዳት የተቻለው ተማሪዎቹ በቃላት አጠቃቀም ላይ ይበልጥ ስህተት እንደሚፈፅሙና ለተማሪዎቹ ስህተት መፈጠር ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ እንደሆነ ነው፡፡ በተራ ቁጥር 21,22 ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው መልስም በስህተት ትንተናው ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳያነት ያለው ነው፡፡ በተራ ቁጥር 22 የተጠቀሰውም ቢሆን በስህተት ትንተናው በተለይም በቋንቋ አጠቃቀም በዐ.ነገር አመሰራረትና በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ የአፍመፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አለው የሚለውን የሚያጠነክር ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6 ተማሪዎች ሲፅፉ የሚፈፅሟቸው የስህተት መጠኖችና በአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የሚፈፅም የስህተት መጠንን በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረቡ መጠይቅ መልሶች

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 % | 2 % | 3 % | 4 % | 5 % |
| 7 | ተማሪዎቹ የሚፈፅሟቸው የስህተት መጠን ምን ያህል ነው? | 18.7.5 | 44.18.33 | 100.41.66 | 54.22.5 | 24.10 |
| 8 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካኝነት የሚፈፀመው የስህተት መጠን ምን ያህል ነው? | 50.20.83 | 68.28.3 | 60.25 | 36.15 | 26.10.83 |

አማራጮች፡-

1. በጣም ከፍተኛ
2. ከፍተኛ
3. መካከለኛ
4. ዝቅተኛ
5. በጣም ዝቅተኛ

ሠንጠረዥ 6 በሚታይበት ጊዜ ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው የስህተቶች መጠን የሰጡት ምላሽ እንደሚጠቁመው አብዛኞቹ መካከለኛ ስህተት እንፈፅማለን ሲሉ 18 ተማሪዎች (7.5%) በጣም ከፍተኛ፣ 44 ተማሪዎች (18.33%) ከፍተኛ 100 ተማሪዎች (41.66%) መካከለኛ፣ 54 (22.5%) ዝቅተኛ 24 ተማሪዎች (10%) ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ስህተቶችን እንፈፅማለን

ዝቅተኛ 24 ተማሪዎች (10%) ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ስህተቶችን እንፈፅማለን ብለዋል፡፡ በተራ ቁጥር 8 የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለውን ተፅዕኖ ሲገለፁ 50 ተማሪዎች (20.83%) በጣም ከፍተኛ፣ 68 ተማሪዎች (28.3%) ከፍተኛ፣ 60 ተማሪዎቹ (25%) መካከለኛ፣ 36 ተማሪዎች (15%) ዝቅተኛ፣ 26 ተማሪዎች (10.83%) በጣም ዝቅተኛ ስህተት እንደሚፈፅሙ ገልፀዋል፡፡ በተራ ቁጥር 7 ና 8 ከቀረቡት መልሶች ማጠቃለል የተቻለው ተማሪዎቹ ከፍተኛ ስህተት ለመፈፀማቸው የቀረበው አዎንታዊ ምላሽ ከፍተኛ መሆኑና የአፍመፍቻ ቋንቋ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖም ከፍተኛ እንደሆነ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 7፡ <u>በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ ችግር የሚፈጥሩ ነገሮች የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች በተመለከተ ለተማሪዎች የቀረቡ መጠይቅ መልሶች</u>

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | የተማሪዎች | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 19 | በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ ችግር የሚያጋጥምህ(ሽ) ምን ላይ ነው? | | |
| | 1. የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ | 62 | 25.83 |
| | 2. የቃላት አጠቃቀም ላይ | 75 | 31.25 |
| | 3. የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ | 35 | 14.58 |
| | 4. የዐ.ነገር አመሰራረት ላይ | 38 | 15.83 |
| | 5. የቃላት ፍቺ ላይ | 30 | 12.50 |
| | | 240 | 100 |
| 20 | በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ በተደጋጋሚ ስህተት የምትፈፅመው(ሚው) ምን ላይ ነው? | | |
| | 1. ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ | 54 | 22.50 |
| | 2. የቃላት አጠቃቀም ላይ | 66 | 27.05 |
| | 3. የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ላይ | 57 | 23.80 |
| | 4. የዐ.ነገር አመሰራረት ላይ | 39 | 16.30 |
| | 5. የቃላት ፍቺ ላይ | 24 | 10.00 |
| | | 240 | 100 |
| 18 | በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ ለሚፈጠሩ ስህተቶች የስህተት ምንጭ ተብለው የሚገመቱ ምን ምን ናቸው? | | |
| | 1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ | 72 | 30.00 |
| | 2. የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት አስቸጋሪነት | 87 | 36.25 |
| | 3. የመምህራን የማስተማር ዘዴ | 40 | 16.66 |
| | 4. የመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት ትኩረት አለመስጠት | 28 | 11.66 |
| | 5. የመምህራን የአስተራረም ጉድለት | 13 | 5.41 |
| | | 240 | 100 |

በሠንጠረዥ 7 በቀረበው መረጃ መሠረት ተማሪዎቹ በሚጽፉበት ጊዜ ችግር ይፈጥሩብናል ያሏቸው ነገሮች ቀደም ሲል በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎችና በመምህራን መጠይቅ ከተሰጡት መልሶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ በተደጋጋሚ እንፈፅማቸዋለን ያሏቸው ስህተቶችም ከመምህራኑ የመጠይቅ መልሶችና በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆኑም በደረጃ በቅደም ተከተል ሲቀመጡ ግን ከቋንቋ አጠቃቀም ውጭ ያሉት በተቃራኒው የተቀመጡ ናቸው፡፡ በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ ለሚፈጠሩት ስህተቶች የስህተት ምንጭ ይሆናሉ ብለው የገመቷቸውም በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪነት የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የመምህራን የማስተማር ዘዴ የመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት ትኩረት አለመስጠትና የመምህራን የአሰተራረም ጉድለት ይሆናሉ፡፡

ስለሆነም በሠንጠረዥ 5፣ 6 ና 7 ከቀረቡት የመምህራንና ተማሪዎች የመጠይቅ መልሶች እንዲሁም በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎችና ከሌሎች ተዛማጅ ጽሑፎች ጋር በማገናዘብ የተገኘው ውጤት እንደሚጠቁመው የአፍመፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ የስህተት ምንጭ መሆኑን ነው፡፡

### 4.2.3 <u>የመማር ማስተማር ሂደት</u>

በስህተት ትንተናው ከተገኙት ፍንጮች በተጨማሪ ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች የመማር ማስተማሩ ሂደት ለጽህፈት ልምምዱ ተግባራዊ አለመሆን አስተዋጽኦ እንዳለው ይጠቁማሉ፡፡ ከእነዚህ መረጃዎች ውስጥ መልመጃውንና የመልመጃውን ተግባራዊነት በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ይገኛሉ፡፡

## ሠንጠረዥ 8፡ የክፍልና የቤት ስራ ልምምድን በሚመለከት ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

| | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | |
| 11 | ጽሁፈትን ለማዳበር የሚያስችሉ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች በት/ቤቱ ይካሄዳሉ? | - | - | 1 | 33.33 | - | - | 1 | 33.33 | 1 | 33.33 |
| 12 | በጽሑፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤት ስራ ሰጥተው ያውቃሉ? | | | 1 | 33.33 | - | - | 2 | 66.66 | - | - |
| 14 | ተማሪዎችዎ የሚሰጣቸውን የክፍልና የቤት ስራ ሰርተው ይመጣሉ? | 1 | 33.33 | 1 | 33.33 | 1 | 33.33 | - | - | - | - |
| 18 | በክፍልም ሆነ ቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አርመው ያውቃሉ | - | - | 3 | 100 | - | - | - | - | - | - |
| 4 | ተማሪዎችዎን በሬዲዮ ካዳመጡት፡ በቴሌቪዥን ካዩትና ከሰሙት በጋዜጣ ካነበቡት ሃሳብ እንዲሰበስቡ ያደርጋሉ? | - | - | - | - | - | - | 2 | 66.66 | 1 | 33.33 |
| 7 | ተማሪዎቹ የጽህፈት ችሎታቸውን ለማሻሻል የተለያዩ ነገሮችን የማንበብ ልምዳቸው ምን ያህል ነው? | - | - | - | - | - | - | - | - | 3 | 100 |
| 6 | እርስዎ ጽህፈትን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | - | - | - | - | 1 | 33.33 | 2 | 66.66 | - | - |
| 5 | ጽህፈትን ለመለማመድ ተማሪዎቹ በግልና በቡድን የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | - | - | 1 | 33.33 | - | - | 1 | 33.33 | 1 | 33.33 |

አማራጭ:-

1. ዘወትር አዎንታዊ
2. አብዛኛውን ጊዜ አዎንታዊ
3. በመጠኑ አዎንታዊ
4. አብዛኛውን ጊዜ አሉታዊ
5. ፍፁም አሉታዊ

የጽህፈት ልምምዱን በተመለከተ ሠንጠረዥ 7 ና 8 ሲተነተኑ ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የተገኙት መረጃዎች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ መምህራኑ በጽሑፍ የሚመለስ የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ ስለመስጠታቸው በተጠየቁት መሠረት ተማሪዎቹም ሆነ መምህራን በአብዛኛው እንደማይሰጡ አሉታዊ የሆነ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹ ግን የተሰጣቸውን የቤትም ሆነ የክፍል ስራ ሰርተው ለመምጣታቸው ከመምህራኑ አዎንታዊ መልስ ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም መምህራኑ በክፍል ሦስት የመጠይቁ ክፍት ጥያቄ ላይ በሰጡት አስተያየት ደግሞ አብዛኞቹ ተማሪዎች ሰርተው እንደማይመጡ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የሐሳብ መቃርን ታይቶበታል፡፡ ጽህፈትን በማለማመድ በኩል መምህራኑ ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎቹም ሆነ መምህራኑ አሉታዊ መልስ ሰጥተውበታል፡፡ ስለዚህ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን ጽህፈት በማለማመድ በኩል ደካማ ናቸው ሊባል ይቻላል፡፡ የጽህፈት ልምምዱን ሊያዳብሩ የሚችሉ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች ድጋፍ ምን ያህል እንደሆነም ተጠይቀው ሲመልሱ የሁለቱም መልስ አሉታዋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ጽህፈትን ለማለማመድ መምህራኑ ዕውቀት ያላቸው ለመሆኑ ከተማሪዎቹ በኩል አዎንታዊ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ ሲታይ ሁለቱ በዲፕሎማ አንዷ በዲግሪ የተመረቁ በመሆናቸውና በዲግሪ የተመረቀችውም በዋና ትምህርት ሳይሆን በንዑስነት ያጠናቸው በመሆኑ በዲፕሎማ የተመረቁትም ቢሆን የ13 ና 14 ዓመት አገልግሎት ያላቸው ሲሆኑ ከኮሌጅ ከወጡ በኋላ ምንም አይነት የሙያ ማሻሻያ ትምህርት ባለማግኘታቸውና እንዲያውም ሁለቱ መምህራን በኦሮምኛ ቋንቋ አፈፌት በመሆናቸው በቤትና በክፍል ስራ ልምምዱ ላይ ያላቸው ጥረት አነስተኛ ሊሆን ችሏል፡፡

ስለዚህ ከሰንጠረዥ 8 እና 9 የቀረቡት መረጃዎችና ሌሎችም እንደሚጠቁሙት ጽህፈትን ለማለማመድ በመምህራኑ በኩል ያለው ልምድ ፍላጎትና ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም የመምህራኑ የትምህርት ደረጃ፣ ዕውቀት፣ ፍላጎትና ጥረት ዝቅተኛ መሆን በጽህፈት ልምምዱ ላይ ለሚፈጠሩት ችግሮች የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ሠንጠረዥ 9 የክፍልና የቤት ስራ ልምምድን በሚመለከት የተማሪዎች መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | |
| 9 | መምህሩ አንቀጽ ወይም ድርሰት ማፃፍ የሚያስችሉ የክፍልና የቤት ስራ ሰጥተው ያውቃሉ? | 10 | 4.17 | 56 | 23.33 | 46 | 19.17 | 100 | 43.33 | 24 | 10 |
| 10 | መምህሩ የሚሰጡትን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ አርመው ይመልሳሉ? | 54 | 22.5 | 37 | 15.41 | 86 | 35.83 | 28 | 11.66 | 35 | 14.55 |
| 3 | ጽሀፈትን ለማለማመድ የመምህሩ ጥረት ምን ያህል ነው? | 10 | 4.17 | 33 | 13.75 | 70 | 29.17 | 112 | 46.60 | 15 | 6.25 |
| 9 | ጽሀፈትን በማለማመድ በኩል የመምህሩ ዕውቀት ምን ያህል አጥጋቢ ነው? | 13 | 5.41 | 37 | 15.41 | 88 | 36.66 | 60 | 25.00 | 42 | 17.5 |
| 6 | መልመጃዎች ታርመው መመለሳቸው ለጽሀፈት ክሂሉ መዳበር የሚሰጡት ጠቀሜታ ምን ያህል ነው? | 98 | 40.83 | 79 | 32.91 | 36 | 15 | 17 | 7.08 | 10 | 4.17 |
| 10 | በት/ቤቱ የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ክበባት ለጽሀፈት ለምምዱ ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? | 29 | 12.08 | 22 | 9.17 | 48 | 20 | 91 | 37.91 | 50 | 20.83 |

አማራጮች፡-

1. ዘወትር አዎንታዊ
2. አብዛኛውን ጊዜ አወንታዊ
3. በመጠኑ /በመካከለኛ ደረጃ/ አዎንታዊ
4. አብዛኛውን ጊዜ አሉታዊ
5. ፈፅሞ አሉታዊ

ኖሪሽ/1990 ፡ 12-15/ እንደሚሉት ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ በቋንቋው ትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣ በምሳሌዎቹ አማካኝነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትና በሠንጠረዥ 9 የቀረቡት መረጃዎችም ይህንኑ የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

## ሠንጠረዥ 10 በጽህፈት ልምምዱ ጊዜ የመምህራኑን የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ለመምህራኑ የቀረበ መጠይቅ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመምህራኑ | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 17 | ተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፉ ሲደረግ ርዕሱ በማን ይመረጣል? | | |
| | 1. በመምህሩ | 1 | 33.33 |
| | 2. በተማሪዎቹ | - | - |
| | 3. በመምህሩና በተማሪዎቹ | - | - |
| | 4. በመማሪያ መጽሐፍ የቀረበው ርዕሰ ተግባራዊ ይሆናል | 2 | 66.66 |
| | 5. ከላይ በተዘረዘሩት በሁሉም ይመረጣል | - | - |
| 16 | በክፍልም ሆነ በቤት ስራ ተማሪዎቹን ድርሰት እንዲፅፉ የሚያደርጉበት ጊዜ | | |
| | 1. በሳምንት አንድ ጊዜ | - | - |
| | 2. በየሁለቱ ሳምንት | - | - |
| | 3. በወር አንድ ጊዜ | - | - |
| | 4. በየሦስት ወሩ | - | - |
| | 5. ሁኔታው ሲጋብዝ | 3 | 100 |
| 9 | ጽህፈትን ለማለማመድ የሚጠቀሙበት መንገድ የትኛው ነው? | | |
| | 1. ርዕስ ሰጥቶ አንቀጽ እንዲመሰረቱ ማድረግ | 3 | 100 |
| | 2. አንቀስ ሰጥቶ ተማሪዎቹ አንቀፁን እንዲመረምሩት በማድረግ | - | - |
| | 3. አስተዋጽኦ ነድፈው ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ | - | - |
| | 4. ተማሪዎቹ የራሳቸውን ርዕስ መርጠው እንዲፅፉ በማድረግ | - | - |
| | 5. ሁሉንም መንገድ በመጠቀም | - | - |
| 7 | በክፍል ውስጥ ጽህፈት በሚያለማመምዱበት ጊዜ ስሊቃላት አመሰራረትና የዐ.ነገር አገነባብ አስተምረው ያውቃሉ? | | |
| | 1. ዘወትር አስተምራለሁ | - | - |
| | 2. አብዛኛውን ጊዜ አስተምራለሁ | 2 | 66.66 |
| | 3. በመጠኑ አስተምራለሁ | - | - |
| | 4. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ | 1 | 33.33 |
| | 5. እንዳመቺነቱ አስተምራለሁ | - | - |
| 10 | የድርሰት ትምህርት ለማስተማር የትኛው ዘዴ የተሻለ ይመስልዎታል? | | |
| | 1. የድርሰት አፃፃፍ ህጐችን አስቀድሞ ማስተማር | 3 | 100 |
| | 2. በመጀመሪያ ተማሪዎቹ እንዲፅፉ በማድረግ | - | - |
| | 3. ራሳቸው ከጻፉት ድርሰት በመነሳት የድርሰት አፃፃፍ ህጐችን እንዲያወጡ በማድረግ | - | - |
| | 4. በተማሩት ህግ መሰረት አንቀጽ ብሎም ድርሰት እንዲፅፍ በማድረግ | - | - |
| | 5. አስተዋጽኦ ነድፈው በነደፉት መሰረት እንዲፅፉ በማድረግ | - | - |
| 13 | ጽህፈትን ለማለማመድ የሚያስችሉ የክፍልም ሆነ የቤት ስራዎችን አልፎ አልፎ የሚሰጡ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል? | | |
| | 1. ጽህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ በመሆኑ | - | - |
| | 2. ለአማርኛ የተሰጠው ክ/ጊዜ ጽህፈትን ለማለማመድ ስለማያስችል | 2 | 66.66 |
| | 3. በጽሑፍ የሚመላስ ጥያቄ በመማሪያ መጽሐፍ በስፋት ስለማይዘጋጅ | 1 | 33.33 |
| | 4. የተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጐት አነስተኛ በመሆኑ | - | - |
| | 5. ጽህፈትን ማስተማር ጠቀሜታው አነስተኛ በመሆኑ | - | - |
| 15 | ተማሪዎችዎ የሚሰጣቸውን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ በአብዛኛው የማይሰሩ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይምስልዎታል? | | |
| | 1. ተማሪዎቹ ትምህርቱን ስለሚንቁት | - | - |
| | 2. የጽህፈት ስራ አስቸጋራ በመሆኑ | - | - |
| | 3. ተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጐት ስለሌላቸው | 1 | 33.33 |
| | 4. በመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት የሚመረጡት ርዕሶች የተማሪዎቹን ፍላጐት ባለመያዛቸው | 2 | 66.66 |
| | 5. ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ ስለሚያስቸግራቸው | - | - |
| 20 | እንደየክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አንዳንድ ጊዜ የሚያርሙ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል? | | |
| | 1. የተማሪዎቹ ቁጥር በርካታ በመሆኑ | 2 | 66.66 |
| | 2. ተማሪዎቹ መልመጃውን ሰርተው ስለማይመጡ | - | - |
| | 3. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ | - | - |
| | 4. በታረመው መሰረት ተማሪዎቹ ጽህፈታቸውን ለማሻሻል ስለማይጥሩ | - | - |
| | 5. በቂ ክ/ጊዜ ባለመስጠቱ | 1 | 33.33 |

በሰንጠረዥ 10 የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ ድርሰት የሚፅፉበት ርዕስ የተማሪዎቹን ፍላጐት ባለመያዙ፣ መምህራንም ድርሰት የሚያጽፉት በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል ሳይሆን ሁኔታው ሲጋብዝ /እንደአመቺነቱ/ በመሆኑ፣ ድርሰትን ለማፃፍ በአብዛኛው የሚቀጠሙበት መንገድ ርዕስ ሰጥቶ አንቀጽ እንዲፅፍ የሚያደርግ እንጅ በተለያየ መንገድ እነዲፅፉ የሚያደርግ ባለመሆኑ በክፍል ውስጥ ስለቃላት አመሰራረትና ዐ.ነገር አገባብ አንዳንድ ጊዜ በማስተማራቸው፣ ድርሰትን ለማፃፍም የተሻለ መንገድ ነው ብለው የሚያስቡትና የሚያስተምሩት አስቀድመው የድርሰት አፃፃፍ ህጐችን በማስተማር እንጅ ተማሪዎቹ ከሚጽፉት ድርሰት በመነሳት ህጉን ራሳቸው እንዲያወጡ ወይም ሌላ የተሻለ መንገድ በመፈለግ እንዲፅፍ የሚያስችሉ ባለመሆናቸው፣ ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ጽህፈትን ማለማመድ ባለመቻሉና የተማሪዎቹ ቁጥር በርካታ በመሆኑ ለማረም አስቸጋሪ ስለሆነና ከስህተታቸውም ሊማሩ ባለመቻላቸው ስህተቶቹ ሊፈፀሙ ችለዋል፡፡ ይህንኑ በተመለከተም ማረው /19987 : 1/ የተማሪዎች ድርሰት በስህተት የተሞላ መሆኑንና የስህተቶቹ መከሰት ምናልባትም ከመምህራኑ የማስተማር ስልትና መጻህፍት በብዛት ካለመዘጋጀታቸው የተነሳ ሊሆን እንደሚችል ኃይለ ሚካኤል /1993/ ን በመጥቀስ ገልፀውታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ተስፋዬ /1986 : 9-10/ እንደሚሉት በተማሪዎች ቁጥር መጨመርና ለአማርኛ ቋንቋ የተሰጠው ክፍል ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ እየተመካኘ ተማሪዎቹ የሚጽፉት ነገር ትክክል ይሁን ስህተት ሳይታረም በመቅረቱ በጽህፈት ላይ ችግር ሊያስከትል እንዳቻለ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደካማ የማስተማር ዘዴ ለስህተት መፈጠር ምክንያት ከመሆን ባያልፍም መርሃ ትምህርቱና የማስተማሪያ መጽሐፉ በሚታዩበት ጊዜ ከመምህራኑ ውጭ በመሆናቸው ስህተት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ /ብራውተን፣ 1993 : 133-5/

ሠንጠረዥ 11፡ <u>ጽህፈትን ለማለማመድ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን ማቴሪያሎች በተመለከተ የመምህራን መጠይቅ ምላሾች</u>

| ተ.ቁ. | | የመምህራን | |
|---|---|---|---|
| | | ብዛት | % |
| 1 | በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡት መልመጃዎች በአብዛኛው የማያዳብሩት የቱን ነው?<br>1. ማደመጥና መናገር<br>2. ማንበብን<br>3. ጽህፈትን<br>4. ስነልሳንን<br>5. ስነ ጽሑፍን | -<br>-<br>1<br>-<br>2 | -<br>-<br>33.33<br>-<br>66.66 |
| 2 | ለጽህፈት ልምምዱ በይበልጥ የሚያግዙ መልመጃዎች የትኞቹ ናቸው?<br>1. መልመጃ አንድ<br>2. መልመጃ ሁለት<br>3. መልመጃ ሦስት<br>4. መልመጃ አንድና ሁለት<br>5. መልመጃ ሁለትና ሦስት | -<br>-<br>2<br>-<br>1 | -<br>-<br>66.66<br>-<br>33.33 |
| 3 | የጽህፈት ትምህርትን በምን ላይ ተመርኩዘው ያስተምራሉ?<br>1. በመማሪያ መጽሐፍ<br>2. በመርሃ ትምህርቱ<br>3. በመርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ<br>4. ከመርሃ ትምህርቱና ከመጽሐፍ ውጭ<br>5. በመርሃ ትምህርቱ በመማሪያ መጽሐፍና ከመጽሐፍ ውጭ | -<br>-<br>3<br>-<br>- | -<br>-<br>100<br>-<br>- |
| 5 | መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍ ጽህፈት የሚዳብርበትን መመሪያና ዝርዝር ሃሳቦቹን ይዘዋል?<br>1. ሙሉ በሙሉ ይዘዋል<br>2. በአብዛኛው ይዘዋል<br>3. በመጠኑ ይዘዋል<br>4. አልፎ አልፎ ይዘዋል<br>5. ምንም አልያዙም | -<br>-<br>1<br>2<br>- | -<br>-<br>33.33<br>66.66<br>- |

በሰንጠረዥ 11 ከቀረበው የመጠይቅ ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለው በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡት መልመጃዎች በአብዛኛው የስነ ጽሑፍ እውቀትን እንደሚያዳብሩ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ሦስት መልመጃዎች መካከልም ለጽህፈት ልምምዱ እገዛ የሚያደርገው መልመጃ ሦስት ሲሆን

ሦስት ሲሆን ይህም ካለው የክፍለ ጊዜ እጥረት የተነሳ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ጽህፈት የሚዳብርበትን መመሪያና ዝርዝር ሃሳቦች ስለመያዛቸው ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ አልፎ አልፎ ይዘዋል የሚል ሲሆን መምህራኑም መርሃ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፍን ብቻ ተመርኩዘው ጽህፈትን የሚያስተምሩ በመሆናቸው በጽህፈት ልምምዱ ላይ ችግር ሊከሰት እንደቻለ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም የመምህራኑን የትምህርት አቀራረብ፣ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት ያላቸውን አስተዋጽኦ በሚመለከት ለተማሪዎቹ በተራ ቁጥር 11፣ 12 ና 13 እንዲሁም በመጠይቁ ክፍል ሁለት መመሪያ ሁለት በተራ ቁጥር 4 ና 5 የቀረቡት የመጠይቅ መልሶች በተማሪዎቹ ቁጥር መብዛትና የክፍለ ጊዜው ማነስ የተነሳ መምህራን ማረም ስለመቸገራቸው፣ የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ጽህፈትን በስፋት እንዲለማመዱ የማያስችል እንደሆነ፣ የመማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎችም በአብዛኛው ጽህፈትን እንደማያለማምዱና በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት መመሪያዎችም ጠቀሜታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

ብራውን /1994 ፡ 215-7/ እንደሚሉት በት/ቤት ውስጥ በሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከመምህሩ አቀራረብ ወይም ደግሞ ከክፍል ውጭ ባለው አስገዳጅ ሁኔታ የተነሳ ስህተት ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህም ከመምህሩ በሚሰጠው የተሳሳተ ገለፃ የተዛባ የቋንቋ አወቃቀር በመጽሐፍ ውስጥ በሚሰጠው የተሳሳተ ገለፃ የተዛባ የቋንቋ አወቃቀር በመጽሐፍ ውስጥ በሚቀርበው መልመጃ ወይም ከተደረገው ልምምድ መካከል ተማሪው የሚያስበውን በማስታወሱ ... ከአውዱ ውጭ በመሆናቸው ስህተት ሊከሰት ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ በጽህፈት በሚግባቡት ጊዜ አስፈላጊውን ፍች ለማግኘት ሲፈልጉ ከዚያ ጋር ለሁኔታው የሚስማማ ቃል በመፍጠር በወቅቱ ለተከሰተው ችግር መፍትሔ ይፈልጉለታል፡፡ በዚህም የተነሳ ስህተት ሊፈጠር ይችላል /ሊትልውድ 1986 ፡ 30-1/፡፡

ስለሆነም በስህተት ትንተናው ከተገኙት መረጃዎች፣ ከመምህራኑና ከተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች እንዲሁም ከተዛማጅ ጽሑፎች የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎቹ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ምክንያቶቹ የመምህራኑ የማስተማር ዘዴ፣ የመርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ ማነስ፣ የተማሪዎቹ ቁጥር

ቁጥር መብዛትና መልመጃዎቹ በወቅቱ ታርመው አለመመለሳቸው ... ሲሆኑ በጥቅሉም የመማር ማስተማሩ ሂደት እንደ አንድ የስህተት ምንጭ ይሆናል ተብሎ ተገምቷል፡፡

### 4.2.4 ስነ ልቡናዊ ሁኔታዎች

ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የስህተት ምንጮች በተጨማሪ ተማሪዎቹን ስህተት እንዲፈፅሙ የሚያደርጓቸው ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች እንዳሉ ይገመታል፡፡

ስነ ልቡናዊ ሁኔታዎች ከተማሪዎቹ የግል ጉዳይ ጋር የሚያያዙ ሲሆኑ ይህም ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአእምሮአቸው ይዘውት የመጡት ጉዳይ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉት ያደርጋቸዋል፡፡

ኖሪሽ /1990 ፡ 19/ ኮርደርን በመጥቀስ በዚህ አይነት ሁኔታ የሚፈፀሙትን የስህተት አይነቶች አላስፈላጊ ድግግሞሽ ናቸው ይላሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በተደረገው የስህተት ትንተና በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ የስህተት ዓይነት ምድብ ውስጥ ከተዘረዘሩት ንዑሳን ስህተቶች አንዱ አላስፈላጊ ድግግሞሽ እንደነበር በ4.1.2.5 መገለፁ ይታወሳል፡፡ ለምሳሌም የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- ይህን ያህል ትብብር ይህን ያህል ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ ምድርን ለማጥፋት ...
- አንድ ተማሪ የወደፊት ምኞት ብዙ ነገር ይመኛል

እነዚህ የተሰመረባቸውና ሌሎችም ተመሳሳይ ስህተቶች በሚታዩበት ጊዜ በአጣማሪዎች መጠቀም ሲቻል በመደጋገማቸው ስህተት ሊከሰት ችሏል፡፡

ግዴለሽነትን ለስህተት መፈጠር እንደ ምክንያት አድርገው የሚቆጥሩ ቢኖሩም ምሁራን ግን ለመማር ካለ ፍላጐት መቀስቀስ ጋር ያገናኙታል፡፡ ይህም ምናልባትም የትምህርቱ አቀራረብ ወይም ደግሞ ለትምህርቱ የቀረበው ነገር ከተማሪው ፍላጐት ጋር ባለመስማማቱ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋን ብሎም የጽህፈት ልምምዱን በተመለከተ ተጠኝ ተማሪዎቹ ያላቸውን ፍላጐት ለመረዳት ከመምህራኑና ተማሪዎቹ የመጠይቅ መልሶች የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አብዛኞቹ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የሚገቡት ለመማር ፍላጐት ኖሯቸው ሳይሆን ቁጥጥሩን ከመፍራት ሳይሆን እንዳልቀረነው፡፡ ለዚህም ከመምህራኑ የተሰጠው አስተያየት በአሁኑ ሰዓት ከአማርኛው ቋንቋ ጐን ለጐን የኦሮምኛ ቋንቋ የሚሰጥ በመሆኑ ምናልባት የዚህ ተፅዕኖ ሳይሆን አይቀርም የሚል ነው፡፡ በማመሪያ መጽሐፍ ጽህፈትን ለማለማመድ የቀረቡት መልመጃዎች የተማሪዎቹን ፍላጐት ሰለመያዛቸውና ብንሰራም እንሳሳታለን ስለሚሉ፣ እንዲሁም ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ የማንበብ ልምዳቸው ያልዳበረ በመሆኑ የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ ለመስራት ያላቸው ፍላጐት አነስተኛ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በክፍልም ሆነ በቤት ስራ የሰሩትን መልመጃ እንዲያነቡ ሲጠየቁ አብዛኞቹ አልሰራንም ማለት እንደሚቀናቸው ነው፡፡ ይህም የሚሆንበትን ምክንያት መምህራኑም ሆነ ተማሪዎቹ እንደገለፁት ተማሪዎቹ ክፍል ውስጥ በሚያነቡበት ጊዜ ስለሚንተባተቡ በጓደኞቻቸውም ሆነ በአስተማሪያቸው ዘንድ ይሳቅብናል፣ ይፌዝብናል ... ከሚል ፍርሃት የተነሳ እንደሆነ ነው፡፡ እንዲያነቡ ቢገደዱም እንኳን ይሳሳታሉ፡፡ ስለሆነም በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች የተማሪዎቹ ፍላጐት ቋንቋውን ለመማር ባለመቀስቀሱ ስህተቶች ይፈፀማሉ፡፡

ስለዚህ በነዚህ በጥናቱ የስህተት ትንተናና ከተማሪዎቹም ሆነ ከመምህራኑ የመጠይቅ መልሶች እንዲሁም ከተዛማጅ ጽሑፎች በተገኙት መረጃዎች መሰረት ስነ ልቡናዊ ሁኔታዎች ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ተብሎ ተገምቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ የተደረሰበት ማጠቃለያና ከጥናቱ ጋር በተዛመደ መልክ በአጥኚዋ የተሰጡ አስተያየቶች ይቀርባሉ፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

የሰው ልጅ ሐሳቡን ለሌሎች ቀርጾ ለማቆየትና ለማስተላለፍ ይችል ዘንድ የጽህፈት ክሂል ትምህርት እንደሚያስፈልገው ይታመናል፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ተነድፎለት ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የአማርኛ የጽህፈት ትምህርት ሲሰጥ የቆየ ለመሆኑ በተለያዩ ጊዜያት ታትመው ከወጡ በርካታ ጽሑፎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው ይህን ጥናት ለማካሔድ ያነሳሳው ጉዳይ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ አቀናብረው የመግለፅቸው ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ በበርካታ ጥናቶች እንደተጠቀመው እየተዳከመ በመሔዱ ነው፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት አላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች በስህተት ትንተና ዘዴ በመመርመር የሚያጋጥሟቸውን ዋና ዋና ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ለመለየት፣ ብሎም ለስህተቶቹ መቃለል የመፍትሔ ሐሳብ ለመጠቆም ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ እንዲመልሳቸው በመጀመሪያ የተነሱት መሠረታዊ ጥያቄዎች ቀጥሎ ያሉት ነበሩ፡፡

1. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት አይነቶች ምን ምን ናቸው?
   - ብዛታቸውስ ምን ያህል ነው?
   - ድግግሞሻቸውስ?
2. የስህተት ምንጮቹ ምን ምን ናቸው?

እነዚህን የጥናቱ ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል በመጀመሪያ ተጠኚዎቹ ተጠኚዎቹና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ተመርጠዋል፡፡ ተጠኚዎቹ

በሙከጡሪ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ፣ በፍቼ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃና በገብረጉራቻ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ በጥናቱ ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት በአንድ በኩል ተማሪዎች ድርሰት ፅፈዋል። በሌላ በኩል ተጠኚ ተማሪዎችና መምህራን መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መሳሪያዎች በድርሰትና በመጠይቅ አማካኝነት ከተሰበሰቡ በኋላ በስህተት ትንትና የአጠናን ዘዴ አማካኝነት ስህተቶች በአይነት ተለይተውና ተቆጥረው ተተንትነዋል። በትንተናው በተገኘው ውጤት መሰረትም የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ተመልሰዋል። በመሆኑም በጥናቱ ውስጥ የተተኮረባቸው አቢይ የስህተት አይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተቶችና ለመለየት ያልተቻሉ የስህተት አይነቶች ናቸው።

## የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት አይነት

የስህተት አይነቱ አማካይ ድግግሞሽ 12.42% ሲሆን በጥናቱ ውስጥ ከተመለከቱት የስህተት አይነቶች ከፍተኛው ነው። የስህተት አይነቱ አጠቃላይ መጠን 45.71 በመቶ እንደሆነም በአቢይ የስህተት ምድቡ የተቆጠረው የስህተት ብዛት አመልክቷል። ከተፈፀሙት 12.42% የቋንቋ አጠቃቀም የስህተት አይነቶች ውስጥ የተፈፀሙ ንዑሳን የስህተት አይነቶች ያሉ ሲሆኑ የእነዚህም ስህተቶች ብዛት መቶኛና አማካይ የስህተት ድግግሞሽ በሚታይበት ጊዜ የቃላት አጠቃቀም የስህተት አይነት መጠን 28.84% (2832) ሲሆን አማካይ ድግግሞሹም 7.84፣ አስፈላጊውን ቃል የመግደፍ (ግድፈት) ስህተት መጠን 5.05% (496)፣ አማካይ ድግግሞሽ 1.37%፣ የኢ.መደበኛ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ስህተት መጠን 4.03% (396) አማካይ ድግግማሽ 1.00፣ የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል ስህተት 3.91% (384) ና አማካይ ድግግሞሹ 1.06፣ አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ ስህተት መጠን 3.87% (380) አማካይ ድግግሞሹ 1.05 ሊሆን ችሏል። /በሠንጠረዥ 4 በገጽ 47 የተገለፀውን መረጃና በ 4.1.2 የቀረበውን ትንተና ይመልከቱ/።

## የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች

በአቢይ የስህተት አይነት ምድብ ከተቆጠሩት ስህተቶች ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛነቱን የያዘ ሲሆን የስህተቱ አጠቃላይ መጠን 19.56% (1920) ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠን 5.31 ሆኗል፡፡ በዚህ አቢይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ካሉት ንዑሳን የስህተት አይነቶች መካከል የዐ.ነገር ስሙሙነት የስህተት መጠን 9% (884) ሲሆን የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠን 2.45% ነው፡፡ የመስተአምር መስተዋድድና ተሳቢ አገባብ የስህተት መጠን 7.78% (764)፣ አማካይ ድግሞሹ ደግሞ 2.11 ሲሆን የአጣማሪዎች አገባብ የስህተት መጠን 2.77% (272)፣ የአማካይ ድግግሞሹ መጠን 0.75 እንደነበር በሰንጠረዥ 4 በገጽ 47 የተገለፀው መረጃና በ4.1.3 የቀረበው ትንተና አመልክቷል፡፡

## የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች

የዚህ አቢይ የስህተት አይነት የስህተት ብዛት 1902 ሲሆን በመቶኛ 19.37ና አማካይ የስህተት ድግግማሹ 5.26 ሆኖ በመገኘቱ በአቢዬ ስህተት አይነቱ ከተቆጠሩት መካከል በ3ኛ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን በጥናቱ የተደረሰበት ውጤት አመልክቷል፡፡ በዚህ አማካይ የስህተት ድግግማሽ መጠን የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት መጠን 15.20% (1492) ና አማካይ ድግግሞሹም 4.13% ነው፡፡ የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም የስህተት መጠን 4.18% (410) ና አማካይ ድግግሞሹ 1.13% ነው፡፡ ስለዚህ በስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ውስጥ የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ጐልቶ የሚታይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ (በሠንጠረዥ 4 ገጽ 47 እና በ 4.1.1 የቀረበውን ትንተና ይመልከቱ)፡፡

## ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች

በተወሰነ የስህተት አይነት ሊመደቡ ያልቻሉትና በ4ኛ ደረጃ የሚገኘው የስህተት አይነት "ለመለየት ያልተቻሉ" ተብለው የተሰየሙት ሲሆኑ የእነዚህ ስህተቶች መጠን 8.03% (788) ሲሆን የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠን 2.18% ነው፡፡ ቀደም ሲል የስህተት አይነቱን መለየት እንዳልተቻለ በተገለፀው መሰረት በዚህ አቢይ የስህተት አይነት ስር የተካተቱ

ንዑሳን የስህተት አይነቶች የሉም፡፡ (በሠንጠረዥ 4 በገጽ 47 የቀረበውን መረጃና በ4.1.5 የቀረበውን ትንተና ይመልከቱ)

## የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተት

የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ አቢይ ስህተት መጠን 7.33% (720) አማካይ የስህተት ድግግሞሹ መጠን 1.99% ነው፡፡ "ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች" ተብለው ከላይ እንደተገለፁት ሁሉ በዚህ አቢይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ ሌሎች ንዑሳን ምድቦች የሉም፡፡ በዚህ የስህተት አይነት ውስጥ የተተኮረበት ጉዳይም ተጠኝ ተማሪዎች ቃላትና ሐረጋቱ በውስጣቸው የያዙትን ጽንሰ ሐሳብ ካለመገንዘባቸው የተነሳ ተገቢ ባልሆነ ቦታ አስገብተው ሲጠቀሙባቸው በተፈፀሙት ስህተቶች ላይ ነው፡፡

በጥቅሉ በ240 ተጠኝ ተማሪዎች የተፈፀሙት ስህተቶች መጠን 9818 የተፈፀመው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠንም 27.17% ሊሆን ችሏል፡፡

በአማካይ የተፈፀመው የስህተት ድግግሞሽ 27.17 መሆኑ የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ከፍተኛ ችግር ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ በተለይም በአማካይ 12.42% የስህተት ድግግሞሽ በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ የስህተት አይነት ምድብ ውስጥ መፈፀሙ የችግሩን ከፍተኛነት የሚያመለክት ሲሆን፣ ይኸው ችግር ቀደም ሲልም በአለማየሁ /1986 ፡ 123/ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀርቦ ነበር፡፡ ተጠኝዎቹ ከፈፀሟቸው የተለያዩ ስህተቶች መካከል በቋንቋ አጠቃቀም ላይ የተከሰተው ጉልህ ችግር የሚያመለክተው በጽህፈት ልምምዱ ወቅት ለቋንቋ አጠቃቀም ትምህርት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ሲሆን ከመጠይቆቹ መረጃ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው ደግሞ ከሌሎቹ ይበልጥ በዚህ ላይ ትኩረት እንደተደረገበት ነው፡፡ ስለሆነም በውጤቱ ላይ የሃሳብ ቅራኔ ታይቷል፡፡

ከስህተት ትንተናው የተገኘው ውጤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በጽሑፍ ቋንቋ የመገልገል ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው ነው፡፡ ኖሪሽ /1990 ፡ 63-6/ እንደሚሉትም ጽህፈት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ክሂል ከመሆኑ ባሻገር ለቋንቋው አፈፈት ተናጋሪዎችም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከንግግር ይበልጥ አስቸጋሪ ነው፡፡

ስለሆነም በጽሑፍ ቋንቋ ለመግባባት በሚታሰብበት ጊዜ ተማሪዎቹ ከመፃፋቸው በፊት በጥንቃቄ የተሞላ ቅድመ ዝግጅት እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል፡፡ ይህም ባለመሆኑ በጥናቱ ውስጥ በተገለፁት በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ በተማሪዎቹ ድርሰቶች ውስጥ መግባባትን እስከማገድ የሚያደርሱ ስህተቶች ተፈፅመው ተገኝተዋል፡፡

## ዋና ዋና የስህተት ምንጭ መላምቶች

በጥናቱ ከተደረሰበት የድርሰት ስህተት ትንተናና ከመጠይቁቹ ምላሾች የተገኙትን መረጃዎች በማገናዘብ የተደረሰበት ውጤት እንደሚያመለክተው በጥናቱ ውስጥ በአቢይ የስህተት አይነትነት ለተጠቀሙት ስህተቶች ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ተብለው የተገመቱት ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የአፍመፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱና ስነ ልቡናዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

## ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

በ4.2.1 የቀረበው የስህተት ምንጭ ትንተና እንደሚያመለክተው ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ በተጠኝ ተማሪዎቹ ለተፈፀሙት ስህተቶች ምክንያት ሊሆን እንደቻለ ነው፡፡ ለውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ መከሰት ምክንያቱ ስህተተ ብያኔ ሲሆን ለዚህም ተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነውን የአማርኛ ቋንቋ ስርአት አንድ ጊዜ ከለመዱ በኋላ በለመዱት መንገድ አስፋፍተው ለመጠቀም ሲሞክሩ ስህተት የፈፀሙ ለመሆናቸው በጥናቱ ትንተና ከገጽ 79.80 የቀረቡት የምህፃረ ቃላት ምሳሌዎች ማስረጃዎች ናቸው፡፡

ሌላው ነጋራ /1983 ፡ 36-9/ እንደሚሉት ያልተሟላ ትምህርት የተሳሳተ ቅንጅትና ያለአግባብ ቃላትን መጠቀም ለውስጠ ቋንቋ ስህተት መከሰት ምክንያቶች ናቸው፡፡ ያልተሟላ ትምህርት ሲባልም ስህተት ያለበት የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤና ሌሎችንም ያካትታል፡፡ ስለሆነም በጥናቱ በተደረገው የስህተት ትንተና ውጤት መሰረት በአቢይ የስህተት አይነቱ ውስጥ ከተነሱት ስህተቶች ውስጥ አብዛኞቹ ከላይ በተገለፀው መንገድ የተከሰቱ በመሆናቸው ተማሪዎቹ ለፈፀሟቸው አብዛኞቹ ስህተቶች የስህተት ምንጭ ይሆናል ተብሎ ታስቧል፡፡ /ምሳሌዎቹንና ዝርዝሩን በ4.2.1 ከገጽ 79-86 ይመልከቱ/

## የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ

እንደሚታወቀው ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ እየተማረው ሲሄድ የአፍ መፍቻ ቋንቋው ከታላሚው ቋንቋ ጋር ይበልጥ እየተዋሃደ በመሄድ ስህተቶቹ ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ ተብሎ ቢገመትም የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪው ቋሚ ባህሪያት የሆኑ ፈፅሞ የማይጠፉ ስህተቶች /Fossilized Errors/ መኖራቸው እሙን ነው/ ሊትልውድ 1986 ፡ 34 ና ብራውን 1994 ፡ 217/። ስለሆነም በኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊቺ ተጠኝ ተማሪዎች ላይ የዚህ አይነቱ ባህርይ የሚታይ መሆኑን በ4.2.2 የቀረቡት የስህተት ትንተና መረጃዎች ያመለክታሉ።

የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊቺ ተጠኝ ተማሪዎች /1/ በቋንቋቸው ውስጥ "ዝ" ና "ዥ" የሌሉ በመሆናቸው በአማርኛ ቋንቋ "ዝ" ና "ዥ"ን ለመጠቀም ሲፈልጉ "ስ" ና "ጅ" ን ያተካካሉ፣ /2/ በቋንቋቸው ውስጥ ያሉት አናባቢዎች 5 ብቻ ሲሆኑ "ኧ" ና "እ" የተባሉ አናባቢዎች የሏቸውም ስለሆነም "እ" በሚገባበት ቦታ "ኢ" ን "ኧ" በሚገባበት ቦታ አንዳንድ ጊዜ ራብዑ "ኣ"ን ሌላ ጊዜ ደግማ ሐምስ አናባቢ የሆነውን "ኤ" ን እያለዋወጡ ይጠቀማሉ፣ የአማርኛ ግሶች በሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ሲነገሩ የመድረሻ አናባቢው "ኧ" ይሆናል። የኦሮምኛ ግስ ደገሞ በ "ኤ" የመድረስ ፀባይ ስላለው በግዕዝ መድረሻ ያላቸውን ቃላት ሲጠቀሙ ግዕዙን ወደ ሐምስ ይለውጡታል። /ይልማ፣ 1956፣3-39ና የትምህርት ሚኒስቴር፣ 1987 6-9/። በሌላም በኩል በኦሮምኛ ቋንቋ ፆታን የሚያመለክቱ የጠበቁ ህጐች የሌሏቸው በመሆኑ ሴቱንም ሆነ ወንዱን በተባዕታይ ፆታ ይጠሯቸዋል። በቋንቋቸው ውስጥ መስተዋድዶችን በቃል መነሻ ላይ ሳይሆን መድረሻ ላይ የሚጠቀሙ በመሆናቸው በአማርኛው ሲጠቀሙ በማይገቡበት ቦታ ላይ ያስቀምጧቸዋል። /ይልማ፣ 1956 ፡ 32/። ስለዚህ በአብዛኛው በቋንቋ አጠቃቀም እንዲሁም በቋንቋ አወቃቀር ከተፈፀሙት ስህተቶች መካከል ብዙዎቹ በነዚህ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የተፈፀሙ ለመሆናቸው በ4.2.2 የቀረቡት ልዩ ልዩ ምሳሌዎችና መረጃዎች እንዲሁም በሠንጠረዥ 6 የቀረቡት መረጃዎች ያመለክታሉ። ስለሆነም ተጠኝ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ለተፈፀሙት ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አንዱ የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ ታስቧል።

## የመማር ማስተማር ሂደት

በ4.2.3 በገጽ 92-95 እንደተገለፀው በርካታ ስህተቶች በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊካተቱ በሚችሉ ልዩ ልዩ ጉዳዮች አማካኝነት ሊፈፀሙ እንደቻሉ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ በአንድ ክፍል ውስጥ ከሚገኙት በርካታ የተማሪዎች ቁጥር አንፃር ሲታይ ለአማርኛ ቋንቋ የተመደበው ክ/ጊዜ አነስተኛ መሆኑና እንዲያውም ጥናቱ በተካሄደበት አንድ ት/ቤት ከሦስት ወደ ሁለት ክፍለ ጊዜ ዝቅ ማለቱ መልመጃዎች ታርመው እንዳይመለሱና የጽህፈት ልምምዱ በስፋት እንዳይካሄድ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመጠይቁ ከተሳተፉት ሦስት መምህራን ሁለቱ በዲፕሎማ የተመረቁና የረጅም ጊዜ አገልግሎት ያላቸው ሆነው ከተመረቁ ወዲህ የሙያ ማሻሻያ ኮርስ አለመውሰዳቸው፣ አንዷም መምህርት በአቢይ ሳይሆን በንዑስ በሰለጠነችበት ሙያ በማስተማሯ በቂ ልምድና ዕውቀት እንደሌላቸው ከራሳቸው ከመምህራኑ በመገለፁ፣ የጽህፈት ልምምዱን ለማዳበር የሚያስችል የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴ በስፋት ባለመደረጉና የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ባለመገኘቱ ... በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ በጽህፈት ላይ ለሚፈፀሙ ስህተቶች እንደምክንያት ሆኖ ሊቆጠር ችሏል፡፡ ስለዚህ የመማር ማስተማር ሂደት እንደ አንድ የስህተት ምንጭ ሊሆን ችሏል፡፡ /ዝርዝሩን በ4.2.3 በገጽ 92-95 ይመልከቱ/

## ስነልቡናዊ ሁኔታዎች

በ4.2.4 በተገለፀው የጥናቱ የስህተት ትንተና ውጤት መሰረት የተወሰኑ ስህተቶች የተፈፀሙት በስነሥልቡናዊ ሁኔታዎች የተነሳ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡ ስነ ልቡናዊ ሁኔታዎች ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር የሚያያዙ ሲሆኑ ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአእምሮአቸው ውስጥ ይዘው በመምጣት በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ እንዳይከታተሉት ያደርጋቸዋል፡፡ ኖሪሽ /1990 : 19/ ኮርደርን በመጥቀስ በዚህ አይነት ሁኔታ የሚፈፀሙትን የስህተት አይነቶች አላስፈላጊ ድግግሞሽ ናቸው ይሏቸዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ውስጥ በተደረገው የስህተት ትንተና በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ የስህተት አይነት ውስጥ ስለአላስፈላጊ የስህተት ድግግሞሽ የቀረቡ መረጃዎች በ4.1.2.5 ተተንትነዋል፡፡

በሌላም በኩል ከተማሪዎቹና ከመምህራኑ የመጠይቅ መልሶች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና በሌሎችም ምክንያቶች ለመማር ያላቸው ፍላጐት አሉታዊ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ አሉታዊ የመማር ፍላጐት መኖር በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የጽህፈት ልምምድ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ተማሪዎቹ የተለያዩ የስህተት አይነቶችን ሊፈፅሙ ችለዋል፡፡

በጥቅሉ በዚህ ጥናት የተደረሰበት ውጤት የሚያመለክተው የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊቺ ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የጾንስ ሐሳብ ግንዛቤና ሌሎች ለመለየት /ለመፈረጅ/ ያልተቻሉ በርካታ ስህተቶችን መፈፀማቸውን ነው፡፡ የጥናቱ የስህተት ትንተና ውጤት፣ በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የትንተና ውጤትና ከተዛማጅ ጽሑፎች ጋር በመገናዘብ የተወሰዱ መረጃዎች እንደሚጠቁሙትም እነዚህ ስህተቶች በውስጠ ቋንቋ፣ በአፍመፍቻ ቋንቋ፣ በመማር ማስተማር ሂደት፣ በስነልቡናዊ ሁኔታዎችና ሌሎችም ተፅዕ ኖዎች አማካኝነት የተፈፀሙ ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡

## 5.2 <u>አስተያየት</u>

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ወደፊት ምንና እንዴት መስራት እንዳለበት ቀጥሎ ያሉት አስተያየቶች በጥናቱ አቅራቢ ቀርበዋል፡፡

1. ጥናቱ የተካሄደው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊቺ ተማሪዎች ላይ ሲሆን በጥናቱ የተደረሰበት ውጤትም የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የኦሮምኛ አፍፊቺ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ያካትታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አፍፊቺ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ያካትታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ቋንቋዎች ከአንድ ቤተሰብ የመጡ ቢሆኑም እንኳን የየራሳቸው የሆነ መለያ ባህሪ እንዳላቸው ይገመታል፡፡ በዚህ መለያ ባህሪያቸውም የተነሳ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን በሚማሩበት ጊዜ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተነሳ የተለያዩ ስህተቶችን ይፈፅማሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን በቋንቋ አጠቃቀም በቋንቋ አወቃቀርና ሌሎችም የተለያዩ ስህተቶች ሲያጋጥሟቸው እንደተፈጥሮአዊ የተማሪው ጉድለት/ድክመት/ አድርገው ከመቁጠር ይልቅ የችግሩን መንስኤ ተረድተው ለችግሩ መፍትሔ በመስጠት ጽህፈትን

እንዲለማመዱ ቢያደርጓቸው፣

2. መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ወቅታዊና የተማሪዎቹን ፍላጐት የያዙ ቢሆኑና የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ችግር የተመለከቱ ሆነው ቢዘጋጁ፣
3. በት/ቤት ውስኘ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎቹ ቁጥር መብዛት ጋር ተመጣጥኖ ቢቀርብ፣
4. ከንግግር ይልቅ የመፃፍ ክሂል አስቸጋሪ መሆኑን በመገንዘብ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ከዝቅተኛው ክፍል ጀምሮ እስከ ላይኛው ድረስ በንባብና በጽህፈት ልምምዱ ላይ ቢያተኩሩ፣
5. ለመምህራን ከወቅቱ የቋንቋ ትምህርት ስልጠና ጋር የተያያዘ የሙያ ማሻሻያ /ተሃድሶ/ ትምህርት ቢሰጥ፣
6. የመማሪያ መጻህፍት በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅተው በተገቢው ጊዜ ለተማሪዎቹ ቢታደሉ ቀደም ሲል በተለያዩ በርካታ ጥናቶችና አሁን ደግሞ በዚህ ጥናት ውስጥ የታዩት የጽህፈት ችግሮች ሊቀንሱ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

# አምደ ቃላት

| | |
|---|---|
| Absolute Frequency | ፍፁም ድግግሞሽ |
| Conceptual Errors | የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተቶች |
| Convinience Sampling | የምቾት ናሙና |
| Creative Constructing | የፈጠራ ግንባታ |
| Degree of Freedom | የነፃነት ደረጃ |
| Developmental Errors | ዕድገታዊ ስህተቶች |
| Frequency of Errors | የስህተት ድግግሞሽ |
| Fossilized Errors | ፈፅሞ የማይጠፉ ስህተቶች |
| Global Errors | መሠረታዊ ስህተቶች |
| Intra language Interference | ውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ |
| Language Competence | የቋንቋ ችሎታ |
| Language Performance | የቋንቋ ብቃት |
| Local Errors | ውሱን ስህተት |
| Miscellaneous Errors | ለመለየት (ለመፈረጅ) ያልተቻሉ ስህተቶች |
| Mothertongue Interference | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት |
| Non-Systematic Errors | ኢስርአታዊ ስህተቶች |
| Overgeneralization | ስህተተ-ብያኔ |
| Pre-selected Category Approach | ቅድመ ግንዛቤን መሠረት የደረገ ምደባ |
| Purposive Sampling | ሁነኛ (የታመነ) ናሙና |
| Relative Frequency | ተዛማጅ ድግግሞሽ |
| Systematic Errors | ስርአታዊ ስህተቶች |
| T-Calculated | የቲ-ስሌት ዋጋ |
| T-Critical | የቲ-ወሳኝ ዋጋ |
| Techniquies of Error Analysis | የስህተት አተናተን ጥበቦች |
| Transitional Errors | ሽግግራዊ ስህተቶች |

# ዋቤዎች

Bhatia, A. Tavadia. 1974. "An Error Analysis of Students' Composition." IRAL, 12:337-349

Broughten, G. 1993. Teaching English as a Second Language. Routledge, London and New York.

Brown, H. Douglas. 1994. "Principle of Language Learning and Teaching." London: Prentice Hall, Inc.

Corder, S. Pit. 1967. "The significance of Learners Errors." IRAL 5.161-169.

____________. 1971. "IDiosyncratic Dialects and Error Analysis." IRAL, 9/1. pp.147-159.

Cox, Terry B. 1996. "Fransisikos Students and French Immersion Graduates: A Comparison of their Written Errors." The International Abstracting Journal for Language Teachers and Applied Linguists. 29/8.173.

Day. S. 1984. The Writers Work Book. McGraw-Hill Book Company.

Efstathidias, S. and P.King. 1972. "Some Lexical and Structural Errors made by Greek Learners of English." ELT. 26/2-pp. 159-167.

Heaton, J.B. 1988. "Writing English Language Tests. New York: Longman Inc."

Lindmann, Beate. 1996. "The Concept of Error in an Analysis of Learner Language." The International Abstracting Journal for Language. Teachers and Applied Linguists. 29/3.112.

Littlewood, W.T. 1986. Foreign and Second Language Learning. Language Acquision Research and Its Implications for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Lott, David. 1983. " Analyzing and Counteracting Interference Errors." ELT. 37/3. pp. 256-261.

McCretton, E. and N. Rider. 1993. "Errors Gravity and Error Hierarchy. "IRAL. 31: 177-188.

Morrissey, M. 1983. "Toward A Grammar of Learners' Errors." IRAL. 21/3. pp. 196-204.

Nagara, E.A. 1983. "Non-contrastive Errors in African English: Types and Signíficance. IRAL. 21/1. p-35.

Norrish, John. 1990. Language learners and their Errors. London Macmillan Publishers Ltd.

Richard, J.C. 1990. Error Analysis: Perpective on Second Language Acquisition. London: Longman Group UK Ltd.

Schachater. Jacquleyn. 1974. "An Error in Error Analysis." Language Learning 24. pp. 205-214.

Scott M.S. and G.R. Tucker 1974. "Error Analysis and English Language Strategies of Arab Students." Language learning. 24/1. pp. 69-71.

Sheal, P. and R. Omajuwa. 1985. Advanced English Course. Longman Sheck Wah Tong Printing Press Ltd.

Spolisky, Bernand. 1979. "Contrastive Analysis, Error Analysis, Interlanguage and other useful fads." Modern Language Journal. 63/1. p.250

Tushyeh Hannay. 1986. "Linguistic Problems Facing Arab Learners of English. "The International Abstracting Journal for Language Teachers and Applied Linguists. 29/4. p. 255.

Widdowson, H.G. 1979. Teaching Language as Communication. Oxford: Oxford University Press.

ማረው አለሙ:: 1987:: "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል በ2ኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና˙ በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ጥናት" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት):: አዲስ አበባ፣ ድኅረ ምረቃ ት/ቤት:: (ያልታተመ)

ሰሎሞን ተሰማ:: 1987:: "የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሔደ ገላጭ ጥናት::" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት):: አዲስ አበባ፣ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)

ባዬ ይማም:: 1987:: የአማርኛ ሰዋሰው:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

ተስፋዬ ሸዋዬ:: 1986:: አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር:: አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.::

ታደሰ ሣህሌ፡ 1979፡፡ "የአዲስ አበባ 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ጽሑፋዊ ባህርይ፡፡" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል፡፡ (ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ፡፡ (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ 1970፡፡ "የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ሥርአተ ትምህርት ከ7-12ኛ ክፍል"፡፡ አዲስ አበባ፣ በስርአተ ትምህርትና ሱፐርቪዥን መምሪያ የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፡፡ (ያልታተመ)

________________፡፡ 1981፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ ሥርአተ ትምህርት ከ9-10ኛ ክፍል፡፡" አዲስ አበባ፣ በአፀደ ህፃናትና መደበኛ ትምህርት ዋና ክፍል የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፡፡

________________፡፡ 1984፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ ከ9-12ኛ ክፍል፡፡" አዲስ አበባ፣ በአፀ.ሕ/መ/ሥ/ት ዋና ክፍል የአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ፡፡

________________፡፡ 1987፡፡ የዘጠነኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ በአፀ.ሕ/መ/ሥ/ት ዋና ክፍል የአማርኛ ትምህርት ቡድን፡፡ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ነጋሳ እጅታ፡፡ 1965፡፡ "በ1962 ዓ.ም. የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ የስህተት አይነቶች፡፡" (የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ)፡፡ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፡፡ (ያልታተመ)

ክፍሌ ኃብተማርያም፡፡ 1986፡፡ "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ የመገለጽ ችሎታ"፡፡ (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ፣ ድህረ ምረቃ ት/ቤት፡፡ (ያልታተመ)

አለማየሁ ፀጋዬ፡፡ 1986፡፡ "በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ ዋና ዋና ስህተቶችና የስህተት ምንጮች" (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ፣ ድህረ ምረቃ ት/ቤት፡፡ (ያልታተመ)

ይልማ ከበደ፡፡ 1956፡፡ "በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቋንቋቸው ጋልኛ የሆኑ ተማሪዎች የሚያደርጉት የአማርኛ ስህተት" (የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ)፡፡ አዲስ አበባ፣ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)

# አባሪዎች

## አባሪ 1

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት**

**የኢት. ቋ. ጥናት ተቋም**

## በ11ኛ. ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

### የተከበራችሁ ተማሪዎች !

መጠይቁ የተዘጋጀው በሰሜን ኦሮሚያ በሰሳሌ ወረዳ በ_______________ ት/ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፀሙ የስህተት አይነቶችን ፣ የስህተት ምንጮችንና ድግግሞሻቸውን ለመለየት ለተጀመረው የድህረ ምረቃ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አጋዥ የሚያደርጉ መረጃዎችን ለማግኘት በማሰብ ነው::

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤትም የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጽህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች ለመቀነስ ብሎም ለማስወገዱ በመጠኑም ቢሆን ድርሻ እንዳለው ይገመታል:: በመሆኑም ከዚህ ውጤት ለመድረስ የእናንተ ቀና ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ መጠይቁን በጥሞና አንብባችሁ ተገቢውን መልስ ትሰጡ ዘንድ በትህትና ተጠየቃችሁ ::

ስለትብብራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለን !

### ማሳሰቢያ ፦

1. በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም::
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው ::

## ክፍል አንድ

### መመሪያ አንድ ፡-

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በማስተዋል ካነበብክ /ሽ/ በኋላ ተገቢ መልስ ነው ብለህ /ሽ/ የምትገምተውን /የምትገምቺውን /በትክክል አስቀምጥ /ጪ/

1.1. ጾታ ________

1.2. ዕድሜ ________

1.3. አፍ የፈታህበት /የፈታሽበት /ቋንቋ ________

1.4. አፍ ከፈታህበት /ከፈታሽበት/ ሌላ የምትናገረው/የምትናገሪው ቋንቋ ካለ /ቋንቋዎች ካሉ ________ ፣ ________ ፣ ________

1.5. ከቤተሰቦችህ/ሽ/ የምትገባባበት /የምትገባቢበት /ቋንቋ ________ ፣ ________

1.6. ከወላጅ ፣ ከዘመድ ፣ ከጓደኛ ... ጋር ደብዳቤ የምትለዋወጥበት /የምትለዋወጪበት /ቋንቋ ________

## ክፍል ሁለት

### መመሪያ አንድ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አማራጭ መልሶች ቀርበዋል:: ስለሆነም ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ ካነበብክ /ሽ/ በኋላ ተገቢ መልስ ነው ብለህ /ሽ/ የምትገምተውን የምትገምቺውን /በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ"✓" ምልክት በማስቀመጥ አመልክት / አመልክቺ /::

1. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ ተገኛለህ /ሽ /?
   1.1. አዘውትሬ አገኛለሁ ☐
   1.2. አብዛኛውን ጊዜ አገኛለሁ ☐
   1.3. በመጠኑ አገኛለሁ ☐
   1.4. አልፎ አልፎ አገኛለሁ ☐
   1.5. በወር አንድ ጊዜ አገኛለሁ ☐

2. በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልሱ ከ1.3—1.5 ያለው ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ?
   2.1. የትምህርት አሰጣጡ ስለማይበብ ☐
   2.2. የቤት ስራ በወቅቱ ስለማልሰራ ☐
   2.3. ባልማርም ስለማውቀው ☐
   2.4. በአብዛኛው የማልገለገልበት በመሆኑ ☐
   2.5. ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ☐

3. የአማርኛን ቋንቋ ትወደዋለህ /ትወጅዋለሽ /?
   3.1. ሙሉ በሙሉ አወደዋለሁ ☐
   3.2. በአብዛኛው አወደዋለሁ ☐
   3.3. በመጠኑ አወደዋለሁ ☐
   3.4. በከፊል አወደዋለሁ ☐
   3.5. አልወደውም ☐

4. በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ 3.1 ወይም 3.2 ከሆነ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል ?
   4.1. ከማህበረሰቡ ጋር በስፋት ስለምግባባበት ☐
   4.2. የስራ ቋንቋ በመሆኑ ☐
   4.3. የራሴን ማንነት ስለምገልፅበት ☐
   4.4. ትምህርቱ በሚገባ ስለሚሰጥ ☐
   4.5. ለመማር ቀላል በመሆኑ ☐

5. በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ 3.3 ፣ 3.4 ወይም 3.5 ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል ?

5.1. ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ☐

5.2. ትምህርቱ ስለማይገባኝ ☐

5.3. በኑሮዬ ውስጥ ብዙ ስለማልጠቀምበት ☐

5.4. በተፅዕኖ እንዲማር ስለተደረገ ☐

5.5. ብማርም ባልማርም ስለማውቀው ☐

6. በኦሮምኛ ቋንቋ አፍን/አፌን/ የፈታ / የፈታች / ተማሪ በአማርኛ ቋንቋ ጽህፈትን ለመለማመድ ፍላጎት አለው /አላት ብለህ /ሽ/ ትስማማለህ /ትስማሚያለሽ /?

6.1. እጅግ በጣም እስማማለሁ ☐

6.2. በጣም እስማማለሁ ☐

6.3. በመጠኑ እስማማለሁ ☐

6.4. አንዳንድ ጊዜ እስማማለሁ ☐

6.5. ምንም አልስማማም ☐

7. በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ መልሱ 6.1 ፣ 6.2 ና 6.3 ከሆነ ምክንያቱ ምን ይሆናል ብለህ /ሽ/ ትገምታለህ /ትገምቻለሽ /?

7.1. ሩቅ ቦታ ለሚኖር ወዳጅ ዘመድ በደብዳቤ መልዕክት ለማስተላለፍ በማስ ቻሉ ☐

7.2. የሰው ልጅ ምኞቱንና ሃሳቡን በስፋት ሊገልፅበት ስለሚችል ☐

7.3. ስራ ለማግኘት ማመልከቻ የሚፃፈው በዚሁ ቋንቋ በመሆኑ ☐

7.4. ተማሪዎች የስነ ጽሑፍ ዕውቀታቸውን የሚገልፁበት በመሆኑ ☐

7.5. ቋንቋው የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ ስለሆነ ከእነሱ ጋር በጽህፈት አማካኝነት ለመግባባት ስለሚረዳ ☐

8. በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ 6.4 ወይም 6.5 የሚሆን ከሆነ ምክንያቱ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ /ትገምቻለሽ /?

8.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ጣልቃ እየገባ ስለሚያስቸግረኝ ☐

8.2. የአማርኛ ቋንቋን ሰርአት በደንብ ባለመረዳቴ ስለምሳሳት ☐

8.3. በምጽፍበት ጊዜ ቃላት ስለሚያጥሩኝ ☐

8.4. የፃፍኩትን በክፍል ውስጥ ሳነብ መምህሩና ተማሪዎች ስለሚስቁብኝ ☐

8.5. የጽህፈት ስራ አስቸጋሪ በመሆኑ ☐

9. መምህሩ አንቀጽ ወይም ድርሰት ማፃፍ የሚያስችሉ የክፍልና የቤት ስራዎችን ሰጥተው ያውቃሉ ?

9.1. ዘወትር ይሰጧሉ ☐
9.2. በአብዛኛው ይሰጧሉ ☐
9.3. በመጠኑ ይሰጧሉ ☐
9.4. አንዳንድ ጊዜ ይሰጧሉ ☐
9.5. ሰጥተውም አያውቁ ☐

10. መምህሩ የሚሰጡትን የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ አርመው ይመልሳሉ ?

10.1. ሙሉ በሙሉ ይመልሳሉ ☐
10.2. በአብዛኛው ይመልሳሉ ☐
10.3. በመጠኑ ይመልሳሉ ☐
10.4. አንዳንድ ጊዜ ይመልሳሉ ☐
10.5. መልሰውም አያውቁ ☐

11. በተራ ቁጥር 10 ለቀረበው ጥያቄ መልሱ 10.4 ወይም 10.5 ከሆነ ችግሩ ምን ይሆናል ብለው ይገምታሉ?

11.1. የተማሪዎች ቁጥር በርካታ በመሆኑ ☐
11.2. መምህሩ ለማረም ስለሚሰንፉ ☐
11.3. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ ☐
11.4. የተማሪዎች ስራ ስለማይጥማቸው ☐
11.5. ምክንያቱ አይታወቅም ☐

12. መምህሩ ጽሁፈትን በሚያለማምዱበት ጊዜ ይበልጥ ትኩረታቸው ምን ላይ ነው ?
/መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል /

12.1. በዐ. ነገር ግንባታ ነው ☐
12.2. በሰርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ነው ☐
12.3. በቃላት አጠቃቀም ላይ ነው ☐
12.4. በፅንሰ - ሃሳብ ግንዛቤ ላይ ነው ☐
12.5. በአስተዋጽኦ አነዳደፍ ላይ ☐

13. ተማሪዎች የጽሁፈት ክሂሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ መምህሩ የሚጠቀሙበት መንገድ ምንድን ነው ?

13.1. ከተለያዩ መጻህፍትና ጋዜጦች ያነበቡትን አሳጥረው እንዲፅፉ በማድረግ ☐
13.2. ርዕስ ሰጥተ እንዲጽፍ በማድረግ ☐
13.3. ከሬዲዮ ያዳመጡትንና በቴሌቪዥን የተከታተሉትን አቀናብረው ጽፈው እንዲያመጡ በማድረግ ☐

13.4. ተማሪዎቹ በፈለጉት ርዕስ ድርሰት ጽፈው እንዲመጡ በማድረግ ☐

13.5. በመማሪያ መጽሐፍ በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት ☐

14. በት/ቤት ውስጥ የድራማና የስነ ጽሑፍ ክበብ ፣ የጋዜጠኞች ክበብ ፣ የፀረ-ኤድስ ክበብ ... እንቅስቃሴ የሚካሄድ ከሆነ ለጽሁፈት ለምምዱ ጠቀሜታው ምን ያህል ነው ?

14.1. ሙሉ በሙሉ ጠቀሜታ አለው ☐

14.2. በአብዛኛው ጠቀሜታ አለው ☐

14.3. በመጠኑ ጠቀሜታ አለው ☐

14.4. አንዳንድ ጊዜ ጠቀሜታ አለው ☐

14.5. ጠቀሜታ የለውም ☐

15. አንዳንድ ተማሪዎች የሰሩትን የጽሁፈት መለመጃ እንዲያነቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ የማይሆኑበት ምክንያት ምን ይመስልሃል ?/ ይመስልሻል /?

15.1. መሳሳትን እንደድክመት ስለሚቆጥሩት ደካማ ላለመምሰል ☐

15.2. ስህተት ቢፈፅሙ በተማሪዎች ፊት እንዳይሳቀቧቸውና እንዳይፌዘባቸው ☐

15.3. ከስህተት መማር መቻሉን ባለመገንዘባቸው ☐

15.4. በሚያነቡበት ጊዜ ቢሳሳቱ ስለሚያፍሩ ☐

16. የተማሪዎቹ መለመጃዎች ሲታረሙ ስህተት ቢፈጠር መምህሩ ምን ያደርጋሉ ?

16.1. ስህተት መፈፀሙ የማይቀር መሆኑን ያስገነዝባሉ ☐

16.2. ስህተት ተፈጥሮአዊ የቋንቋ መማር ሂደት አንዱ አካል እንደሆነ ይገልፃሉ ☐

16.3. ተማሪዎቹ ስህተት የማይፈፀሙበትን መንገድ ያመቻቻሉ ☐

16.4. ስህተት መፈፀም አስነዋሪና አስቀያሚ እንደሆነ ይገልፃሉ ☐

16.5. ተማሪው ተሳሳተ ማለት መምህሩ ምንም እንዳልሰራ ተቆጠረ ማለት ነው በማለት ይናደዳሉ ☐

17. ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተት ከተማሪዎቹ ድክመት የመጣ ነው ብለህ/ሽ/ የምትገምት/ቺ/ ከሆነ ለድክመቱ መንስኤው ምን ይሆናል ተብሎ ይታሰባል ?

17.1. ከተማሪው ውስጣዊና ውጫዊ የግል ችግር ☐

17.2. የትምህርትን አውድ በመሳቱ ☐

17.3. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ለቋንቋው ትምህርት ያልተመቻቸ በመሆኑ ☐

17.4. በድካምና በሰውነት መዛል በሚፈጠር ዝንጋታ ☐

17.5. የትምህርቱ አሰጣጥ ስለማይስበው ☐

18. በጥቅሉ ተማሪዎች ጽህፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈጠሩ ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ተብለው የሚገመቱት ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ ናቸው ?

18.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ☐

18.2. የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርአት አስቸጋሪ ነት ☐

18.3. የመምህራን የማስተማር ችሎታ ☐

18.4. የመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት ትኩረት ባለመስጠቱ ☐

18.5. የመምህራን የአስተራረም ጉድለት ☐

19. ጽህፈትን በምትለማመድበት/በምትለማመጂበት / ጊዜ ችግር የሚያጋጥምህ/ሽ / ምን ላይ ነው ?

19.1. የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ☐

19.2. የቃላት አጠቃቀም ላይ ☐

19.3. የፅንሰ ሃሳብ ቅንብር ላይ ☐

19.4. የዐ. ነገር አመሰራረት ላይ ☐

19.5. የቃላት ፍቺ ላይ ☐

20. አንተ /አንቺ/ ስህተት በምትፈፅምበት/በምትፈፅሚበት / ጊዜ ተደጋጋሚ ስህተቶችን የምትፈፅመው / የምትፈፅሚው ከላይ በተራ ቁጥር 19 ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኞቹ ላይ ነው ?

20.1. 19.1 ☐

20.2. 19.2 ☐

20.3. 19.3 ☐

20.4. 19.4 ☐

20.5. 19.5 ☐

## መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች አምስት አማራጭ መመዘኛዎችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ሲሆን ከቀረቡት መልሶች መካከል ተገቢ መልስ ነው ብለህ /ሽ / የምታምንበትን /የምታምኚበትን/ መመዘኛ በመምረጥ መልሱን በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ" ✓ " ምልክት በማስቀመጥ አመልክት/ቺ /፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | አንተ/አንቺ በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፈትን ለመለማመድ ያለህ/ሽ/ፍላጎት ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 2 | አንተ/አንቺ ከልዩ ልዩ መጻህፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጣዎች፣ ከሬዲዮና ቴሌቪዥን ወዘተ --- የሰበሰብከውን/ሽውን ሃሳብ በራስህ/ሽ/አባባል ጽፈህ/ሽ/ ለማቅረብ ያለህ/ሽ/ ፍላጎት ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 3 | ጽሁፈትን ለማለማመድ የመምህሩ ጥረት ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 4 | የመማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች ጽሁፈትን በማለማመድ በኩል ያሳቸው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 5 | በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽሁፈት ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት መመሪያዎች ጠቀሜታቸው ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 6 | መልመጃዎች ታርመው መመለሳቸው ለጽሁፈት ክሂሎ መዳበር የሚሰጠው ጠቀሜታ ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 7 | መልመጃዎች እየታረሙ በሚመለሱበት ጊዜ ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው የስህተቶች መጠን ምን ያህል ነው ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 8 | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ አማካኝነት የሚፈፀሙ ስህተቶች መጠን ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 9 | ጽህፈትን በማለማመድ በኩል መምህሩ ያለው ዕውቀት ምን ያህል አጥጋቢ ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 10 | በት/ቤቱ የተቋቋሙት ልዩ ልዩ ክበባት ለጽህፈት ልምምድ ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

## ክፍል ሦስት

### መመሪያ

ከዚህ በታች የተማሪውን ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል ::
ስለሆነም ጥያቄዎችን በጥንቃቄ ካነበብክ /ሽ/ በኋላ ተገቢ መልስ ይሆናል ብለህ/ሽ/ የምትገምተውን / የምትገምቺውን / ሃሳብ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በሰፊው ፃፍ /ፊ /

1. ጽሁፈትን ለመለማመድ ችግር የሚያስከትሉብህ /ሽ/ ነገሮች ካሉ በዝርዝር ገለፃ ቸው /ገለጪ ቸው / ______________________________

______________________________

______________________________

2. በጽሁፈት ልምምድ ጊዜ የምትፈፅማቸው/የምትፈፅሚያቸው/ የስህተት አይነቶች ምን ምን እንደ ሆኑ በዝርዝር ገለፀ /ጪ / ______________________________

______________________________

______________________________

3. በጽህፈት ልምምድ ጊዜ ለሚፈፀሙት ስህተቶች የስህተት ምንጮች ናቸው ብለው የሚገመቱት ምን ምን ናቸው ? ______________________________

______________________________

______________________________

4. በጥቅሉ እስካሁን ድረስ የቀረቡትን መጠይቆች በሚመለከትና የአማርኛን የጽህፈት ትምህርት አስመልክቶ የሚኖርህን/ የሚኖርሽን/ አስተያየት ገለፀ /ጪ /______

______________________________

______________________________

5. ስለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚኖርህን / የሚኖርሽን/ አስተያየት በሰፊው ገለፀ /ጪ / ______________________________

______________________________

______________________________

ስለተባበራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለን !

## አባሪ 2

### የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
### የድህረ - ምረቃ ትምህርት ቤት
### የኢት. ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

### በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

የተከበራችሁ መምህራን!

ይህ መጠይቅ የተዘጋጀው በሰሜን ኦሮሚያ በሰላሌ ወረዳ በ__________ ተ/ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በሚጽፏት የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የሚፈፅሟቸውን የስህተት አይነቶች ፣ የስህተት ምንጮችና ድግግሞሻቸውን ለመለየት ለተጀመረው የድህረ - ምረቃ ዲግሪ ማሟያ ጥናት እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በማሰብ ነው።

በዚህ ጥናት የሚደረስበት ውጤትም የአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ትምህርት በሚካሄድበት ጊዜ ሂደቱን ሊያደናቅፉ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ችግሮች ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በመጠኑም ቢሆን አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል። ሆኖም ከታሰበው ግብ ለመድረስ የሚቻለው መምህራን በሚሰጡት ሙያዊ ድጋፍ በመሆኑ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ የቀረቡትን መጠይቆች በአግባቡ ሞልታችሁ እንድትመልሱልን ትብብራችሁን እንለምናለን።

ስለትብብራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

## ክፍል አንድ

አጠቃላይ መመሪያ ፦ ትክክለኛ የሆነውን መልስ በባዶው ቦታ ላይ ያስቀምጡ::

1.1. ጾታ ____________

1.2. የትምህርት ደረጃ ____________

1.3. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ

አብይ ____________

ንዑስ ____________

1.4. የአገልግሎት ዘመን ____________

1.5. በዚህ ት/ቤት ያሰፉት የማስተማር ልምድ ____________

1.6. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ /መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል/

______________________________

1.7. አሁን በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ያሰፉት የስራ ልምድ ____________

1.8. በተመደቡበት የክፍል ደረጃ በሳምንት የሚያስተምሩት ክ/ጊዜ ብዛት ________

## መመሪያ አንድ

ከዚህ በታች አማራጭ መልሶችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ከነዚህ ጥያቄዎች አንዳንዶቹ ከአንድ በላይ የሆኑ አማራጭ መልሶችን ይዘዋል:: ስለሆነም ጥያቄዎቹን በጥሞና ካነበቡ በኋላ ትክክለኛ መልስ የያዘ/ዙ/ የሚመስልዎትን / የሚመስሉዎትን መልስ/መልሶች በሳጥኑ ውስጥ የ" ✓ " ምልክት ያድርጉባቸው ::

1. ለክፍሉ ደረጃ በቀረበው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የመልመጃ ይዘቶች በአብዛኛው ተማሪዎቹ የትኞቹን የዕውቀትና የክሂል ዘርፎች እንዲለማመዱባቸው ያስችላሉ ?
   - 1.1. ማዳመጥና መናገርን □
   - 1.2. ማንበብን □
   - 1.3. ጽህፈትን □
   - 1.4. ስነ ልሳንን □
   - 1.5. ስነ ጽሑፍን □
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 1.3 ከሆነ ተማሪዎችን በይበልጥ በጽህፈት ክሂል ላይ እንዲለማመዱ የሚያደርጉት መልመጃዎች የትኞቹ ናቸው ብለው ይገምታሉ ?
   - 2.1. መልመጃ አንድ □
   - 2.2. " ሁለት □
   - 2.3. " ሦስት □
   - 2.4. መልመጃ አንድና ሁለት □
   - 2.5. " ሁለትና ሦስት □
3. የጽህፈት ትምህርትን የሚያስተምሩት በምን ላይ ተመርኩዘው ነው ?
   - 3.1. በመማሪያ መጽሐፉ ብቻ □
   - 3.2. በመርሀ-ትምህርቱ ብቻ □
   - 3.3. በመርሀ-ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ □
   - 3.4. ከመርሀ-ትምህርቱና ከመማሪያ መጽሐፉ ውጭ ከተለያዩ ነገሮች ላይ በተወሰዱ ጽሑፎች □
   - 3.5. በመርሀ-ትምህርቱ በመማሪያ መጽሐፉና ከመጽሐፉ ውጭ □
4. ከላይ በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 3.4 ወይም 3.5 ከሆነ ተማሪዎችዎ በሬዲዮ ካዳመጡት ፣ በቴሌቪዥን ካዩትና ከሰሙት ፣ በጋዜጣ ፣ መጽሔት፣ መጻህፍት--ካነበቡት ሃሳብ ሰብስበው ጽፈው እንዲመጡ ያደርጋሉ ?

4.1. ዘወትር አደርጋለሁ □
4.2. አብዛኛውን ጊዜ አደርጋለሁ □
4.3. አንዳንድ ጊዜ አደርጋለሁ □
4.4. በወር አንድ ጊዜ አደርጋለሁ □
4.5. ፈጽሞ አላደርገም □

5. በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው ጥያቄ 3.3. ወይም 3.5 ከሆነ መርሃ ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ጽሁፈት የሚዳብርበትን ዝርዝር ሃሳቦችና መመሪያዎች ይዘዋልን?

5.1. ሙሉ በሙሉ ይዘዋል □
5.2. በአብዛኛው ይዘዋል □
5.3. በመጠኑ ይዘዋል □
5.4. አልፎ አልፎ ይዘዋል □
5.5. ምንም አልያዘም □

6. ለክፍሉ ደረጃ በቀረበው የመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉት ጽሁፈትን የሚመለከቱ መልመጃዎች ተማሪው ጽሁፈቱን በምን አይነት መንገድ እንዲፅፍ ያደርጉታል ?

6.1. ቃላትን ከቃላት አገጣጥሞ ዐ.ነገር እንዲፅፍ በማድረግ □
6.2. ዐ.ነገርን ከዐ.ነገር አገጣጥሞ አንቀጽ እንዲፅፍ በማድረግ □
6.3. አንቀጽን ከአንቀጽ አገጣጥሞ ድርሰት እንዲፅፍ በማድረግ □
6.4. የተሟላ ድርሰትን አሳጥሮ እንዲፅፍ በማድረግ □
6.5. አስተዋጽኦ እንዲፅፍ በማድረግ □

7. በክፍል ውስጥ ጽሁፈት በሚያለማምዱበት ጊዜ ስለ ቃላት አመሰራረትና የዐ.ነገር አገነባብ አስተምረው ያውቃሉ ?

7.1. ዘወትር አስተምራለሁ □
7.2. አብዛኛውን ጊዜ አስተምራለሁ □
7.3. በመጠኑ አስተምራለሁ □
7.4. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ □
7.5. እንደሁኔታው አስተምራለሁ □

8. ተማሪዎችዎን ስለድርሰት አፃፃፍ ደንብ አስተምረው ያውቃሉ ?

8.1. ዘወትር አስተምራለሁ □
8.2. አብዛኛውን ጊዜ አስተምራለሁ □
8.3. በመጠኑ አስተምራለሁ □
8.4. አንዳንድ ጊዜ አስተምራለሁ □
8.5. እንደሁኔታው አስተምራለሁ □

9. ድርሰት /ጽሁፈት/ በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚጠቀሙበት መንገድ የትኛው ነው ?

9.1. ርዕስ ሰጥቶ አንቀጽ እንዲመሰርቱ ማድረግ □
9.2. አንቀጽ ሰጥቶ ተማሪዎች አንቀፁን እንዲመረምሩት ማድረግ □
9.3. አስተዋጽኦ ነድፈው ድርሰት እንዲፅፉ በማድረግ □
9.4. ተማሪዎች የራሳቸውን ርዕስ መርጠው እንዲፅፉ በማድረግ □
9.5. ሁሉንም መንገድ በመጠቀም □

10. ተማሪዎችን የጽህፈት/ድርሰት/ትምህርት ለማስተማር የትኛው ዘዴ የተሻለ ይመስለዎታል ?

10.1. የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን አስቀድሞ ማስተማር ☐

10.2. በመጀመሪያ ተማሪዎች እንዲፅፉ ማድረግ ☐

10.3. ተማሪዎች ራሳቸው ከፃፉት ድርሰት በመነሳት የድርሰት አፃፃፍ ህጎችን እንዲያወጡ ማድረግ ☐

10.4. በተማሩት ህግ መሰረት አንቀጽ ብሎም ድርሰት እንዲፅፉ ማድረግ ☐

10.5. አስተዋጽኦ ነድፈው በነደፉት አስተዋጽኦ መሰረት እንዲፅፉ ማድረግ ☐

11. ለቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በተለይም ጽህፈትን ለማዳበር የሚያስችሉ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች በት/ቤቱ ውስጥ ይካሄዳሉን ?

11.1. ዘወትር ይካሄዳሉ ☐

11.2. አብዛኛውን ጊዜ ይካሄዳሉ ☐

11.3. በመጠኑ ይካሄዳሉ ☐

11.4. አልፎአልፎ ይካሄዳሉ ☐

11.5. ተካሂዶም አያውቅ ☐

12. ቋንቋውን በሚያስተምሩበት ጊዜ በጽሑፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤት ስራ ሰጥተው ያውቃሉ ?

12.1. ዘወትር አሰጣለሁ ☐

12.2. አብዛኛውን ጊዜ አሰጣለሁ ☐

12.3. በመጠኑ አሰጣለሁ ☐

12.4. አልፎአልፎ አሰጣለሁ ☐

12.5. ከሁለት ወር ከ3 ወር አንድ ጊዜ አሰጣለሁ ☐

13. በተራ ቁጥር 12 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 12.3 ፣ 12.4 እና 12.5 ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል ?

13.1. ጽህፈትን ማስተማር አስቸጋሪ በመሆኑ ☐

13.2. ጽህፈትን ማስተማር ጠቀሜታው አነስተኛ በመሆኑ ☐

13.3. የተማሪዎቹ የመጻፍ ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ ☐

13.4. በጽሑፍ የሚመለስ ጥያቄ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለማይዘጋጅ ☐

13.5. ጽህፈትን ለማለማመድ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ☐

14. ተማሪዎችዎ የሚሰጧቸውን የክፍልና የቤት ስራ ሰርተው ይመጧሉ ?

14.1. ዘወትር ይሰራሉ ☐

14.2. አብዛኛውን ጊዜ ይሰራሉ ☐

14.3. በመጠኑ ይሰራሉ ☐

14.4. አንዳንድ ጊዜ ይሰራሉ ☐

14.5. ከወር ከሁለት ወር አንድ ጊዜ ይሰራሉ ☐

15. በተራ ቁጥር 14 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 14.3 ፣ 14.4 ወይም 14.5 ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልዎታል ?

15.1. ተማሪዎቹ ትምህርቱን ስለሚንቁት □

15.2. የጽህፈት ስራ አስቸጋሪ በመሆኑ □

15.3. ተማሪዎቹ የመፃፍ ፍላጎት ስለሌላቸው □

15.4. በመማሪያ መጽሐፍ ለጽህፈት የሚመረጡት ርዕሶች የተማሪዎችን ፍላጎቶች ባለመያዛቸው □

15.5. የጽህፈትን ጠቃሚነት ባለመረዳታቸው □

16. በክፍልም ሆነ በቤት ስራ ተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፉ የሚያደርጉት ምን ጊዜ ነው ?

16.1. በሳምንት አንድ ጊዜ □

16.2. በየሁለት ሳምንት □

16.3. በወር አንድ ጊዜ □

16.4. በየሦስት ወሩ □

16.5. በሴሚስተር አንድ ጊዜ □

17. ተማሪዎቹ ድርሰት እንዲፅፉ በሚደረግበት ጊዜ ርዕሱ በማን ይመረጣል ?

17.1. በመምህሩ ይመረጣል □

17.2. በተማሪዎች ይመረጣል □

17.3. በመምህሩና በተማሪዎች ይመረጣል □

17.4. በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረበው ርዕስ ተግባራዊ ይሆናል □

17.5. ከላይ በተዘረዘሩት በሁሉም ይመረጣል □

18. እንደየክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ የሰጡትን መልመጃ አርመው ያውቃሉ ?

18.1. ዘወትር አርማለሁ □

18.2. አብዛኛውን ጊዜ አርማለሁ □

18.3. በመጠኑ አርማለሁ □

14.4. አንዳንድ ጊዜ አርማለሁ □

14.5. ከወር አንድጊዜ አርማለሁ [

19. በተራ ቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ አርማለሁ የሚል ከሆነ እርማቱ በማን ይከናወናል ? /መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል /

19.1. የመምህሩ ግለ - እርማት □

19.2. የቡድን እርማት □

19.3. የቢጤ እርማት □

19.4. የተማሪው ግለ - እርማት □

19.5. የጥቂት ተማሪዎችን አስነብቦ ማለፍ □

20. በተራ ቁጥር 18 ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ 18.4 ወይም 18.5 ከሆነ ችግሩ ምን ይመስልዎታል ?

20.1. የተማሪዎች ቁጥር በርካታ በመሆኑ ☐

20.2. ተማሪዎቹ መለመጃውን ሰርተው ስለማይመጡ ☐

20.3. የማረም ስራ አድካሚና አሰልቺ በመሆኑ ☐

20.4. በታረመው መሰረት ተማሪዎቹ ጽሁፈታቸውን ለማሻሻል ስለማይጥሩ ☐

20.5. በቂ ክፍለ ጊዜ ባለመሰጠቱ ☐

21. እንደ የክፍልዎ ሆነ የቤት ስራ የሰጡትን የጽሕፈት መለመጃ በሚያርሙበት ጊዜ አብዛኞቹ ተማሪዎች ይበልጥ ስህተት የሚፈፅሙት በየትኞቹ ላይ ነው? /መልሱ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል /

21.1. ሰርአተ ነጥብ ላይ ☐

21.2. የቃላት አገባብና አጠቃቀም ላይ ☐

21.3. የዐ. ነገር አመሰራረትና የአንቀጽ አፃፃፍ ላይ ☐

21.4. የፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ላይ ☐

21.5. በመስተዋድድ አጠቃቀም ላይ ☐

22. ለተማሪዎች ስህተት መፈፀም ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል ?

22.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ☐

22.2. የተማሪዎቹ ግዴለሽነት ☐

22.3. የሁለተኛ ቋንቋው ሰዋሰዋዊ ስርዓት አስቸጋሪነት ☐

22.4. የመምህራን የአስተራረም ጉድለት ☐

22.5. የመርሃ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፉ ብቃት ማነት ☐

22.6. ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት ☐

23. ተማሪዎቹ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሙትን ስህተቶች ከተማሪው ድክመት የመጡ ናቸው ብለው የሚገመቱ ከሆነ ድክመቱ ከምን የመጣ ይመስለዎታል?

23.1. ከተማሪው ውስጣዊና ውጫዊ ችግር ☐

23.2. በድካምና በሰውነት መዛል በሚፈጠር ዝንጋታ ☐

23.3. የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ የተማሪውን ፍላጎት የማይስብ በመሆኑ ☐

23.4. የመማሪያ ክፍሉ ሁኔታ ለትምህርቱ ያልተመቻቸ በመሆኑ ☐

23.5. የድርሰቱ ርዕስ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዕድሜ የማይመጥን በመሆኑ ☐

## መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች አምስት አማራጭ መመዘኛዎችን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: ለእያንዳንዱ ጥያቄም የሚሰጠው መልስ አንድ ብቻ ሲሆን ከቀረቡት መልሶች መካከል ከሁሉም የበለጠ ተገቢ መልስ ነው ብለው የመረጡትን መመዘኛ በተሰጠው ባዶ ሳጥን ውስጥ የ" ✓ " ምልክት ያስቀምጡ::

| ተራ ቁ. | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አዎንታዊ አመለካከት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 2 | የመማሪያ መጽሐፍ የመልመጃ ይዘት ጽሁፈትን ለመለማመድ ያለው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 3 | እርስዎ ተማሪዎችን ጽሁፈትን ለማለማመድ የሚሰጡት ጊዜ ምን ያህል በቂ ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 4 | ለቋንቋው ትምህርት የተፈቀደው ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ ጽሁፈትን ለማለማመድ የሚኖረው አፍራሽ ተፅዕኖ ምን ያህል ነው ብለው ይገምታሉ? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 5 | ጽሁፈትን ለመለማመድ ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 6 | እርስዎ ጽሁፈትን ለማለማመድ የሚያደርጉት ጥረት ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 7 | ተማሪዎች የጽሁፈት ችሎታቸውን ለማሻሻል የተለያዩ ነገሮችን የማንበብ ልምዳቸው ምን ያህል የዳበረ ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 8 | በጽሁፈት ልምምድ ላይ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚኖረው አፍራሽ ተፅዕኖ ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |
| 9 | ተማሪዎች ድርሰት/ጽሁፈት/በሚለማመዱበት ጊዜ የሚፈፅሙት የስህተት መጠን ምን ያህል ነው? | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ | ☐ |

## ክፍል ሦስት

### መመሪያ

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች የእርስዎን ነፃ አስተያየት የሚጠይቁ ናቸው:: ስለሆነም ከስራ ልምድዎ ፣ በስራ ሂደት ካጋጠመዎ ችግሮችና ከተመለከቱት ... በመነሳት ይሆናል ብለው ያሰቡትንና የገመቱትን ሃሳብ እንዲሰጡ በአክብሮት ይጠየቃሉ::

1. በት/ቤቱ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ምን ይመስልዎታል ? ____________________

____________________

____________________

2. ለክፍሉ ደረጃ ተዘጋጅቶ የቀረበው መርሃ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ምን ያህል ነው ብለው ይገምታሉ ? ____________________

____________________

____________________

3. በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማዳበር የሚኖረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዴት ይመለከቱታል ? ____________________

____________________

____________________

4. የሁለተኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ተማሪዎችዎ በጽህፈት የሚመለስ እንደየክፍልም ሆነ የቤት ስራ ያለውን በአብዛኛው ሰርተው የሚመጡ ከሆነ ለመስራታቸው ምክንያቶች ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን ቢገልጿቸው ? ____________________

____________________

____________________

5. እርስዎ የሚሰጡትን እንደየክፍልም ውስጥ ሆነ የቤት ስራ ያሉትን ተማሪዎች ሰርተው የማይመጡ ከሆነ በአብዛኛው ሰርተው የማይመጡ ተማሪዎች የትኞቹ ናቸው

ብለው ይገምታሉ ?/ የአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎች ወይስ የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺ ዎች ? / ምክንያቱ ምን ይመስለዎታል ?

6. እንደ የቤት ስራም ሆነ የክፍል ስራ የሰጡትን የጽሁፈት መለመጃ በሚያርሙበት ጊዜ በአብዛኛው ስህተት የሚፈፅሙት ተማሪዎች የትኞቹ ናቸው ?/ የአማርኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎች ወይስ የኦሮምኛ ቋንቋ አፍ ፈቺዎችና ሌሎች / ለምን እንደሆነ ያለዎትን አስተያየት ቢገልፁ?

7. ተማሪዎችን ጽሁፈት በሚያለማምዱበት ጊዜ የሚፈፀሙት የስህተት አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጿቸው ?

8. በጽሁፈት ለምምዱ ወቅት በተደጋጋሚ የሚፈፀሙት የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው ብለው ይገምታሉ ? ለምንስ የሆነ ይመስለዎታል ?

9. ተማሪዎችዎ ጽሁፈትን በሚለማመዱበት ጊዜ ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮች ይሆናሉ ብለው የሚገምቱትን ቢጠቅሱልን ?

10. በጥቅሉ የ2ኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን የጽሁፈት ክሂል ለማዳበር ሊደረግ ይገባ ዋል ብለው የሚገምቱትንና የስህተት ምንጮች የሚሏቸውን ለማስወገድ የሚወስደውን ርምጃ ቢገልፁልን

# አ ባ ሪ 3

## የድርሰት መለመጃ

## ክፍል አንድ

### ሀ. መመሪያ አንድ

1. ድርሰት በሚፅፍበት ወረቀት ላይ ስም አይፃፍም
2. በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ አፍ የፈታህበትን /የፈታሽበትን/ ቋንቋ/ አስቀምጥ /ጪ/
3. ድርሰቱ የሚፃፈው በኢ-ልብወለድ ድርሰት ነው ::

### ለ. መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች ድርሰት ሊያጽፍ የሚያስችሉ 5 ርዕሶች ቀርበዋል:: ከነዚህም ውስጥ ይቀለኛል ፣ ርዕሱ በዙ ያጽፈኛል የምትለውን /የምትይውን/ አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ከ100 - 150 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ፃፍ/ፊ /:: ይህንንም ለመፃፍ የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ብቻ ነው ::

1. በሃገራችን የጾታ ትምህርት በስፋት ባለመሰጠቱ ከጾታ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ በሽታዎች ህብረተሰቡን ሲጐዱት ቆይተዋል:: ስለሆነም ይህንን ጉዳት ለማስቀረት እንዲቻል "የጾታ ትምህርት" በሚል ርዕስ የምታውቀውን /የምታውቂውን/ ያህል ፃፍ/ፊ /
2. በፈተና አካባቢ የሚታየውን ሁኔታ በማስታወስ "የፈተና ሰሞን" ብለህ /ሽ/ ድርሰት ፃፍ /ፊ /::
3. የአካባቢህን /ሽን / የገና ስርአት ለማያውቅ ሰው ለማሳወቅ ቢፈለግ እንዴት ልትገልጽለት /ልትገልጪለት / እንደምትችይ በማሰብ "የገና ስርአት" በሚል ድርሰት ፃፍ /ፊ /
4. በዚህ አመት በሃገራችንና ከሃገራችን ውጭ ወቅትን ባልጠበቀ ዝናብ አማካኝነት የተከሰተው ጎርፍ የበርካታ ሰዎችን ህይወትና ንብረት እያጠፋ ለመሆኑ በሬዲዮ ሲደመጥና በቴሌቪዥንም ሲታይ ሰንብቷል:: ስለሆነም አንተ/አንቺ / ይህንኑ ችግር መነሻ በማድረግ "ጎርፍ ያስከተለው ችግር" በማለት አንድ ድርሰት ፃፍ /ፊ /::

5. አንተ /አንቺ/ ሐኪም ብትሆን /ኚ/ ለበሽተኞችህ /ሽ/ ለታደርገላቸው /ለታደርጊላቸው/ የሚገባህን /የሚገባሽን/ በማሰብ " ሐኪም ብሆን ኖሮ" በሚል ርዕስ ድርሰት ፅፈህ /ሽ/ አቅርብ /ቢ/::

# ክፍል ሁለት

## ሀ. መመሪያ አንድ

1. ድርሰት በሚጽፍበት ወረቀት ላይ ስም አይጻፍም
2. በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ እና የፈታህበትን/የፈታሽበትን / ቋንቋ አስቀምጥ /ጪ /
3. ድርሰቱ የሚጻፈው በኢ- ልብወለድ ድርሰት ነው ::

## 2. መመሪያ ሁለት

ከዚህ በታች ድርሰት ሊያጽፉ የሚያስችሉ 5 ርዕሶች ቀርበዋል :: ከነዚህም ውስጥ ይቀለኛል ፣ ርዕሱ ብዙ ያጽፈኛል የምትለውን /የምትይውን/ አንድ ርዕስ ብቻ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ከ100 - 150 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ጻፍ /ፊ/ :: ይህንንም ለመጻፍ የተፈቀደው ጊዜ 40 ደቂቃ ነው ::

1. " አስተዋይ ተማሪ " በማለት አንድ አስተዋይ ተማሪ ሊፈፅማቸው የሚችሉ ተግባራትን በድርሰት መልክ አቀናብረህ /ሽ/ አቅርብ /ቢ/
2. ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ለወደፊቱ ሊሰማሩበት ስለሚፈልጉት የስራ መስክ ከአሁኑ ይመኛሉ:: ስለሆነም አንተ /ቺ / ለወደፊቱ ስለሚኖርህ /ሽ/ ምኞት በማስታወስ " የወደፊት ምኞቴ " በማለት ምኞትህንና /ሽን/ በጽሑፍ ግለፀው / ግለጪው /
3. በየሳምንቱ ቅዳሜ ከሰአት በኋላ የሚቀርበውን የወጣቶች ሳምንት የራዲዮ ፕሮግራም በማሰብ ፕሮግራሙ ለወጣቶች የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ጉዳት በማነፃፀር "የቅዳሜ የወጣቶች ሳምንት የራዲዮ ፕሮግራም" በሚል ድርሰት ጻፍ /ፊ /
4. በሃገራችንም ሆነ ከሃገራችን ውጭ የሰውን ልጅ ህይወት በመቅሰፍ እንደ ቅጠል የሚያረግፈው በሽታ ኤድስ እንደሆነ በተለያዩ የዜና ማሰራጫ አውታሮች እየተነገረ ነው:: ስለሆነም አንተ /አንቺ/ ስለዚሁ በሽታ አስከፊነት " የኤድስ በሽታ አስከፊነት " በሚል ካለህ /ሽ/ ግንዛቤ በመነሳት ርዕስ በድርሰት መልክ ጻፈው /ጻፊው /::
5. የእናት ጥቅም በቀላሉ ዘርዝሮ አያልቅም:: ስለሆነም ስለእናት የሚኖርህን /ሽን/ ግንዛቤ "እናት" በሚል ርዕስ ጻፈው /ጻፊው /

# አባሪ 4

## የቲ-ስሌት መግለጫ

$\bar{x}1 = 29.425$

$S^2_1 = 46.169375$

$\bar{x}_2 = 13.625$

$S^2_2 = 17.384375$

$$t = \frac{\bar{x}1 - \bar{x}_2}{\frac{\sqrt{(n1-1)S^2{}_1 + (n_2-1)S^2{}_2 x\left[\frac{1}{n1}+\frac{1}{n2}\right]}}{n_1 + n_2 - 2}}$$

$$= \frac{29.425 - 13.625}{\frac{\sqrt{(240-1)x46.169375 + (200-1)x17.384375x\frac{1}{240}+\frac{1}{200}}}{240 + 200 - 2}}$$

$$= \frac{15.80}{\frac{\sqrt{11034.481 + 3459.4906x0.0091666}}{440-2}}$$

$$= \frac{15.80}{\sqrt{0.3033343}}$$

$$= \frac{15.80}{\sqrt{0.5507599}}$$

$t = \underline{28.687741}$

Therefore, t-observed value is greater than the critical t-value. the critical t-value on the t-table is 1.95 at 0.05 level of significance and n - 2 (438) degree of freedom.

- እናትዬ ምን ትቸገራለህ ታዲያ ለዜ ተለና ይነሳም ይበዛም ያለኝህን ተሳለች አሰጨሎ

- የኔ ምኞት ገደብ የለውም አገዛብሔር ያድርሰኝ ብቻ ምንም አለለም ዛሬ

- አንዳንዱ ሰዎች ቃመው ሳያቸው.... ማረፊያ ቦታ ሰጥቴ ነበረ የማስተናገዳቸው

- ነገር ግን ያንን የተመኘትን በተግባር ማሳየቱ ላይ ነው ቁም ነገሩ

- በመሆኑም ቶሎ አይገድለም አሰቃይቶ የአለጋ ቁራኛ አድርጎ ነው የሚያሳርፈው አፅመን ከጉድጓድ

- ይህን ያህል ተበበር ይህን ያህል ብርታት የሰውን ልጅ ጨርሶ ምድርን ለማጥራት ከፍ ያለ ኤድስ

- የጾታ ልዩነት አያ የዘር ልዩነት አያውቅ ሁሉንም በመደዳ የሚጨፈጭፍ አገደ ሰደዱ አሳት አይምረው ኤድስ ታጥቶ ተነስቷል ለሰው ልጅ ሁሉ

- ማነው ይህን አይነት ፀቀዱ አውጥቶ የሚያሰራው ብዬ ስጠይቅ ኢንጅነር ከሆነክ መስራት ትችላለህ አለኝ አንዱ አዲስ አበባ የሚኖር ወንድሜ

- በፈተና ሰሞን ማድረግ ያለብኝ ማድረግ ያለበት ሰው በኖር በመጀመሪያ የፈተናው ጊዜ ሳይደርስ ዘዴዎች መኖር አለባቸው የሚል ነበት

- - -

01-6

[illegible]

ለርም

## ገበርቆ የሥነተለው ችግር

በዘሁ፡ አሰት፡ ለሃገርኛ(፡)የለመጠቀ፡ ዝርዝ(፡)ገዛ፡ ችግርን (በእገርኛን) ለይ ሊረዳ፡
ንግዛህም ችግሮች መገንዘብ፡ እንደእንደቹ(፡)ለመንቀሳቀስ፡ (የ)ምንርዳሁ።
(እርሱንም) ሀገሮችን፡ መሰረት፡ እንደቆጠሩ(፡)ከለመዘው፡ የሚተዳደሩ፡ ከሃገሮች ነው፡
አሁን፡ መቆተ(፡)ከለመጠቀ፡ዝርዝ፡ አሰማዎችን፡ ገዛ እንደሆነ፡ መፍቀል፡
[ለምሳሌ፡ በእገርኛን፡ ይበልጥ የሚመርተው፡ ገዛ (እንደሆነ)፡ ነቸው፡] 05
ንግዛህም፡ እንደሆነ፡ መሰን፡ መሰረ፡ አሰማዎችን፡ የሉ፡ (ቀን) ቀን ለሁ፡ የሚሆን
እንደሆነ፡ አለ። ለምሳሌ፡ መቆተ፡ በደብ እና አቶ፡ በዛሁ፡ ገዛ፡ የሉ፡ ከሉ
የመጠቀ ነቸው። [እንደዚሁ፡ መቆተ፡ ከለመጠቀ፡ ዝርዝ፡ አሰማዎችን፡ ገዛ፡ እንደለ፡ መቆ
የቀል።] እንግዛህም (ለይ)፡ ከቻ ከሌሎችን፡ በዛ፡ ለሃገሮች እንደሆነ ለይም ይረዳል፡
ንግዛህም፡ አደገኛ፡ መገንዘብ፡ ዝርዝ፡ ከዘገብ፡ በሁለ፡ በገርቆ፡ አሰማዎችን፡ ገዛ
መሰረቶች[ለምርትተዎችን፡ በመንቀሳቀሻ፡ መቆ የቀል፡] (እንዛሁ፡ መሰረቶች፡ ከቻ ለይ፡ ከይሁ
ም። በገመር፡ እንዘበዘ፡ ከበሮ እንዘ ቀር፡ ከሆኑ፡ ከገባቸውን ለመጠቀል፡]
(የኛን) (ከገባቸው) (የሚመጠቀው) (ለሮች) ለሆን(፡)(የሚያገቡ፡ ከ6 — ከ6 — 12 ወሮች
የሰቸው፡ ለሮች ነቸው።] [ይህ፡ ለሮች፡ ዝርዝ፡ ከዘገብ፡ በሁለ፡ ገበርቆ በሚገ
ርበት፡ ገዜ፡ የሚገባቸውን፡ ገበርቆ መሰን፡ ይፈልገዋል፡ በእንደገናቸው፡ የኛን ገበርቆ መሰን፡
ይፈልጋል።] (ገበርቆ) አሁን፡ ከለሆ፡ እንደገኛቸውን፡ በእንደ ገዜ (መለየው) የሁ
ለሮች፡ ገበርቆ፡ መሰን፡ ይመደቃል።] (ከመደቀም፡ በሁለ፡ ይህ፡ ገበርቆ፡ በእንዲ
አቀንመጠ፡ ይገበር (የህን) ይለሮች ይጠቀቃል።] 05
ለምሳሌ፡ የሁለ በዘሁ፡ (እውነት)፡ መቆተ(፡)ከለመጠቀ፡ ዝርዝ፡ አሰማዎችን፡ ገዛ
ች፡ አለ፡ ለይ (ይረዳል)።[አሁን፡ ዝርዝ፡ ለን፡ ሌላት፡ ~~ ~~ የዘገብ እን
ሆር፡ (ለማቶ) (ተገባል)።] ዝርዝ፡ ከዘገብ፡ በሁለ፡ ገበርቆ የሚመደብ ለተግር ከሎቸ፡
ከ(ለ)ገበርቆቸው፡ ገር (የዘው) (ይሰራል)፡ ይህ(መሰረት)(በ)ገበርቆ፡ (አሰማዎችን) በለሆኑ(ን)
በገበርቆቸው ከር፡ በእገር ዕድገት፡ ለይም፡ ከቀት ገደት የሚረዳል።
በአጠቃላይ፡ ገበርቆ በሰው፡መደቀት(፡)በገበርቆ(፡)በእገር ዕድገት፡ በእንደገና፡
በእፀቀት፡ ለይ፡ ከቀት፡ ገደት፡ ይረዳል።

[illegible]

02.3 01-6 06 01.X

[illegible]

[illegible]

06 [illegible]

[illegible] 06 [illegible]

06 [illegible] 06 [illegible]

[illegible] 02.3 [illegible]

01.5 [illegible] 06 [illegible]

[illegible]

06 01.5 [illegible] 01.5 [illegible]

[illegible] 06 [illegible]

[illegible]

[illegible] 02.3 01.1 [illegible] 03.1 [illegible] 01.4 [illegible]

06 – [illegible]

06-[illegible]
01.5
01.4
01.1
} [illegible]

– 02 – 02.1 ⇒ 02.7 } [illegible]

– 03 – 03.1 ⇒ 03.2 } [illegible]

# አባሪ 6

## የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች

ሀ. የቁጥር አለመስማማት ፡፡

- የፈተናው ቀን አንዱ ሳምንት ሲቀር የትምህርት አይነቶች ተመንተው ማለቅ አለበት::
- ከዚህም በተረፈ በዚያን ወቅት በፈተናው ወቅት በስርዓት የምያስፈልጉ ነገሮችን ይዘው ::
- አብዛኛው ተማሪ የወደፊቱን አላማ ለስተካከላቸው የምቻለው በራሳቸው ጥረት እና አካባቢያቸውን በመልማት የወደፊት አላማቸው እንዲሳካላቸውም ከህብረተሰቡ ጋር ተባብረው መስራት አለበት
- የገጠር ህዝብ በጣም ችግረኛች ስለሆኑ ልጆችን ወደ ከተማ ወስደ ማስተማር ስለማይችል .... ልጆችን ሳያስተምሯ መሃይም ሆኖ ያስቀራል
- የጸታ ትምህርት አለመስጠቱ ብዙ በሽታዎች ሰውን እያጠቃ ነው
- ይህንን ለማስወገዱ ቀላል ዘዴ አሉ
- ከዚያም ደግሞ ህፃናቸውን በጥሩ ሁኔታ ያሳድጉትና
- ለሰው ልጅ መሰረቱ እናት ከመሆኑ የተነሳ ማንኛውም ፍጡር ያለእናት መገኘት አይችሉም
- የእናት ውለታዎች ተወርተው ተነገረው አያልቅም
- ለምሳሌ በአገራችን ይበልጥ የሚመረተው ብዙ እህሎች ናቸው
- ከወደቁም በሀላ ይህ ጉርፍ በአፋና በአፍገጫው ይገባና ይህንን ልጆች ይሞታሉ ...

ለ. የጾታ ስምምነት ፡፡

- አንዱ ታላቅ እህት ሁልጊዜ--- አታጠናም ይሻል ሃለ ወ ዩውለህ ተወድቅና --- ተለኝ ነበር:: እኔ የዛን ጊዜ ... ጠለቅ ብዬ ስለማላውቅ የሱ ምክርና የሱ ቁጣ ምንም አይመስለኝም ነበር::
- ውብነሽ የምትባል ልጅ ነበረች:: በጣም ወደድኩት:: ወደድኩሽ ብዬ ለነገራት አልቻልኩም በጣም አፈራ ነበር::

- ከበደች ክበት ለቀማ ስትሔድ ከአንድ ልጅ ጋር እያወራሽ በምትሔጂበት ጊዜ ቶሳ
  ከጋራ ቤት ቤት ወጥቶ ብቅ አለበት
- አባትየው ወደውጭ ሲወጣ ከበደች በሩጫ ወደቤት ገባች ደራርቶም አንቺ! ምን አጠ
  ፋሽ ዛሬ ደግሞ አለቻው ::
- የእናት ውለታዎ ብዙ ነው:: በመሆኑም እንደዚህ አይነት ውለታ ለምውል ሰው አፀፋ
  ውን የምመልስ ልጅ መሆኑ ግልፅ ነው ::

...

ሐ. የአጧማሪዎች አጠቃቀም ስህተት

- ከወደቀም ባህሉ ይህ ጐርፍ በአፍና አፍንጫው ይገባና ይህንን ልጆች ይሞታሉ::
- ጐርፍ አደገኛ ስለሆነ አገራቸውን በአንድ ጊዜ ጠለፈው ይህ ልጆች ጐርፍ ውስጥ
  ይወድቃሉ
- ይሁን እንጅ ቢሆንም እኔ ደግሞ በበኩሌ ተ/ቤት ገብቼ መማርን ጀምሬ መመኘትን
  ጀምሬ እንደነበረ የአእምሮዬ ክፍል ይመሰክራል
- በገጠር አካባቢ ከሰኔ አስከጥር ሰዎች ከብቶታቸውን ይጠብቃሉ:: ያንን ከብቶች
  የሚጠብቀው ልጆች ቢሆን እድሜያቸው ከ6 - 12 ዕድሜ ያላቸው ልጆች ናቸው
- ለማንኛውም ሰው አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን ነገር ግን በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ
  የሆነ ማስተዋል እንዳሉባቸው ማስገንዘብ ይኖርባቸዋል::
- የወደፊት ምኞቴ ይሄንን ይመስላል:: ይህንን ነገሮች እንዲሟላ ጥረት የሚያደርግ
  ልኝ ደግሞ የመንግስት እርዳታ ይፈልጋለው
- ተምሬ ጥሩ እንዲሆም ነገር ግን በጣም ቀንጀ ደረጃ ለመያዝ እፈልጋለሁ
- የፈተና ውጤት አስከፊ የሆነ ጬረስ መወሰን አንዳንዴም መልካም አይደለም ይሁን
  እንጅ ነገር ግን የወደፊት ምኞቴ ዶክተር ለመሆን እፈልጋለሁ::
- ...
- በገጠር አካባቢ ከሰኔ አስከ ጥር ሰዎች ከብቶቻቸውን ይጠብቃሉ ::
  ያንን ከብቶች ልጆች ቢሆን ዕድሜያቸው ከ6 - 12 ዕድሜ ያላቸው ልጆች ናቸው

...

# አባሪ 7

## ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች

እና ይህ የፈተና ሰዓን በእኛ አካባቢ ሳይሆን በሁሉም ነገር የሚከናወን መሆኑን ሃገርንም ሆነ ሰውን ሳይለይ እንደፈተናው ሁሉ ቀኑ /ሰሙ ተ ይወገታል / ይህ የፈተና ሰዓን ለመምጣት የራቀ ከሆነ ተማሪው ቶሎ እንደማይመጣና በመጨም እንግሚሰራው ሁሉ ሽሳ ብሉት ልክ የፈተና ሰዓን ሲደርስ ቀን ከለሉቱ የቀን ሰርተ እንደሚተው ያሳጣዋል፡

የምገርመው ነገር ቢኖር የተፃፈው ከመስከረም እስከ ፈተና ሰዓን ብዙ ታሪክ ያሳያል እንደዚሁም በተማሪዎች ብቻ ሳይሆንና የፈተና ሰዓን ተዘታ በመምህራንም ላይ የሰነፍ ተማሪ ለምን አወድቃለሁ ብዬ መምህሩ በጣም ጠንቀ ያዘጋጀውን ፈተና በምንጩ ምበት ወቀት ተማሪው ደልዞ አጥፍቶ ቁጥር ይህን ነው የምለው ለምንድን ነው የሚሳገኘው እያለ እንኳ ስሳንተያ ይደምራል

ለመሆኑ ለእናት የምያስብ ስንቶቻችን ነን ? እያ ሁሉም ለእናት ያስባል ለማለት ያስደፍራል ስለሆነምና ያሳለፋችሁ ጣጣ ሁሉ ለማስተዋል ለወደፊት ተውለዱ ማስተዋል በጣም አስረለገ ነው

ከዚያም በኋላ በክለፉ እንደእንደወጡ በተሰቦቻችንና አገራች በከፍተኛ ደረጃ እንደደረሱና እሆ በራስ ከፍተኛ ስራ ይዘን ከፍተኛ ጥቅም እንደነገን በሰባች ከእግዚአብር ጋር ክፍተኛ ምኞ በለበ እለው

ቷም ወዳን የሌለበት በሽታ ቷም በአልጋ ቶናት ሲሰወጡ ወራት ቢፈራረቀ በተራ እሱ ወሰን የለው እያበቃ ከጉድጓዱ ያይደርስ

በተለይም እናታችንን የምናስቀየው በሕፃንነታችን ዘመናት እናታችንን ከሸንት ንና ሌሎችን ነገሮች እየተከረመተች እኛ የምናሳደት መከራ የለም ለኛ ምከንያት ለባል ልጅ እያልቀስ በመባል ወንዘ የምያደርገው ውሃ እንኳን ብርቀ ይሆናታለ

ይከውም እናቱ በጣም ደሃ ከሆነች እሱ ገን የምሠራው ስራ ከፍተኛ /ኢንጅነር ከሆነ/ እቤ እሱጋ ከሄደችና ሌሎች ከዳኖች እሱን የእንቴ እናት ናት ብለው ስጠይቁ አረ የእና እናት አይደለችም ይለዋል

- ለዚኛው ብቻ አይደለም ደከተር በጣም ረቂቅና ምስጥሩ የገባው ሰው ስራው ተነገር የሚያስቅ አይደለም

- ማንኛውም ሰው በተወጋ መርፌ እንደተወጋ መፍሳት በጣም አስፈላገ ነው

- ይህ ሰዎች ዝናብ ከዘነበ በሀላ ጉርፍ በሚኖርበት ጊዜ የሚፈሰውን ጉርፍ ውስጥ ሄደው በእግራቸው ያንን ጉርፍ ውስጥ ይሄዳሉ

- አሁን ወቅቅ ባልጠበቀ ዝናብ አማካይነት ብዙ አህሎች ጠፍተዋል:: ለምሳሌ ጸጸገራችን ይበልጥ የሚመረተው ብዙ አህሎች ናቸው

- የእናት ሆዷ እሩሩ ዘጠኝ ወር ተሸከማ አሁንም ካደጉ በኋላ ለመሸከም ለልጆቿ ሌትተ ቀን የምትራራ

- ትምህርት ጨርሼ እገዝሐብር ዶክም ብሆን ኖር የአቅምን ያሀል እረዳቸዋለሁ

- በመሆኑ ለወደፊትም ንቁ እእምሮ ያለውና ግንባር የሆነ ተውለዱ ለሀገራቸ መፈርት ስለምንችል ትምህርትን ለመስጠት በብርሀ ተሰፋ ከተማሩት ሰዎች የሚጠበቅ ድርሻ ስለሆነ ... ትኩረት ያስፈልጋል ::

- በአካባቢ የሚታየውን ሁኔታ በማስታወስ ሰዎች በዚህ ጊዜ ከማሠብና ከመጨነቅ የተነሳ ራሳቸውን ማዝናናትና ካጠኑ በኋላ እረፍት እንደሚያስፈልጋቸው ባለማሠብ ሃሳባቸውን ሙሉ በሙሉ በፈተናው አወጣጥ ላይ በማተኮር ከፍተኛ ውድቀት ላይ ይደርሳሉ ::

ወዘተረፈ

## አባሪ ፬

## የጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተቶች

- እኔ የወደፊት ምኞቴ ትምህርቴን ጨርሼ አስራ ሁለተኛ ከጨረስኩ በኋላ ውጤት በማም ጣት ዶክተረት መሆን እፈልጋለው
- ፓይለት አብራሪ ፣ ዶክተሬት ፣ አስተማሪነት ፣ ተመራማሪ ለመሆን እፈልጋለሁ
- ሰነፍ ተማሪ ፈተናው ሁለት ቀን ወይም 3 ቀን ሲቀረው መኖጠፕ ይመጣበታል
- በዘንድሮ አመት 11ኛ ክፍልን አልፌ ወደ 12ኛ ከገባሁ በኋላ በፊት ያመናኁቸውን ዕውቀቶች / ነጥቦች / ደግሜ በማየት /በማስታወስ /ለE.S.L.C.E ፈተና ደህና ውጤት በማምጣት እኔና የት/ቤቱ ስም እንድንከራበት ማለተው
- ትምህርት የሰው ልጅ መሰረታዊ ህይወት ኑሮ ነው ::
- የኤድስ በሽታ አሉማችንን እያገቁ ቁጠ ያለው መንስኤው የለለው በተቻለ መጠን የአለምችን ህዝቦች በለው ዘዴ ተቀማችሁ መኖር ከኤድስ ነፃ መሆን ትችላላችሁ ::
- ኤድስ የሚባለው ቀጫጭ / ቀለጠፋ / በሽታ የመጣው ከአንደሜሎት ከሆነ ከዘንደሮ ሲሆን ··ሕለት ተገነዘቡ የማይረባ ነገር ለመባዛት ፣ ለመሠራጭ ፣ ከቦታ ወደ ቦታ መጋዝ በጣም ፈጣን ነው
- ተማገኛው የሰው ልጅ ተወለደ ለመፈፀም አንዳንዱ ህይወት መስኮች አሉ :: ከነ ዘህም አንቀ ተምሮ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስና ··· ለሃገሩ ጥምር ይጠቀማል::
- ከዚያም በኋላ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ኮምሽን ከገባው በኋላ ትምህርቱን በደንብ በማጥና በሃገሬ ምድር ላይ ወገኖቻችን በተቸገሩት ሁሉ እየተረዳዳን እኖራለሁ::
- የወደፊት ምኞት ተማሪዎች ትምህርቱን በደንብ ተከታተሉ ለጥሩ ውጤት የሚያበቃ ከሆነ ለወደፊት ብዙ ክስተቶች ልመኝ ሰለምችል ነው::
- ማገኛውም ሰው ሆኔ ተማሪ አንዱን ነገሮ ለመስራት ወይም ለመንገርም ሆነ ለመፃፍ ከፍ ተኛ የሆነ ማስተዋል ይጠይቀዋል::
- የማትሪክን ውጤት አጥጋቢ በማምጣት ወደ ሌላ ኮምፓስ ት/ቤት ለመግባት እፈልጋ ለሁ ::
- ሆኖም ይህ በሽታ በጣም አስከፊና መዳኒት ያልተገኘለት በሽታ መሆኑን እናውቃለን:: ገን ሰዎች ከዘህ በሽታ ለመከላከል የምያደርጉት አስተዋይነት አይኖርም::
- ምኞቱ ፣ ዶክተሬት ፣ ኢንጅነሪንግ ፣ እስፖርት ለመሆን ነው

- በዚህ ዘመንም ይኸው ኤይድስ የተባለው <u>በጠና ከታሰበበት</u> ምድሯን ለማጥፋት ያሰበ ይመስላል

- ይህ ተማሪ የሚመጣው ፈተናውን ለመፈተን ቁርቱ አንዱ ፊደል የማይጭር አገኘሁ ይህ ተማሪ <u>እንደ መደበኛው ተማሪ</u> ክፍል ይገባና ከተማሪዎች ጋር ተቀላቅሎ ፈተናውን ሊፈተን ይዘጋጃል

- ወጣቶች ሁሉም ነገር መስራት የሚችሉ ቢሆኑ ኤይድስ ግን ሃገሪቱን ለመቆጣጠር <u>የወጣት</u> ማለት ነው::

- እኔም ተምሬ መልካም <u>የስራ መስክ አምጥቼ</u> የቤተሰቤን ውለታ መመለስ አለብኝ

- የኤይድስ በሽታ በወባ ትንኝ አማካይነት አይታለፍም ይህ የሆነበት ምክንያት የወባ ትንኝ ደም ትመጣለች እንጂ ደም ወደ ሰው <u>አልተስተጋባም</u>

- ብዙ ሰዎች የወደፊት ምኞታቸውን በተለያየ <u>የአስተሳሰብ አሳማ</u> ያያሉ::

- እናት የሚባለው <u>ታሪክ በብዙ ታምራት የሚቆጥር</u> መሆኑን የአሳብን የእናትን ሁኔታ መከረል አለብን ማለት ነው ::

ወዘተርፈ

# የለርብተ ገኛ-ብ ከጦቆቆም ለሁተቶምክሎ

[illegible]

[illegible] ቅጣቱ

በዚሁ አጠቃ ለዘሬዎችና ከዘሬዎች ውጭ ወገኖችን ባልጠበቀ ሁኔታ አስከፊውን
የተከለከለ የአጼዩ መንግሥታት እንደ በለቆችና በንጉሥ ላይ ክህደት ነው
እስከተፈጸመ[03-2] [illegible] መንግሥቱም ፋሽስት ለመፅናት ስለ ንጉሥ አስረዳ[03-2]
የተከበሩት መንግሥታት ርሱ የመንግሥትም በተባበረው እንደ የመረጃ ውስጥ
ሠራዊቱ የመለከት ወቅ እስከ[03-2] ይገባሉ ይሁንም ሠራዊቱ ለግድቡ[03-2] በተለይ
በዘገቦች [illegible] ለጸሎት እንደየአገሩ ስለ ንጉሡ እንደ ሚገባ[03-2] የመንግሥ መንግሥ
እንደአገሩ ለሌሎ እንደሚገባ የአቋም ወገን ቃልና በእንግሊዝ ህዝቡን
የመንግሥ አንድነቱ ለዘሬዎች ለመሳሰሉ ከንጉሥም ጋራ እንደገለጸ[03-2] ስለ ዘሬዎች
ይህ መጠለል እስ ተፈጥሮ[03-2] የስለ ለዘሬ ህዝብን እንዲያ[03-2] ስለ ለዘሬዎችን ለዚህም
ወደፊት[03-2] በዚሁ ለገንዘብ ደጋፊዎች ለመሆኑ በፊት እስከዚህ ውስጥ ገበሬ[03-2] በዚህ
ምክንያት የተለያ ቀስዞ ለዘሬ ህዝብንና ንጉሥ ለወገ ቀንድ ለሌዘሬ ሀገሩ
ቅዱሳ በሰራተኛ ለአገ በስደተኛ ወሰ ሰዎች ለዘሬ ለበሀ የሚለምዩዩ
ሊሰሙ [illegible] መለኮት ነው[03-2] ምክንያቱም ለዘሬ ይደግፋሉ ንጉሥ ሃገሩ የሚገኘው
ስለ በመከፋት ከተቀበለ ሌሎች ብቻለሁ[03-2] ሠራዊቱ የለንም እንደ በለለ ዋና በምክር
ይህ ሀገሮችን ስለ የንጉሥ መሳሪያ ያለክንያት[03-2] ምክንያቱም ነው ይህም ከፈተል
የሆቴሉ ንጉሥ ለተባ እንደነገሩም[03-2] ደግ በለዘገ የተባሉ የዘሬ ሀገር
የለቀቁም[03-2] ሰዎች ባለተለዩ እንደነው ሠራተኞችን ለመሆ ብቻለሁ[03-2]

<u>ማረጋገጫ</u>

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑንና በጥናቱም የተጠቀምኩባቸውን ድርሳናት ዋቢነታቸውን በትክክል ማመልከቴንና መሰነዴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ደብሬ ተሰማ

ፊርማ ፡- ______________

ቦታ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ኢት. ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የማስረከቢያ ቀን፡- ግንቦት 21/ 1990 ዓ.ም.